مؤسسة دار الفكر
Dar Al-Fiker Foudation
فنفني – إثيوبيا

# مقاصد الشريعة
# دليل للمبتدئ

جاسر عودة

# የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች
# የጀማሪዎች ጠቃሚ (መሪጃ)

አዘጋጅ፡
ጃሲር አውዳ

ተርጓሚ፡
ዳር አል ፊክር ፋውንዴሽን

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2021

# مقاصد الشريعة دليل للمبتدئ

جاسر عودة

# የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች የጀማሪዎች ጠቃሚ(መረጃ)

**አዘጋጅ፡**

ጃሲር አውዳ

**ተርጓሚ፡**

ዳር አል ፊክር ፋውንዴሽን

የቅጂ መብት ለዳር- አልፊክር ድርጅት በህግ የተጠበቀ ነው : :

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2021

**DF-E-TrBs-21/95**

**ማውጫ**

- መግቢያ---------------------------------------------------------------------4
- የደራሲው ፡መግቢያ ስለኪታቡና፡ትርጉሙ፡(አስተያየት)--------------6-

ምዕራፍ፡አንድ-----------------------------------------------------------------------8

-የሸሪዓ፡መዳረሻ ግቦች(المقاصد)ማለት ምን ማለት ነው-------------------------8

-"ለምን?"የሚለው ጥያቄ፡ደረጃዎች-----------------------------------------------8

-ግብ(መቃሊድ)ና፡በጥቅም(መሣሊህ)መሀከል ያለውልዩነት: -------------------10

-የመዳረሻ ግቦች(መቃሊድ)አጠቃላይ፡ይዘት፡ ------------------------------------11

-በሰሀቦች ዘመን የነበረው፡በመቃሲድ ዙሪያ የነበረው ምርምር: ---------------20

-ለመጀመሪያው፡ ዘመን ግዜ፡የነበረው፡ስለመቃሲድ እይታዎች : --------------24

ምዕራፍ ፡ሁለትከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ የሂጅራ/ ዘመን የነበሩ፡

"የመቃሊድ" ሊቆች፡ ------------------------------------------------------------28

-አልኢማም አልጀውዚ፡ "የብዙሀን ፍላጎት" "ጥቅል ፍላጎት": ------------------28

-አልኢማም አልገዛሊ፡ "የአስፈላጊ ነገሮች ደረጃ": -------------------------------29

-ኢዘዲን ቢን አብድሠላም "ከህግጋት ጀርባ ያሉ ጥበቦች": ---------------------30

-አልኢማምአልቂራፊ "የነብዮ ሰ.ዐ.ወ. ተግባራት: ------------------------------31

-አልኢማም ብነኢአቀይም "የሸሪዓ፡ትክክለኛ ምንነት: -------------------------31

-አልኢማም አሻጥቢይ፡መቃሲድ የሸሪዓ፡መስረታዊ፡ጉዳይ: -------------------33

ምዕራፍ ሦስት በዘመናችንየእስልምናን ተሃድሶ ለማረጋገጥ

የመቃዲስ ዕውቀትያለው ሚና: ----------------------------------------------35

-የመቃሲድ ዕውቀት የልማት ፕሮጀክትናየሰብዓዊ መብትን: ------------------36

-መቃሲድ ለአዲስ ምርምር መሰረት: ------------------------------------------41

-ምክንያት ወይም መንገዶች(ወሣኢልና) ግቦች(ጋያት) ያላቸው ልዩነት: ------47

-መቃሲድና በርዕስ ላይ የተፈረጀ የቁርዓን ተፍሲር(ትንታኔ) : ----------------51

-ነብያዊ መቃሲዶችን መረዳት -አድራሽ መንገድንበመዘርጋት

አንጻር አድራሽመንገድን መክፈት: -------------------------------------------52

-አለም አቀፋዊነትን ሃሳብን ማረጋገጥ- መቃሲድ በኢስላማዊ

ት/ቤት የጋራ መድረክ: ----------------------------------------------------60

# መግቢያ

አለም አቀፍ የኢስላማዊ ሀሣብ (ፊክር) ተከም ይህን የመቃሲድ ሸሪዓ ዕውቀት ጠከሚ መጽሐፍ ለአንባቢያን ሲያቀርብ በታላቅ ደስታ ነው። መቃሲድ ሸርዓ (የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) ዕውቀት የእስላማዊ ድንጋጌዋና ዓላማን የሚያስረዳ የዕውቀት ዘርፍ ሲሆን ይህ መጽሐፍ የመቃሲድ የሸሪዓ ዕውቀት ዘርፍ በቀላሉ ያስተዋውቀናል። የመጽሐፉ ደራሲዶ/ር ጃሲር ዐውዳናቸው፤ እርሳቸው ሁለንተናዊ የሸሪዓ ሊቅ ሲሆኑ የመቃሲድ ሸርዓ (የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) ልዩ ዕውቀት አላቸው።

በእንግሊዘኛ ከንከ በመቃሲድ ሸሪዓ ዙርያ የተጻፈና የተተረጎመ መጽሐፍ ቁጥራቸዉ አናሳ በመሆኑ ይህን ክፍተትለመሙላት አለም አቀፍ ኢስላሚ ፊክር(ሃሣብ)ተከም ከመቃሲድ ጋር  በተያያዘ የተጻፉ የተለያዩ መጽሐፎችን ለመተርጎምና  አሳትሞ ለማሰራጨት ወስኖ ይሰራል። ይህን መነሻ በማድረግ ይህ ውሰብሰብ ያለዕውቀት በቀላሉ መልኩ ለእንግሊዘኛ አንባቢዎች ለማቅረብ እስካሁን የተለያዩ መጽሐፎችን ተርጉሟል መቀሲድ ሸሪዓ አል ኢስላሚ (የሸህ ሙሐመድ አሹር) መጽሐፍ፤ ነዘር የቱል መቃሲድ ዒንደ ኢማም አሻጥቢ (የዶ/ር አህመድ አሩይሱነይ) መጽሐፍ ነህው ተፍኢል መቃሲድ አሸሪዓ(የዶ/ር ጀማሉዲን ዐጥያህ) መጽሐፍ ከተተረጎሙት መጽሐፎች መሀከል ናቸው።ተከሙ መቃሲድ አሸሪዓፊልሰፊቱን ሊተሸሪዕ አልኢስላሚ የተባለው የዶ/ር ጃሲር አውዳ መጽሀፍ በመተርጎም ላይ ነው።

የመቃሲድ ሸሪዓ ርዕሥ የተሳሰረና ለመረዳት የሚያስቸግር  በተግዳሮት የተሞላ ስለሆነና በርዕሡ ዙርያ ያሉ ድርሰቶች አብዛኛዎቹ ለዘርፉ ባለሙያዎች፤ ለአዋቂዎች ለሙህራንየተጻፉ በመሆናቸው የአለማቀፉ ድርጅት  የለንደን ቅርንጫፍ ቢሮቀለል ያሉና ለጀማሪ የሚሆኑ መጽሐፎችን በማሣተም ያሰራጫል።ከዚህለጀማሪዎች ጠቃሚእንዲሆን ታስቦ ለተዘጋጀ መጽሐፍ በተጨማሪ  የዶ/ር መሐመድ ሃሺም ከማሊይ መጽሐፍ የሆነው አደሊል አልሙበሠጥ ፊመቃሲድ አሸርኢያ ፤ የዶ/ር መሐመድ ኡመር የሆነውን አሩያ

አልኢስላሚያ ፊመቃሲድ አሸሪዓ የተሰኘውን መጽሐፍ ተተርጉሟል በቅርቡም ለአንባቢያን ይሰራጫል ኢንሻአላህ።

አነስ አሸህ አሊ

የአለም አቀፍ ኢስላማዊ ፊክር (ሃሣብ)ተበም የአካዳሚው አማካሪ የለንደን ቅርንጫፍ

ለንደን፥ጃንዋሪ 2010 ረጀብ 1431 ዓ.ሂ.

## ስለ መጽሐፉናትርጉሙየደራሲው አስተያየት

የአለም አቀፍ ኢስላማዊ ሀሣብ(ፊክር) ተከም ከተከከመበት 1980ዎች ጀምሮ ለመቃሲድ ሸሪዓ(ለሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) ዕውቀት ዙሪያ የሰጠው ትኩረት ጉልህ ነው። ለዚህም የሚያሳትማችውና የሚያሰራጫቸውመጽሐፎችና በራሪ ወረቀቶች፤የሚያከናውናቸው ዝግጅቶች ጉልህ ማሣያ ናቸው። የተከሙይህ ጥረት በሙስሊሙ አለም በዚህ የእውቀት ዘርፍ የሚደረገውን ጥናትና ምርምርላይ ለውጥአምጥቷል። በመጨረሻዎቹ አምስት አመታትተከሙይህን የእውቀት ዘርፍ በእንግሊዘኛ ከንከ ለማስተዋወቅ ብዙ ስራዎችን ሰርቷል ። ፎረሞችና ኮርሶች ያዘጋጃል በራሪ ወረቀቶችያሰራጫል በአረብኛ የተተርጎሙ ና በእንግሊዘኛ የተፃፉ መጽሐፎች ማቅረቡ ተከሙ ለዚህ የእዉቀት ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ሌላ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ከዚህ ቀደም በእንግሊዘኛ ከንከ የጻፍኩትን መጽሐፍ ተከሙ ቢያሳትምልኝም የመጽሐፉ ይዘትና የተጠቀምኩት ሙያዊ ቃላት የእንግሊዘኛ አንባቢያን ዘንድ በስፉት እንዳይዳረስ አድርጎታል። የተቋሙ የለንደን ቅርንጫፍ የአካዳሚ አማካሪ የሆኑት ወንድሜ ዶ/ር አነስ አሸይኽ አሊ በእንግሊዘኛ ከንከ የተጻፈና ቀለል ያለለ ጀማሪዎች መግቢያ የሚሆን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ ስለጠየቁኝ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ተነሳስቻለሁ። ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ የሸሪዓ ጥልቅ እውቀት የሌለው ማንኛውም ሰውሊያነበው እንዲችል በማሰብ የጻፍኩት ሲሆን ስለእስልምናድንጋጌዎችና ፍልስፍና ለማወቅ የፈለገ ሁሉ የፍላጎቱን ያገኛል ብዬ አስባለሁ። ይህ በእንግሊዘኛ ያዘጋጀሁትመጽሐፍ የአረብኛ ከንከተተርጎሞሳየው ከፍተኛደስታ ነው የተሰማኝ።ወደአረብነኛ ከንከየመለሰውን ዶ/ር አብዱለጢፍ፲ያጥን ማመስገን እፍልጋለሁ።ይህ መጽሐፍ በደንብ መልዕክንቱ አንዲደርስ የተሰራና በቀላል ከንከ የተተረጎመነው ። የሸሪዓ ዕውቀት ተማሪዎች በዚህ የእውቀት ዘርፍ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ቢፈልጉ “ነውጡልአህካም

አሸርኢያ ቢመቃሲዲሃ"  (نوط الاحكام الشرعية بمقاصدها) የተሰኘውን መጽሐፍን እንዲያነብ እመክራለሁ፡፡

ይዚህን መጽሐፍ ዝግጅት ከዳር ለማድረስ አስተዋጽኦ ያደረጉትን በዚህ ታላቅ ተከም ውስጥ የሚሰሩ ወንድሞችን አላህ(ሱ.ወ)ከፍ ያለ ምንዳ እንዲሰጣቸው በመቃሲድ ሸሪዓ እውቀት  ህዝባችን እንዲጠቀምና ዕውቀቱም እንዲስፋፋ ጌታዩን እማጸነዋለሁ።

## ምዕራፍ አንድ

## መቃሲድ(የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) ማለት፡ምን ማለት ነው

## "ለምን?" የሚለው ጥያቄ ደረጃዎች

ህጻናቶች ሆን ብለው ይሆን ሣያውቁት ለመገመት በሚቸግር መልኩ የፍልስፍና ጥያቄ ሲጠይቁ እንመለከታለን ፡፡ ደስ የሚለው ግን ህጻናቶች እንደ አዋቂ ይህን መሠል ጥያቄዎች የሚያነሱት በእውቀትወይም በአምነት ላይ ተመስርተው አይደለም፡፡ ብዙ ግዜ በመቃሲድ አሸሪዓ (የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) ዙርያ ስልጠና ሲሰጥ አባዃን የበዛጥያቄ በምጠይቀው የትንሽ ልጅ ታሪክይጀምራል፡፡ ልጅቱ አባቷን እንዲህ ስትል ትጠይቃለች "አባዩመኪናዎች ትራፊክ ማብራትላይ ለምን ይቆማሉ?"አባዃም ኣንደ አስተማሪ በመሆን "ቀይ መብራት ስለበራ ነዉ ቀይ መብራት ደግሞ ቁም ማለት ነው"ይላታል፡፡ነገር ግን ልጅዮ ጥያቄዋን አላቆመችም "ግን ለምን ይሄይሆናል？" ብላአሁንም ትጠይቃለች በአስተማሪ አኳኃን ወላጅ አባዣ "ይህን ካላረግን የትራፊክ ፖሊስ ይቀጣናል" ይላትል፡፡ትንሿ ልጅ ቀጠለች "የትራፊክ ፖሊስ ለምን ይቀጣናል?"አባት መለሰ "ቀይ መብራት ጥሶ መሄድ ለአደጋ ስለሚያጋልጥ ነው" ህጻኗ ለምን?የሚለውን ጥያቄዋንላባዃቀጠለች "ወላጅ አባዣ፡"ነገሩ እንዲህ ስለሆነ ነው ብሎ ጥያቄዋን በደፈናዉ ለመቃወም ቢፈልግም የበለጠ ትዕግስት በመላበስ "ሠዎች ላይጉዳትማድረስ አግባብ አይደለምና ነው አንቺ ጉዳት ቢደርስብሽ ትወጃለሽ？" ሲል ጠየቃት "አይ አልወድምበማለት መለሰች "ሌሎች ሰዎችም እንደዚሁ ጉዳት እንዲደርስባቸውአይፈልጉም" ነብዩ ሰ.ዐ.ወ. ለራስህ የምትወደውን ለሌሎች ውደድ ብለዋል"አላት፡፡ ትንሿ ልጅ ግን ጥያቄ ማቅረቧን አላቆመችም "ለምን ለራስህ የምትወደውን ለሌሎች ትወዳለህ" ስትል ጠየቀየች፡፡ አባዃትንሽ አሰበና እንዲህ አላት ምክንያቱም ሠዎች ሁሉ እኩል ናቸው" ለምን ብለሽ ከጠየቅሽኝ

አላህ ፍትሃዊ ስለሆነሁላችንም እኩል መብት አለን፤ እኩል አድርጎ ፈጠረን፤ አላህ ዩንቨርሱን የፈጠረውበፍትህ መሠረት ላይ ነው።

“ለምን?”የሚለው ጥያቄ “መቃሲድ ማለት ምን ማለት？” የሚለው ጥያቄጋር ተነፃፃሪ ነው “ለምን？”በሚል ጥያቄ የሚነሳምርምር ”አቻ ነው።□እነዚህ ቃላቶች የተለመዱ የፍልስፍና ቃላቶች ሲሆኑ በመቃሲደ ሸሪዓ የእውቀት ዘርፍ ውስጥ በፊቅህ ሊቆች ዘንድ በተደጋጋሚ ይነሳሉ። ይህን መሠረት በማድረግ “ለምን？”የሚለውን ለመመለስ ስንነሳ በህፃ□ና በአባታታሪክ እንደተመለከትነው፡የትራፊክ መብራትህግ፤ቅጣትየመሳሰሉትን ጥቃቅን ዝርዝር ምክንያቶችንከማንሳትይልቅ ሰፊና ጥልቅ የሆነውን ዋና ግብ ማለትም የጋራ ጥቅም፤የሰዎች ደህንነት፤ ከዚህም አልፎ ዋና መርህ የሆነው ወደአላህባህሪ ፍትህናእዝነት እንደርሳለን።

ከዚህ በመነሳት የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች(መቃሲደሸሪዓ) “ለምን?” በሚል መልኩ በሁሉም ደረጃዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ እስላማዊ የእውቀት ዘርፍ መሆኑን እንረዳለን ነገሩን የበለጠ ለመረዳት የተወሰኑ ጥያቄዎችን እናነሳለን።

-ዘካመስጠትለምንአንዱ የኢስላም መሰረትሆነ?

-ለጎረቤት በጎ መሆንለምንኢስላማዊ ግዴታ ሆነ?

-የሙስሊሞች ሰላምታለምን “አሰላሙ አለይኩም ሆነ?

-የረመዳን ወር መጾም ለምን አንዱ የኢስላም መሰረት ሆነ?

-ሙስሊሞች ሁል ግዜ አላህን ለምን ያወድሳሉ?

-ሆን ብሎ ሠውየገደለ ወይም.........ሠው ፍርዱ የሞት ቅጣት ለምን ሆነ?

መቃሲድ ሸሪዓ(የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች)የአውቀት ዘርፍ ከህግጋት ከድንጋጌዎቸ ጀርባ ያሉትን ግቦችናጥበቦች ይተነትናል

ለምሳሌ፡ ከዘካ ድንጋጌ፤ ለጎረቤት መልካም መዋል፤ ከሰልምታ መለዋወጥ በስተጀርባ ማኅበራዊ ትስስር ማጠንከር አንዱ ጥበብ ና ግብ ሆኖ እናገኘዋልን። ከልካይ ፤ ፈቃጅ ፤ አዛዥ የሆኑ ሀይማኖታዊ ድንጋጌዎች ህግጋትመልካም ግብን ዓላማ ያደርጋሉ። ከግቦቹ መካከል የሰዎችን ነፍስ፤አዕምሮ፤ ደህንነት መጠበቅ አንዱ ሲሆን ለምሳሌ ፡ኢስላም እስካሪ፡መጠጦችን በጥብቅ ሲከለክል የሰዎችን ንብረትና ክብርለመጠበቅ በማሰብ ነዉ። የሞት ቅጣት ሲደነገግ በሱረቱል በቀራ1785 በሱረቱል ማኢዳ 33 እንደ ተገለፀው የግድያ ወንጀልንና ጥፋትንለመከላከል ነው።

መቃሲድ(የመዳረሻ ግቦች)የእስልምና ሸሪዓዊ ድንጋጌ መሰረት የሚያደርገዉ እንደፍትህ፡የሠውልጅ ክብር፣የማህበራዊ ትስስር፣ጥብቅነት፤ገርነት፣የነጻነት ፍልጎት ፡የመሳሰሉት መለኮታዊ ዓላማዎችንና ስነ ምግባራዊ ግንዛቤዎች ነው። እነዚህ ግንዛቤዎች ና ዓላማዎች በአሁኑ ግዜ በብዛት ከሚነሱ ዘመናዊ ግንዛቤዎችማለትም ልማት ፤ ማህበራዊፍትህ፤ሰብአዊ መብት ጋርየሚያገናኙ ድልድዩችናቸው።ይህ እውቀት በዘመናችን የሚነሱ አዳዲስ ጥያቄዎች ለመመለስ፡ ያስችላል፡ለምሳሌ፡- ቁርዓንና ሀዲስን ለመገንዘብና የዘመናዊውን ዓለም በሚያወያይ መልኩ ከእንደገና ለመተንተን የተሻለው መንገድ ነው። ለቀጣዮቹ ጥያቄዎች መልስ ምይሰጣል ።

-ሥለ"ነጻነት"ና "ፍትህ" ኢስላማዊ ጽንሰ ሃሳብ ምንድ ነው?

-ሠብዓዊ መብትን በተመለከተ በኢስላም ሸሪአዊ ድንጋጌናበዘመናዊ አስተሳሰብ መሀከል ያለው የጋራ ነጥብ ምንድነው?

-እስላማዊህግ(ሸሪዓ)ልማትን፣ስነ ምግባርን፣ማህበራዊ ፍትህን ለማረጋገጥ ምን ሚና አለው፡

እነዚህን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ፡በመቃሲድ የእውቀት ዘርፍ የሚገኙ፡ ሙያዊ ቃላቶችናበዘርፍው የተደረጉጥናቶችን ዕይታዎችን እንመልከት፡፡

## <u>በመቃሊድ(በመዳረሻ ግቦችና) በመሣሊህ(በጥቅም) መሀከልያለው ልዩነት</u>

መቃሲድ -መቅሰድ የሚለው ቃል ብዜት ሲሆንግብ፣ዓላማ፣መዳራሻ የሚል ምልዕክት አለው በእንግሊዝኛ "ኢንድ"

በፈረንሣይኛ ቴሌዮሰ ፤ በግሪክበንክ ፊናሊ፝ዮ፤በጀርመንኛዝፊይክ የሚሰጡትንትርጉም ይሠጠናል።

የሸሪዓዊ አተረጋጎሙን ስንመለከት ከኢስላም ድንጋጌዎችና ህግጋቶችጀርባ ያልዉዓላማና ግብነው፡፡ እንደ ታልቁ አሊም አብዱል መሊክ አልጅወይኒዬ ያሉ አንድ አንድ የእስልምና ሊቆች መቃሲድ (መዳረሻግብ) ናመሣሊህ (ጥቅም)ተመሣሣይና ተነጻጻሪ ትርጉምአላቸው ብለው ያምናሉ።

አብዱል መሊክ አልጅወይኒ (470 ሂ /1185 ዓ.ል የሞተ)መቃሲድና (ግብ) መሣሊህ(ጥቅም) የሚሉትን ሁለት ቃላቶች በተመሣሣይነት በመውሰድ ተጠቅማቸዋል።

ሌላኛው አሊም አቡሀሚድ አልገዛሊ(565ሂ/1119ዓ.ል የሞቱ) የጀወይኒን ሀሣብ ላይ በመመስረት መቃሲድን (ግቦችን) ከመሳሊህ ሙርስላ(አጠቃላይ ጥቅም)ስር አስገብተውታል፡፡ ከዚያ በኃላ የመጡት ፈኽረዲን አራዚ(6064/1209.ዓ.ል የሞቱ)ና አልአሚዲ(613ሂ/1234/ዓ.ል.)የገዛሊን ሀሣብ ተከትለው ሂደዋል። ነጅመዲን አጡፊይ (716ሂ/1316ዓ.ል.የሞቱ) መስለሃ (ጥቅም) ከአንድ ትዕዛዝ ጀርባ ያለውን የአላህና የረሱል(የሸሪዓን)ሃሣብ የሚያሳውቅ ነው በማለት አስተዋዉቀዉታል ። ቂራፊ ዳግም(1285ሂ/1868ዓ.ልየሞቱ) በመቃሲድ ዙሪያ አጠቃላይ ህግ ያስቀመጠ ሲሆን ህጉም እንዲህ ይላል። "የሸሪዓ መዳረሻ ግብ(መቃሲድ)ብሎ የሚወስደው ቀና ዓላማ የሚያረጋግጥ ፤ጥቅም የሚያስገኝና ፤ ጉዳት የሚያስወግድ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ የምንረዳው መቃሲድ (የሸሪዓ መዳረሻ ግብ)ማለት የሠውን ጥቅም የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፤ይህ አባባል ትክክለኛውን የመቃሲድ(የሸሪዓ መዳረሻ ግብ) ዕይታና ፍልስፍና ያስተዋውቃል።

## <u>**የመቃሲድ ይዘት (ልኬት)**</u>

የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች(መቃሲድ)የተለያዩየሸሪዓ ሊቆች እንደ ዕይታቸዉ ፡ በአንጻራዊንት በተለያዩ ምድቦች ከፋፍለዋቸዋል ከእይታዎቹ፡ መሀከል ፡
1-የአስፈላጊነት ደረጃ(ይህ የተለመደውና ቀደምቱ ምደባ ነው፡)

2-መዳረሻ ግቦችን (መቃሲድን)ለማረጋገጥ ዓላማ ያደረገ የህጎች አይነት
3-መቃሲድ(የሸሪዓ መዳረሻግቦች)የሚመለከታቸው የህብረተሰብክፍል
4-የመቃሲድ (የሸሪዓ መዳረሻግቦች)አካታችነት
የመጀመሪያውና የተለመደውአከፋፈል በውስጡ፡ሦስት ደረጃዎችያሉትሲሆን ፡-
1-አንገብጋቢ ጉዳዩች(ዶሩርያት)
2-አስፈላጊ ነገሮች (ሃጅያት)
3-ሃሃያ ወይም የቅንጦት ነገሮች(ተህሲናት)ናቸው፡፡
የመጀመሪያዉ አንገብጋቢጉዳዮች(ዶሩሪያት) የሚለዉ ክፍል፡አምስት ለሰው ልጆች በጣም አንገብጋቢ የሆኑ ጉዳዩችየያዘ ነው። እነርሱም፡- ሃይማኖተን፣ ሕይወትን፣ገንዘብን አእምሮን ዘርን፣መጠበቅ ነው። አንድ አንድ የሸሪአ ሊቆች፤ ስድስተኛ፤ ክብርን መጠበቅ የሚልጨምረዋል። እነዚህ አምስት አንገብጋቢጉዳዩችለሰው ልጅ በህይወቱይሁን ከሞተ በኃላላለው ዓለም በጣምአስፈላጊናቸው። እነዚህ አምስት ነገሮች ለአደጋ ከተጋለጡየሰው ልጅህይወቱና አእምሮዉ አደጋላይ ይወድቃል። ለዚህም ነው እስልምና አጥብቆ አስካሪ መጠጦች፤አደንዛዥ ዕጾችንእርም ያደረገው። እንደዚሁም ለበሽታ የጥንቃቄ እርምጃካልተወሰደናአካባቢያችን ከብክለት ካልጠበቅን ህይወት አደጋላይ ይወድቃል።

ይህን መነሻ በማድረግነብዩ ሙሐመድ ሰ.ዐ.ወ. ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረስ ብቻ ሳይሆን በእንስሳት ላይ ሆነበዕጽዋት ላይጉዳት ማድረስተገቢ አለመሆኑን ያስተማሩን ለምን እንደሆነእንረዳለን ።ኢስላምወለድን ፤ ሸቀጥ ማከማቸትን ፤ ሙስናንና ማታለልንከልክሏል፡እነዚህ ነገሮች ከተሰፉፉየኢኮኖሚ (የገንዘብ)ቀውስ ይከተላል ፤በሠዎች ህይወትላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ዘርን መጠበቅ ለሚለው ከፍተኛ ቦታ ሰጥቶት እናጋኛለን፡ ይህንክፍልበትኩረት
ስንመለከትቤተሰብንናህጻናትንለመንከባከብሸሪዓያስቀመጣቸውህጎችሚስጥር ይገባናል።

በመጨረሻም ሃይማኖት (እምነትን) መጠበቅየሚለውን እናገኛለን፡ ይህነጥብሃይማኖት (ዕምነት)ለሠው ልጅበተለይ ከሞተ በኃላላለው ዓለም

መሠረታዊና አንገብጋቢ ጉዳይ ነዉ ። እስልምና የዚህን ዓለም ህይወት ወደ ዋናው መዳረሻ(ዓላማ)የጉዞ አካልአድርጎ ነው የሚመለከተው።

በአጠቃላይ እነዚህ አንገብጋቢ ጉዳዩችን መጠበቅ የሸሪዓ ህግጋቶች ወይም ማንኛውምመለኮታዊ ህግዓላማና ግብ ሆኖ እናገኘዋለን።

ከተጠቀሱት አንገብጋቢ ጉዳዮች(ደሩሪያት) በመቀጠል፥በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠውን አስፈላጊ ጉዳዩች(ሃጅያት) እናገኛለን፥በህይወት ውስጥ አስፈላጊ (ሃጅያት)ከሆነ ጉድዩ መሀከል ጋብቻ፣ ንግድ፣ የመጓጓዣስልትለምሳሌነት ይጠቀማሉ፡ እስልምና እንደዚህ መስሎችን አስፈላጊ ጉዳዩችንእንዲማሉ የሚያበረታውንያህልስርዓትእንዲይዙ ያዳርጋል፥ነገርግንእነዚህ አስፈላጊ ነገሮች በከፊል ወይምበግለሰብ ደረጃ ባይሞሉ፥የሞት ሽረትጉዳይ ነውብሎ አያምንም። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ጋብቻለመፈጸምባይፈልግ፥ሌላው በንግድላይተሠማርቶለመስራት ፍላጎትባይኖረውየሠው ዘርን ህልውናአደጋ ላይየሚጥልበት አጋጣሚ አይኖረውም፥ነገር ግንእነዚህአስፈላጊ(ሃጅያት)ነገሮች ብለንየጠቀስናችውነገሮችበሰፊውማህበረሰብ ጋር ክለሉወደ አንገብጋቢነት(ዶሩሪያት) ያድጋሉ።ይህን ሃሣብ በገዢው የፊቅህ አጠቃላይህግ፤ (rule)ቃኢዳእንዲህ ተብሎተጽፎ እናገኘዋለን።

"الحاجة اذاعمت نزلت منزلة الضرورة"


"አንድአስፈላጊነገር(ሃጅያት)ሠፊውንየማህበረሰብክፍልየሚመለከትከሆነወደአንገ ብጋቢነት፥ያድጋል፡

በሦስተኛ ደረጃ፥የተጠቀሰው፡ (ተህሲናት )ýýያ ነገሮችወይምቅንጦት ዉስጥለህይወት ውበትየሚያለብሱጉዳዩች ይካተታሉ።ለምሳሌ ሽቶን፤ ውብ ልብስን ማንሣት ይቻላል፥እነዚህ ነገሮችየጌታ ቱርፋትሲሆኑ በአግባቡ መጠቀምተገቢ፥አለብን ፥ነገር ግንትኩረታችንመሆን ያለብት ለቀደሙት አንገብጋቢናአስፈላጊ ነገሮች ነዉ ።

ኢማሙ ሻጥቢይእንደሚሉት እነዚህ የተጠቀሱት የሸሪዓ መዳረሻግቦች፡ (መቃሲድ ሽሪዓ)ሦስቱምመድቦችእርስ በእርስ የተጣላለፉናቸው ለምሳሌ፡

ጋብቻናንግድአስፈላጊ ነገሮች(ሃጂያት)ዉስጥ የሚካተት ሲሆን ነገርግንሁለቱአስፈላጊነገሮችሊኖሩ ነውገንዘብንዘርንመጠበቅናማስቀጠል የሚቻለው።በሁለቱ በአስፈላጊና በአንገብጋቢነገሮች መሀከልከፍተኛ ቁርኝት አላቸው።አንድ አስፈላጊነገርክፍተቱና ዕጥረቱ በስፋትከተስተዋል ደረጃውንበማሳደግወደ አንገብጋቢጉዳይይቀየራል።ለምሳሌበበዛ ሁኔታ የንግድ ኪሣራቢያጋጥም ለኢኮኖሚ ቀውስያጋልጣል፡ይህን ግዜንግድ ከአስፈላጊ ጉዳዮች (ሃጃያት)ምድብ ወጥቶ አንገብጋቢ(ደሩሪ)ይሆናል፡ ይህንመሰረት በማድረግየሸሪዓ ሊቆችየአስፈላጊነገሮችግራፍ አቀማመጥእርስ በርስ የተሳሰረ

ክብ እንጂፒራሚዳዊአይደለምየሚሉትለምሳሌ ተከታዩንግራፍ ይመልከቱ




**የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች(መቃሲድ)ደረጃ ፒራሚዳዊ ግራፍ**

ይህ የአስፈላጊ ነገሮች ደረጃ በ20ኛውክፍለ ዘመን መካከል ላይ አብረሃም ማስሎ ያስቀመጠውን ፒራሚዳዊ ግራፍ ያስታዉሰኛል አብረሃም በግራፉ ላይ መለኮታዊ ያልሆነ የሠውልጅ ጥቅሞች ፍላጎቶች መሰረት ያደረገ ሲሆን (የፍላጎቶች መሰላል) በማለት ጠርቶታል በአብረሃም ዕይታ መሰረት ደህንነትን ጨምሮ መሠረታዊ ሦጋዊ ፍላጎት በመጀመሪያ የሚመጣ ሲሆን በመቀጠል ፍቅርና ክብር የማግኘት ፍላጎት ይከተላል በመጨረሻም "ራስን የመገንዘብ"ፍላጎትይመጣል።

ማስሎ ገና በ1947 ዓ.ል. አምስት የፍላጎት ደረጃዎች አሉ ብሎ ሃሣብ ያቀረበ ሲሆን በ1970ዎች ደግሞ ሃሣቡን በማስተካከል ወደ ሠባት አሳድጎታል እዚህ ላይ በማስሎና በሻጢቢይ መሀከል ያለው ፍላጎቶችን በአምስት በመመደብ ያላቸዉ ተመሳሳይነት አስገራሚ ነው ። የማስሎ ለውጥን ተቀባይ አመዳደብ በኢስላም ያለው መቃሲድ"የሸሪዓ መዳረሻግቦች" አመዳደብ ጋር ይመሣሰላል። የሚመሳሰሉበት ትልቁ መገለጫ በዝግታ የሚመጣ ዕድገት ናለውጥ አንዱና ዋናዉ ነው።መቃሲድ ሸሪዓ(የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች)በክፍለ ዘመን ሂደት በተለይ በ20ኛው ክ/ዘመን ከፍተኛ እድገትና ለውጥ አስመዝግቧል ።ለዚህም ነው የዘመናችን የመቃሲድ(የሸሪዓ መዳረሻግቦች)ተመራማሪዎች የዘልማዱን የዶሩያተት (ፍላጎት) አመዳደብ በተለያዩ ምክንያቶች የተቻሉ። ከሚተቹበት ምክንያት ውስጥ የተወሰኑትን እናንሳ።

1-የመቃሲድ ትምህርት ዘርፍ በቀደምት ጊዜ አጠቃላይ የሸሪዓ ህጎችን የሚተነትን ሲሆን በኢስላም ድንጋጌዎች ያሉ ምዕራፎችን አንደ አንዴ ካልሆነ በስተቀር አይመለከታቸውም ።በዚህ ምክንያት የቀደምት ግዜ የነበረውየመቃሲድትምህርት ዝርዝር ጉዳዩች ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን አይመልስም ።

2-የቀደምት የመቃሲድ(የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች)ትምህርት በምርምሩ ቤተሰብን፤ ማኅበረሰብን፤ በአጠቃላይ የሠው ዘርን ከመዳሰስ ይልቅ ለግለሰብ ብቻ ትኩረት ይሰጣል። እውነታው ተቃራኒ ሆኖ ሳለ ሸሪዓ ለግለሰ ብህይወት ፤ ገንዘብ፤ ክብር ትኩረት የሚሰጥና፡ለህብረተሰብህልውናክብር፤ ሃብትናኢኮኖሚግድ የሌለውያስመስላል።

3-የቀደሙትየመቃሲድአመዳደብ አንገብጋቢ የሆኑትን እንደ ፍትህ፤ነጻነትንያሉ አንገብጋቢጉዳዮችን አያካትትም።

4-የቀደምቱ የመቃሲድትምህርትዘርፍን ስንመለከትአብዛኛው የተወሰደውከቁርአንና ከሀዲስ ሳይሆንበተለያዩ መዝሀብ ያሉ የፊቂህ ሊቃውንቶችካስቀመጡትድምዳሜ ነው።

በዘመናችን ያሉዑለማዎች የተጠቀሱት ክፍተቶች ለመሙላት የተለያዪ ግንዛቤዎች ናአዲስ አመዳደቦች ያመጡ ሲሆን ይህም ለመቃሲድ ዕውቀት አዲስ ይዘት ና ቅርጽ አላብሶታል። ከዚህ በመነሳት የዘመናችን ዑለማዎች መቃሲድን በሦስት ደረጃ አስቀምጠዉታል።

1-ጠቅላይ የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች (አል መቃሲድ አልዓማ) ይህ ክፍል በሁሉም የሸሪዓ ርዕሦች ውስጥ የምናገኛቸውን ዓላማ ና ግቦች የያዘ ነው። በተለመደው የቀደምት ኡለማዎች አመዳደብ የተጠቀሱት አንገብጋቢ አስፈላጊ በተጨማሪ በዘመናችን ዑለማዎች ለውይይት የቀረቡትን እንደ ማኅበራዊፍትህ፣ ሉዓላዊነት፣ነገሮችን ማቅለልን ያካትታል።

2-ልዩ የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች (አል መቃሲድ አልኸሣ) ይህ ክፍል ቅርንጫፋዊ የሸሪዓ ርዕሦችናምዕራፎች ውስጥየምናገኘው ነዉ። ለምሳሌ በቤተሰብ ህግ ውስጥ የህጻናት መብትን ማስከበር ፤ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ጋር ተያይዞ የወንጀልቅጣት፤የፋይናንስ ህግ ውስጥ ሸቀጥበ ህግ ወጥ መልኩ ማከማቸትን መከልከልን ና የመሳሰሉትን ያካትታል።

3- ጥቃቅን የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች (አልመቃሲድ አልጁዝኢያይህ) የመቃሲድ ክፍል አንድ ህግ ወይም ድንጋጌ የተቀመጠበትን ምክንያት ና ግብ የሚመለከትነው ለምሳሌ ነገሮችን ማቅለል የሚልዉ ግብ ስንመለከት የሸሪዓ በጾም ዕለት ለታመመ ሰው እንዲይፈጠር ይፈቀድለታል ። ደሃዎችን መመገብ ፤ በበዓል ቀን ለሚስኪኖች ሥጋ ማከፋፈል ስንመለከት የሰዎችን ችግር ማቅለልን አላማ ያደርጋል ።

በዚህ አዲስ የመቃሲድ አመዳደ ብየ ዘመናችን ዑለማዎች በግለሰብ ብቻ የታጠረውን የመቃሲድ ዕውቀት ሰፊውን የህብረተሰብ ክፍልን ፤ቤተሰብን፤

ማኅበረሰብን፤ ሰብዓዊነትን፣እንዲያካትት አድርገዋል። ለምሳሌ ታላቁን አሊም ኢብኑ አሹርን ብንመለከት ኡማውን የሚያካትት የመቃሲድ ምርምር አድርጎ እናገኘዋልን። ኢብኑ አሹር ግለሰባዊ ከሆነው ከቅድሞዉ የመቃሲድ ይልቅ ለአዲሱ የመቃሲድ ምርምር የበለጠ ትኩረት ይሰጣል። ሌላው የዘመናችን ሊቅ ራሺድ ሪዳ ስለ መቃሲድ ባለው እይታ ለውጥን ፣ተሃድሶን ፣የሴቶች መብትን አካቷል።ታላቁ ዓሊም ዶ/ር ዩሱፍ አልቀራዳዊም ሰብአዊ ክብርን ና የሴቶችን መብት በመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ አካተውታል።

የዘመናችን ሊቆች የመቃሲድ አድማስ በማስፋታቸው ይህ የትምህርት ዘርፍ አዳዲስና ዘመናዊ ጉዳዮችን ፤ፍልጎቶችን፡እንዲመረምር በር ከፍቿል ። ከዚህ በመነሳት አንድ ዓሊም ከሁሉም ሸሪዓዊ ድንጋጌጀርባ ያለውን ጥበብ እንዲመረምርና የለውጥና ተሃድሶ ተግባራዊ ዕቅድ እንዲያስቀምጥ ዕድል ይሰጠዋል።

እነዚህ የዘመናችን ዑለማዎች መቃሲድ እውቀትና መርሁን እንደ ዜግነት፣ ውህደት፣ሰብዓዊ መብት፡የህዳጣን ሙስሊሞች ሁኔታ የመሳሰሉ አዳዲስ አስተሳሰቦች የወቅቱ ርዕስ እንዲሆን አድርጎታል።

እነዚህ ዑለማዎች ከፊቅህ ጥራዝ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከቁርዓንና ከሀዲስ በመውሰድ አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውግቦች አንስተዋል። ይህን ማድረጋቸው በዘመን ሂደት የሚፈጠሩ አዳዲስ ውስብስብ ጉዳዮች መፍትሄ እንዲያገኙ ና ቀየት ያሉ ቀደምት ዑለማዎች ብይን የሰጠባቸው ፈትዋዎች ፈር እንዲይዙ መንገድ ከፍቿል። ምክንያቱም ከላይ የተጠቅሱት አዳዲስ ሃሳቦችና ግንዛቤዎች ከእስልምና መርህጋር የሚጣጣሙ ናቸው ። በቀጣይ የዘመናችን ዑለማዎች በቀጥታ ከቁርዓንና ከሃዲስ የወሰዳቸው አጠቃልይ ግቦች (አልመቃሲድ አልኩልያ) ለአብነት የተወሰኑትን እንጠቃቅሳለን።

1-ረሺድ፡ሪዳ (1354ሂ/1935የሞቱ) ቁርዓንን በመመርመር የተለያዩ መቃሲድ (ግቦች) ያቀረብ ሲሆን የመቃሲድ ዓላማ የሃይማኖት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ተሃድሶ ማምጣት ፤የነብያት የተላኩበት ምክንያት ማሳውቅ ፤እስልምና የተፈጥሮ፣የንጹህ አእምሮ፣የእውቀት፣የጥበብ፣የመረጃ፣የነጻነት፣የማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ሃይማኖት መሆኑን አስረግጦ አልፋል። ኢስላም የአምልኮት

ስርዓትን መከወን ፣ከእርም የመራቅ ግዴታ፣በሀገራት መሀከል ያለ አለም አቀፍግኑኝነት ፣የኢኮኖሚና የፋይናንስን ለውጥናዕድገት፣የጦርነት ጉዳት መከላከል፣ ለሴቶች ተገቢውን መብት መስጠት፣ የባሪያ ፍንገላን መዋጋት የእስልምና ግቦች መሆናቸው አስቀምጣል።

2-ጣሂር ቢን አሹር (1325 ሂ/1907 ዓ.ል. የሞተው) መቃሲድ (የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) አለማቀፋዊ ነው ብሎ ያምናል።ይህ አለማቀፉዊ ግብ የህዝብን ስርዓት መጠበቅ፣ እኩልነትን፣ ነጻነትን ማረጋገጥ ዋናው ዓለማው ነው ። ኢብን አሹር ያነሳው የነጻነት "ሁርያ" ሃሣብ  በቀደም ግዜ ፋቃሃዎች ዘንድ ከሚታወቀው ባሪያን ነጻ ከማውጣት ግንዛቤ ፈጽሞ የተለየ ነው።ኢብን አሹር ያነሳው "የነጻነት" ሃሳብ በቀድሞ ዘመን በስፋት ከሚታየው "መሺኣ "ጋር ተመሣሣይነት አለው። ትርጉሙም የፈለጉትን ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ይህ ቃል የፍላጎት ፣የእምነት ነጻነትን፣ ይይዛል።በቁርአን ላይ የምናገኘውም ይህንኑ ነው።

قال تعالى: ﴿ فمن شاء فليؤمن ومن شاء فليكفر﴾

**"ያሻም ሠው ይመን ያሻም ሠው ይካድ፡" ሱረቱል ካህፍ፡29**

"ነጻነት" (ሁርያ) የሚለው ቃል ከቅርብ ግዜ ወዲህ ወደ ኢስላም መዝገበ ቃላት የተቀላቀለ ሲሆን የሚገርመው ኢቢን አሹር ነጻነትን (ሁርያን )ወደ መቃሲድ ለማስገባት ያነሣሣው ከፈረንሳዩ አብዮት በኃላ በ19ኛው ክ/ዘመን ወደ አረብኛ የተመለሱ የፈረንሳይኛ ጽሑፎች እንደሆኑ ይነገራል ። ኢብን አሹር ከዚህ በመነሳት ኢስላም የሃሳብ፣የእምነት፣ሃሳብን የመግለጽ፣የስራ ነጻነት ዙርያ የለዉን እይታ በስፋት አብራርቶ የመቃሲድ አንድ አካል መሆናቸው አስቀም√ል።

2-ሙሐመድ አል ገዛሊ፡(1416ሂ /1996 የሞተ)ካለፉት አስራ አራት የሂጅራ ክ/ዘመናት የእስልምና ታሪክ ትምህርት መውሰድ ተገቢ መሆኑን ያሳስባሉ። ይህን መሰረት በማድረግ ሙሐመድ አልገዛሊ "ፍትህና ነጻነትን" በመቃሲድ ሸሪዓዋና ክፍል በሆነው አንገብጋቢ ጉዳይ (ደሩሪያት)ስር አካቷቸዋል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዘመን መቃሲድ በተመለከተ የቀደመውን አመለካከት ቃል በቃል እየተተረጎሙ እግር በእግር እየተከተሉ የሚሄዱ ዑለማዎችን መተቸታቸው እንደ ትልቅ አርማጃ ይወስዳል ። ሼህ አልገዛሊ የጻፉቸውን ጽሁፎች ስንመለከት

እኩልነትን፣ማህበራዊ ፍትህን፡ከመቃሲድ አካል አድርገው፡ያስቀምጡታል፡ ስለሴቶች ያላቸውን ዕይታ የተነተኑበት ሁለቱን መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እኩልነትን፣ማህበራዊ ፍትህን፡ መነሻ በማድረግ ነው።


4-ዩሱፍ አልቀርዳዊ (1345 ሂ/1926 የተወለዱ ) የቁርዓንን ገፅበገፅ በመመልከት በማጥናት በአጠቃላይ ስለ ስነ መለኮት ፣ነብያዊ ተልዕኮ ፣የትንሳኤ ምንዳ፣የሰው ልጅ ክብርና መብት፣ ስብከትን፣የሠው ነፍስን ፅህና ፣ ሥነ ምግባር፣መልካም ቤተሰብ መመስረት ፣የሴት ልጅ ፍትህማግኘት፤ኡማን መገንባት፣በትብብር ላይ የተመሰረተ ሰብዓዊ አለም መመስረት የሚባሉትን ግንዛቢዎች ላይ ያለን እምነት ናዕይታ መታደስ ይገባዋል ብለው ያምናሉ። ሼህ አልቀርዳዊ ይህን ይበሉ እንጂ ማንኛውም በመቃሲደ ሸሪዓ ዙሪያ የሚሠጡ አስተያየቶች የቁርአንና የሀዲስ በቂ ዕዉቅትና ልምድ ካለው ሰው መሆን እንዳለት ያሳስባሉ።

5-ጠሃ አልዓልዋኒ (1354 ሂ/ 1935 የተወለዱ) ቁርዓንን ሙሉ በሙሉ በጥልቀት ካጠኑ በኃላ (ከፍተኛ ናገዢ የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) ያላቸውን መቃሲድ አስቀምጠዋል ። እነሱም፡- ተውሂድ፣ ነፍስን ማንጻት፣ምድርን ማሳመር ናቸው፡፡ እነዚህን ሦስት ግንዛቤዎች የበለጠለ ማብራራት አልዓልዋኒ ምርመሮችን እየጻፉይገኛሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን ግቦች(መቃሲዶች)የዘመናችን ዑለማዎች በመቃሲድ ዘርፍ ለውጥ ና ተሃድሶ ለማምጣት ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል።በቀደምት ግዜም ሆነ በዘመናችን ዑለማዎች ያስቀመጡት የመቃሲድ አመዳደብ ናአከፋፈል ፍፁም የአላህ ፍላጎት ነው ማለት አይቻልም ። የሠው ልጅ የሚያስቀምጣቸው ምድቦች ና ክፍሎች የራሱ የሠው ልጅ የምርምር ውጤቶች ሲሆኑ ይህም ሠው ነገሮችን ለማብራራትና ለራሱቀላል ለማድረግ ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ ነው።ስለ መቃሲድ አከፋፈል ና አመዳደብ ልንል የምንችለው በተለያየ የዕይታ መዓዘን ና አንፃር የተቀመጡ ናቸው ማለት ብቻ ነው።

በሀያኛው ክ/ዘመን የተለያዩ ዑለማዎች ያነሳቸው መቃሲድን የተመለከቱ ሀሣቦችን እና በከፊል የጠቀስናቸው ነጥቦች የሚያስረዱን መቃሲደ ሸሪዓ (የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች) አንድ ዓሊም በሚያደርገው ምርምር ና የእስልምና ግንዛቤ ላይ ተሃድ ስለማምጣት በሚያደርገው ጥረት የሚደርስባቸው ዕይታዎች ናቸው ።

ይህግን የሚሆነው ሃሣቦች ከቁርዓንና ከሀዲስ የተቀዱ ሲሆኑ ብቻ ነው ። አወንታዊ የሆኑ ዘመናዊ ፍላጎቶችን ከቁርዓን ና ከሀዲስ ጋር ለማጣጣም በሚደረገው ጥረት ለመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ ትልቅ ቦታ እንዲሰጠዉ አድርጓል።




## <u>**አልመቃሲድ አሸርዒያ(የሸሪዓ መዳረሻ ግቦች)በሶሃቦች ረ.ዐ. እይታ**</u>

በሶሃቦች ዘመን በመቃሲድ ዙርያ የነበረው ምርምር የተለያዩ ታሪካዊ ክስተቶች ስንመለከት ከቁርዓንና ከሃዲስ ትዕዛዛት ጀርባ ያለውን ጥበብ ማግኘትና ዓላማውና ግቡ ምን እንደሆነ መመርመር የተጀመረው በሰሃቦች ዘመን ነው ሆኖ

እናገኛዋለን። ለዚህ ትልቅ ማሣያ ተደርጎ የሚነሳው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሰሃቦቻቸውን የአስር ሶላትንን በኒ ቁረይዛ እንጂ እንዳትሰግዱ ብለው ትዕዛዝ ያስተላለፉበት ሀዲስ ነው።ነገር ግን ሶሃቦች በኒ ቁረይዛ ሳይደርሱ የአስር ሰላት ወቀት ሊያልፍ በመቃረቡ ሰሃባዎች በሁለት ተከፈሉ። ከፊሉ በኒቁረይዛ ነው የምንሰግደው ሲል ከፊሉ ደግሞ የሰላቱ ወቀት ሳያልፍ ባለንበት መስገድ አለብን በማለት በደረሱበት ሰግደው ነበር።

የመጀመሪያው ቡድን የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.)ትዕዛዝ ግልፅ ስለሆነ በኑ ቁረይዛ ነው መስገድ ያለብን የሚል መከራከሪያ ሲያቀርቡ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ.)በኒ ቁረይዛ አስርን እንድንሰግድ ሲያዙን ሃሳባቸው በፍጥነት ድረሱ ማለታቸው ነው እንጂ የአስር ሰላትን ማንጎደድ አይደለም በማለት የመከራከሪያ ሃሳብ አቅርባል ። የሃዲሱ ዘጋቢ እንደሚገልፀው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.)ሁለቱንም ቡድን ሳይወቅሱ ዝምታን ነው የመረጡት ይላል ። የፊቅህ ሊይቃውንት እንደሚሉት የነብዩ ዝምታ የሁለቱንም ቡድን ሃሳብ ትክክል መሆኑን የሚያፀድቅ ነው።

የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ.) ትዕዛዝን በደፈናው ከመረዳት ይልቅ ከጀርባው ያለውን ጥበብና፤ ግብ መገንዘብ መሆን እንዳለበት የሚያሳየን ሌላው ክስተት በኡመር ቢንሀጣብ( ረ.ዐ.) የኺላፋ ዘመን የጠፍ መሬትን በተመለከተ የተከተሉት አካሄድ ነው። ይህ ክስተት ሀሊፋው ኡመር ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ሰፋ ያለ ውይይት ከሰሀቦች ጋር ያካሄዱ እንደነበር፡ውሣኔያቸው በምርምር (ኢጅቲሃድ) ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያሳያል። የጠፍ መሬቱን ክስተት ምክንያት ስንመለከት ሰሀቦች ሀሊፋው ዑመርን(ረ.ዐ.) በግብፅና በኢራቅ ያሉ መሬቶችን ከድል ማግስት እንዲያከፋፍላቸው ጠይቀው ነበር። ሰሃቦች የተማረኩ ንብረቶችን ለዘማቾች መከፋፈል እንዳለበት የሚያስረዳውን ግልጽ የሆነውን የቁርዐን አንቀጽ ጠቅሰው ቢጠይቁም ሀሊፋው ዑመር ግን በግብጽና በኢራቅ ከተሞችና ቀጠናዎች ያሉ መሬቶችን ሙሉ በሙሉ ለማከፋፈል አልፈቀዱም፡፡ ዑመር (ረ.ዐ.) ይህን ሲያደርጉ የምርኮ ገንዘብን ለምን አላማ እንደሚከፋፈልና በዚህ ጉዳይ ጠቅለል ያለ መልዕት ያዘለው ሌላው የቁርዐን አንቀጽ እንደመረጃ በመውሰድ ነበር፡፡

قال تعالى: ﴿ **كي لا يكون دولة بين الأغنياء** منكم ﴾ [الحشر/7]

**"ከእናንተ ውስጥ፡በሀብታሞቹ፡መካከል፡( ብቻ ሀብቱ)ተዘዋዋሪ፡እንዳይሆን"**

ይህ ማለት ባለ ሀብቶቹ ገንዘብና ንብረትን በብቸኝነት እንዳያግበሰብሱ ማለት ነው፡፡ከዚህ የምንረዳው ኡመር (ረ.ዐ.)ከሳቸው ጋር ተመሳሳይ አከም ያላቸው ሰሃባች ምርኮ መከፋፈልን በተመለከተ የሚጠቀሱ የቀርአን አንቀጽየተረዱት ሊያረጋግጡት ከሚፈልጉት አላማና ግብ አንጻር ነው እንጂ በደፈናው አልነበረም፡፡ የእነዚህ አንቀጾች መዳረሻግብ በድሃና በሃብታም መሃከል ያለው የኑሮ ደረጃ ክፍተት ማጥበብ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ሊያስጨብጠን የሚችለው ሌላው ምሳሌ ዑመር (ረ.ዐ.) ድርቅ በተከሰተበት ግዜ ቁርዓን የሚያዘውን ቅጣት በሌቦች ላይ አለመፈጸማቸው ነዉ። ምክንያቱም ሠው እራሱን በረሃብ ከመሞት ለመታደግ የፈጸመውን ወንጀል በቅጣት ማስተካከል መሞከር የሸሪዓ ዋና ግብ ከሆነው ፍትህ ጋር የማይጣጣም ስለሆነ ፎሊፋው ዑመር (ረ.ዐ.) ቅጣትን ተግባራዊ ለማድረግ ብቻ ብሎ ታላቁን የፍትህ መርህ መጣስ አልፈለገም ።

ሦስተኛው ምሳሌ "አንድ ወታደር የማረከውን የጠላት ንብረት ይወስዳል" የሚለውን ሃዲስ ኡመር (ረ.ዐ.) ተግባራዊ ያደረጉበት መንገድ ነው፡፡ ፎሊፉው ኡመር ወታደሩ የማረከው ንብረት መጠን ብዙ ከሆነ 1/5 ብቻ ይሰጠው ነበር ፡፡ ይህን ያደርጉት የነበረው በወታደሩ መሃከል ፍትሃዊ ክፍፍል እንዲኖርና የኡማውን የጋራ ሀብት ለማበልጸግ በማሰብ ነዉ ፡፡

አምስተኛው ምሳሌ ዑመር(ረ.ዐ.) ሰጋር ፈረሶችን ዘካግዴታ ከሚሆንባቸው የእንሰሳት ሃብት ማካተታቸው ነው፡፡ በርግጥ ነብዩ( ሰ.ዐ.ወ.) ፈረስን ከዘካ ገንዘብ ጋር አላካተቱም፡፡ በዑመር (ረ.ዐ.)የፎሊፉነት ዘመን የሰጋር ፈረስ ዋጋ ከግመል ዋጋ በመብለጡ ከፍተኛ የሃብትምንጭ በመሆኑ ከዘካ ገንዘቦች አካተውታል፡፡ ኡመር ይህን ሲያደርጉ ዘካ የተደነገገበትን ዋና ግብና ጥበብ በመረዳት ነው፡፡ ዋናዉ የዘካ ግብ ማኀበራዊ ትብብርን ማረጋገጥ ሆኖ ሳለ ሠዎች በደፈናው ተግባራዊ የሚያደርጉት ዘካን በተመለከተ የተዘገቡ ሀዲሶችን ቃል በቃል ነዉ ፡፡

እነዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ከሃነፊ መዝሀብ ዉጭ ያሉት ሁሉም የፊቂህ መዝሀቦች ዘካ ግዴታ የሚሆንባቸው የገንዘብ ዓይነቶች ዉስጥ ሀዲስ ላይ ከተጠቀሰው ውጪ ማካተትን ተቃውመዋል፡፡ይህም የሚያመለክተን በዘልማዱ የፊቅህ አረዳድ ዘንድ ነገሮችን በደፈናው ቃል በቃል የመረዳት አባዜ እንዳለ ነው ፡፡ለምሳሌ የኢብን ሃዝም አዛሂሪን ንግግር ብንመለከት እንዲህ ይላል፡ “ዘካ ግዴታ የሚሆነው ከስምንት የገንዘብ አይነቶች ብቻ ነው፡፡ እነርሱም ፡- ወርቅ፣ ብር፣ስንዴ፣ገብስ፣ተምር፣ግመል፣ከብት ፣በግና ፍየል ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉ ፍራፍሬም ሆኑ ሰብሎች ፈረስም ይሁን ባሪያ ማርም ይሁን የንግድ ሸቀጥ ዘካ መስጠት ግዴታ አይደለም ” ይህ የኢብን ሀዝም ንግግር ትልቅ ማህበራዊ ጥቅም የሚሠጠውን የዘካ ሥርአት ምን ይህል እንደሚጎዳ መገመት ቀልል ከመሆኑ ባሻገር የዘካ ዋና አላማ የሆነው ማህበራዊ ፍትህን ፤ መደጋገፍን እንደሚያደናቅፍ ግልጽነው፡፡ የዘመናችን ዕውቁ አሊም ዶ/ር ዩሱፍ አልቃርዳዊ ይህን መሰል አካሄድ በጥብቅ ይቃወማሉ፡፡(ፊቂህ አዘካህ)በሚባለው የተዋጣለት መጽሐፉቸው “ማንኛውም የሚፋፋ ገንዘብ ዘካ ይመለከተዋል ”

ዘካ የተደነገገው የደሃዎችን ፤ በእዳ የተያዙ ሠዎች፤ የመንገደኞችን ፍላጎት፡ ለሟሟላት፤እንደ ጀሀድ ያሉ የሙስሊሙን አጠቃላይ ጥቅም ለማሣለጥ ነው እንጂ አላህ (ሰ.ወ. )ዘካን ግዴታ ሲያደርግ ከ5 ግመል ከ40 ፍየል ከአምስት ዳዉላ እህል የማይበልጥ ያለዉ ሰዉ ላይ ዕዳ ጥሎ እንዱስትሪ ፤ግዙፍ ህንጻ ያላቸው ግለሰቦች፤ከፍተኛ ደመወዝ ያላቸውን ተቀጣሪ ባለሙያዎችን ነጻ ለማዉጣት አይደለም ።

ይህ የዘረዘርነው በቂ የሆነ ምሳሌ የመቃሲድን ዕድገት ፍንትው አድርጎ ያሳየናል። መቃሲድን የማይለዋወጡ መሠረታዊ ህጎች ጋር መመደብ ምን ማለት እንደሆነ ተረድተናል። ነገር ግን ትኩረት ሊሠጠው የሚገባው ነገር የመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ ላይ ተመርኩዞ ሁሉም የሸሪዓ ህግጋት ላይ ብይን መስጠት በተለይ ከአምልኮ ስርዐት ላይ ተግባዊ ማድረግ ተገቢ አይደለም ። ይህን ለመረዳት ያህል ቡኻሪ የዘገቡት የዑመር (ረ.ዐ.) በ፹ሊፋ ዘመናቸው የተናገሩትን ማንሳት ተገቢ ነው።

" فيم الرملان والكشف عن المناكب وقد أعز الله الإسلام ونفى الكفر وأهله "

**“(ጠዋፍ)ስናደርግ ለምን መፍጠንና ትከሻ መግለጽን ያስፈልጋል ? ኢስላም ኃያልነቱን አግኝ[?] ክህደትና ባለቤቶቹ ጠፍተዋል”**

ዑመር (ረ.ዐ.)እዚህ በዚህ ንግግራቸዉ መጥቀስ የፈለጉት ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ና ባልደረቦቻቸውን መካ ለሀጅ ሲገቡ የመካ ቁረይሾች የመዲና ወባ ሰውነታቸው አድክሞአቸዋል የሚል አሉባልታ ነዝተው ስለነበር ለዚሁ አሉባልታ ላለመበገር ሱሃቦችን በጠዋፍ ግዜ በፍጥነት፡እንዲይያደርጉ፤ትከሻቸውን በመግለጽ ጥንካሬአቸውን (ጡንቻቸውን)እንዲያሳዩ ነበር። ይህ ትዕዛዝ የተላለፈበት ግዜያዊ ምክንያት እየታወቀ ፪ሊፋው ዑመር

**" ولا ندعو شيئا كنا نفعله على عهد رسول الله "**

**“በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ግዜ ስንሰራ የነበረው ግን አንተውም”**

በማለት በስርዓተ አምልኮና በምድራዊ እንቅስቃሴዎች መሃከል ያለውን ልዩነት ፪ሊፋዉ ኡመር በዚሁ መልኩ አስረድተዋል።

ኢማሙ ሻጢቢይ በሁለቱ ማሃከል ያለውን ልዩነት እንዲህ በማለት ገልጸውታል። “አምልኮን በተመለከተ ፍፁም ታዛዥነት መሠረቱ ሲሆን የታዘዝነውን ለመፈጸም ምርምር ይሁን አስተያየት ቦታ የለውም ። ምድራዊ ነገር ከሆነ ግን ለምርምር ክፍት ሲሆን፡ግልጽ የሆነ ክልከላ ካልተገኘ ሁሉም ነገር የተፈቀደ ነው”

ከዚህ በመነሳት ማንኛው የአምልኮ ስርአት በሚና የማይቀያየር ነው። ፡ ስንፈጽመውም ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ.) በፈጸሙት መንገድ መሆን ይገባል። በምድራዊ እንቅስቃሴአችን ግን ሙሉ በሙሉ መከተል ሣይጠበቅብን መቃሲደሸሪዓን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት፡፡

## <u>ስለመቃሲድ በመጀመሪያው ግዜ የነበሩ ዕይታዎች (ንድፈ ሃሣቦች)</u>

የመቃሲድ ንድፈ ሃሳብ ከሡሃቦች ግዜ ጀምሮ የነበረ ሲሆን አሁን የምናውቀውን ቅርጽ የያዘው የኃለኞቹ የሸሪዓ ህግጋት ሊቆች ከመጡ በኃላ ነበር ፡፡ ይህ ማለት ከአምስተኛው እስከ ስምንተኛው የሂጅራ ክ/ዘመን ሊቆች ያካትታል በመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ክፍለ ዘመን መቃሲድ ሌላ ስያሚ ይዞ የቀየ ሲሆን ሂክማ(ጥበብ)፤ኢለል (ምክንያት)፤ ሙናሰባት (አጋጣሚ መነሻ)፤

አግራድ(ዓላማ)፤መዓኒ(ትርጉም)በማለት ይጠሩትነበር። ሊቆኡ ይህን ተግባራዊ ሲያደርጉ የተለያዩ ስልቶች ይጠቀማሉ። ለምሳሌ (ቂያስ)ማነጻጸር፤ (ኢስቲህሳን)ይሁንታ፤(መስላሃ)ጥቅምን ማስቀደም የሚባሉ ስልቶችን ይጠቀሙ ነበር ። እስከ ሶስተኛው ክ/ዘመን መቃሲደሸሪዓ እራሱን ችሎ እንደርዕስና የጥናትና ምርምር ዘርፍ ሆኖ ብቅ አላለም ። ከዚያ በመቀጠል ግን (ደረጃትአደሩሪያት)የአስፈላጊ ነገሮች ደረጃዎች የሚል እይታ (ንድፍ ሃሳብ) አልኢማም አልጁወይኒ (478ሂ/1085ዓል የሞተ)ይዘው ብቅ አሉ ይህ የሆነው በአምስተኛ ክ/ዘመን ነበር ።

ከሦስተኛ እስከ አምስተኛው ክፍል ዘመን ያለውን የመቃሲድ አሸሪአ ንድፍ ሃሳብ ዕድገት በአጭሩእንመልከት።

1-አትርሚዚይ አልሃኪም (296ሂ/9089ልየሞቱ)አቲርሚዚይ አልሃኪም (አሰላትወመቃሲድ)ሰላትና መዳረሻ ግቡ በሚል ርዕስ የጻፉት መጽሐፋቸዉ መቃሲድ የሚለዉ ቃል በርዕሱ ላይ የተጠቀሰ ሲሆን በመቃሲድ ዘርፍ የተጻፈ የመጀመሪያ መጽሐፍ ተደርጎ ይወሰዳል። በዚህ መጽሐፉቸው ከሰላት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ጀርባ ያለውን መንፈሳዊ ጥበብና ሚስጥር ተንትነውበታል ።ሰጋጁ ጌታ ፊት ሊቆም ከሸሸት ፤ ወደ ቂብላ አቅጣጫ ሲዞር ከማፈንገጥ፤ሊያወድስ ከመዘንጋት፤ ሲያጎነብስ ከድርቀት ፤ በግንባሩ ሲደፉ ከሀጢያት ነጻ ይሆናል። እያሉ ይተንትናሉ ቲርምዚ በዚህ መንገድ የተጻፉ ስለሀጅ ጥበብና ሚስጥር የሚናገር መጽሀፍ አላቸው።

2-አቡ ዘይድ አልበልኺይ(322ሂ/933ዓ.ልየሞተ)

አቡዘይድ አልበልኺይ(አልኢባና ዐንኢለሊ አዲያናህ) (ሃይማኖታዊ ድንጋጌ ምክንያት ማብራራት ) የሚል መጽሀፍ ጽፈዋል። ይህ መጽሀፉቸው በምድራዊ እንቅስቃሴ (ሙዐመላት) በተመለከተ የተጻፈ የመጀመሪያ የመቃሲድ መጽሀፍ ተደርጎ ይወሰዳል። በዚህ መጽሐፍ የሸሪዓ ድንጋጌዎች ዒላማ የሚያደርጉትን ግቦች አብራርተዋል። አልበልኺይ(መሣሊሃል አብዳን ወኑፋስ )(የሥጋና የነፍስጥቅም) የሚል መጽሐፍ ያዘጋጀ ሲሆን በዚህ መጽሐፉ ኢስላማዊ ግብረገብነትና ኢስላማዊ ድንጋጌዎች በሰው ልጅ አካላዊና መንፈሳዊ ጤና ላይ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳላቸው አብራርቷል ።

3-አልቀፋል አልከቢር አሻሲይ (365ሂ/975ዓ.ል.የሞተ)

በግብጽ የቤተ መጻህፍት ውስጥ ካገኘኋቸው የመቃሲድን ርዕስ ከሚተነተኑ ማኖስክሪፐቶች ቀደምቱ የቀፋል(መሃሲን አሸሪዓ)የሚለው መጽሐፍ ነው። ይህ በእጅ የተጻፈ ማኖስክሪብት ሀያ ገፅ የሚፈጅ መግቢያ ሲኖረው በተለመደው መልኩ በምዕራፍ የተከፋፈለ ነው። የጦሃራ ምዕራፍ፣ ውዱእ፣ ሰላት እያለ እስከመጨረሻው በዘልማዳዊ የምዕራፍ አወቃቅር ይቀጥላል።ስል ድንጋጌዉ በአጭሩ ከተናገረ በኃላ ከድንጋጌዉ ጀርባ ያለውን ጥበብና ግብ በስፋት ያብራራል። የዕጅ ጽሑፉ (ማኖስክርፒቱ) በግል የሚታይ ሲሆን 400ገጽ ያለውና በመጨረሻው ገጽላይ ረቢኢልአወል ወር 11ኛቀን 358ዓ.ሂ(969ዓ.ል.በጀንዋሪ) እንደተጠናቀ ተጽፏል። መጽሐፉ ሰፋ ያሉ የፊቅህ ርዕሶችን የሚዳስስ ሲሆን እያንዳንዱን ርዕሥ በተናጥል የሚነሳ ቢሆንም ሁሉንም ርዕሶች ከመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ አያይዞ አይተነትነዉም ፡ ይህ መጽሀፍ ካለበት ዉስንነት ጋር ትልቁ አስተዋጾኦ አበርክዃል።

አብዱ ናስር አስጋኒ የተባሉ ዓሊም የአልቀፋልን መሀሲንአሸሪዐ በተሰኘዉን ማኖስክርቢት ዙርያ ጥናትና ምርምር አድርገው፡የአርትዖት ስራ የሰሩበት ሲሆን ለዶክትሬት ትምህርታቸው በ2004 በእንግሊዝ ለሚገኘው የዊልዝ ዩንሃርስቲ መመረቂያ ጽሑፍ አርገው አቅርበውታል። በዚህ የዶክትሬት ጽሑፍ ሱፐር ⎫ይዘር የነበሩት መውኢል ኢዘዲንስለማንስክርቢቱ የሚከተለውን ብለዋል። “እንደ አልቀፋል አልሻሺ ምልከታ የሸሪዓዊ ትዕዛዞች አስፈላጊነት በመልዕክቱ ላይ የተመሰረተ ነው፡ለምሳሌ የአልኮልን እርምነት ብንመለከት ሰይጣን መጠጥን ተጠቅሞ ጥላቻንና ጠብን በሰዎች መሀከ ፡እንደሚስፋፉ፡ሸሪዓው ተናግራል፤ አላህን ከማውሳት፡ከጸሎት፡ይከለክላል ”

በዚህ መልኩ አሻሺ (መልዕክት)ና፡(ምክንያት)ን የሸሪዓን ግብ ለመረዳት ስልት አድርጎ ማቅረቡ የመቃሲድ ንድፍ ሃሣብን በማለዳ ከተነተኑ፡ሠዎች ያደርገዋል። ይህ አካሄድ በአጠቃላይ ቀፋል አሻሺ የሚከተለዉ የሻፊኢ መዝሀብ መንገድ መሆኑ ቢታወቅም አሻሺ ያስቀመጣቸዉ አዳዲስ ግንዛቤዎችን ከእርሱ በኃላ ለመጡት አልጀወይኒና አዘሃቢ መንገድ ጠርጎላቸዋል።

4- ኢብን ባቡያህ አልቁሚይ(381ሂ/991ዓ.ል.የሞተ)

የመቃሲደሽሪዓ የውቀት ዘርፍ ምርምር የሚያደርጉ አንዳንድ ግለሰቦች ይሄ ዕውቀት በሱናው አለም ብቻ ያለ ይመስላቸዋል።በዚህ ሃሳብ በተቃራኒ በአራተኛው የሂጅሪ ክ/ዘመን በመቃሲድ ዙሪያ የተጻፈ የኢብንባቡያህ አልቁሚይ የተሟላ ምርመር እናገኛለን። ይህ ሸህ ታላቅ የሽሪዐ ሊቅ ሲሆን እስከ 335 የሚደርስ ርዕስ በመቃሲድ ዙሪያ ፅፈዋል፡(ኢለሉሽሪዓ)(የሽሪዓ ምክንያታዊነት) የሚለው መጽሐፋቸው በአላህ በነብያት፤ በሩቅ ነገር(ገይብ) እምነት፡ዙሪያ፡ በአመንኪዮ በማስገደፍ ይተነትናሉ። ከሰላት፣ከጾም፣ከሀጅና ከስደትበስተጀርባ ያለውን ሚስጢርና ጥበብ በስፋት ተንትነዋል።

5-አልአሚሪ አልፈይለሱፊ(381ሂ/991ዓ.ል.የሞተ)

የአልአሚሪ የመቃሲድሽሪዓን በንድፍ ሃሣብ ደረጃ  ለመጀመሪያ ግዜ ያነሳ መጽሀፍ የጻፈ አሊም ሲሆን (አልአዕላም ፊመናቂብ አልኢስላም)በሚል ርዕስ መጽሐፍ አዘጋጅቷል ፡በዚህ መጽሐፉ ላይ የነፍስ ማጥፋትን ወንጀል፤ ገንዘብ የመንጠቅ ወንጀል፤ ሰውን ማጋለጥ (ቅሌት ላይ የመጣል )ወንጀል፤ ክብር የማጉደፍወንጀል፤ ሃይማኖትን የመተው ወንጀል፡የመሣሰሉት ርእሶችን ከቅጣት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች  በስፋት ትኩረት በመስጠት ተንትኗል።

አምስተኛ ክ/ዘመን ድረስ የመቃሲድ ዕውቀት ዘርፍ (ደሩሪያት)አስፈላጊና አንገብጋቢ ነገሮችን የማንሣት ደረጃ ላይ አልደረሰም። ይህ የእውቀት ዘርፍ የዕድገት ማማ የደረሰው በ8ኛውየሂጅራ ክ/ዘመን ነው።  ይህ ማለት ግን የ20ኛው ክ/ዘመን ዕድገቱን አያካትትም።

# ምዕራፍ፡ሁለት

## ከአምስተኛው እስከ ስምንተኛው የሂጅራ ክ/ዘመን የነበሩ የመቃሲድ ዕዉቀት ሊቆች

አብደላህ ቢን በያህ "የኢስላም ድንጋጌ ፍልስፍና " ብለው የሚጠሩት የዕውቀት ንቅናቄ በአምስተኛው ክ/ዘመን የተወልደ ሲሆን በአምስተኛው የሂጅራ ክ/ዘመን ሙስሊሙ አለም የደረሰበትን የስልጣኔ ክፍታና እሱን ተከትሎ የመጣው ውስብስብ አዳዲስ ፈጠራዎችና ተግባራት የቀደመው ቃል በቃል በመረዳትና በድፍኑ ፈትዋ የመስጠት ስልት አዋጭ ሆኖ ስላልተገኘ ነዉ ። ይህን አዲስ ፍላጎት ለሃ̄ሃ̄ላት "ሰፊ ጥቅም " (አልመሳሊሀ አልሙርሰላ )የሚባል አዲስ ዕይታ ተፈጠረ፡ በእነዚህ አዲስ በመጡ ፈጠራዎችና እንቅስቃሴዎች ዙሪያ (ፈትዋን ለመስጠት የፊቅህ ሊቅ ከቁርዐንና ከሀዲስ ቀጥተኛ ማስረጃ አይገኝላቸው። ይህ (ሰፊ ጥቅም )የሚለው አዲስ ዕይታ መምጣት በዚህ ረገድ የነበረው ክፍተት መሙላት ችሏል።

ይህን ተከትሎ መቃሲድ አሽሪዓ የሚለው የዕውቀት ዘርፍ እንዲፈጠር አድርጎታል። ይህም የሆነው ከአምስተኛው እስከ ስምንተኛው የሂጅሪክ/ዘመን ሲሆን በዚህ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ካደረጉለት መሀከል አቡልመዓሊ አልጁወይኒ፤ አቡል ሃሚድ አልገዛሊይ፤አልዒዝ ቢን አብዱሰላም፤ሺሃቡዲን አልቂራፊይ፤ሸምሰዲን ኢብንቀይም ይገኙበታል፡የአቡኢስሃ አሻጢቢይ አስተዋጾ ግን በጣም የጎላ ነው፡፡

## አልኢማም አልጀውይኒና የብዙሃን ፍላጎት(አልሃጃትልዓማህ)

አቡል አልመዓሊይአልጀወይኒ፡(478ሂ/1085ዓ.ል.)
አልጁወይኒ (አልቡርሃን ፊኡስልፊቅህ) በሚል ርዕስ የፍላጎቶችን ደረጃ ያብራሩበት መጽሐፍ ጽፈዋል፡በዚህ መጽሐፍ ያነሱት ሃሳብ በዚህ ዘመን ካለው ዕይታ በጣም ተቀራራቢ ነው። አልጁወይኒ አምስት የፍላጎት ደረጃዎችን ያስቀመጡ ሲሆን አንደኛ (በዶሩራት) በጣም አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የገደለ ሰውመግደልን(ቂሷስን) አንስተዋል። ሁለተኛ ደርጃ በአጠቃላይ ፍላጎት ስር ኪራይ እንደ ምሳሌ ጠቅሰዋል።በሶስተኛ ደረጃ ያነሱት ሃሳብ መልካምነት

መላበስና  የመልካምነትን ተቃራኒ  ማስወገድ ሲሆን ንጽህናን ለዚህ ክፍል ምሳሌ አድርገው አቅርበዋል። በአራተኛ ደረጃ ትርፍ ጉዳዮች ሲያነሱ አምስተኛ ደረጃ ላይ በቂ እና ግልጽ ምክንያት፤የታውቀ ግብ የሌለው ነገር በማለት ጠቅሰው በመጨረሻዉ  ክፍል ስር የሚገኙ ነገሮች ኢምንት መሆናቸው አስረግጠዋል።
አልጅወይኒ፡የጻፉት ሌላው (ጊያሱልኡመም)የተሰኘው መጽሐፋቸው  የሸሪዓን ፖለቲካዊ ክፍል በዋናነት የሚተነትን ቢሆንም የመቃሲድ ሸሪዓን  በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውታል ባይነኝ ። አልጅወይኒ እንደ ምሳሌ ሲጠቀሱ ለሽያጭ ግዜ መስማማት ተገቢ መሆን ፤ዘካ የደሃዎችን ፍላጎት ለማሟላት የተደነገገ  መሆኑንና  የመሳሰሉትን  ይጠቅሳሉ።  የአልጅወይኒ ይህ(ጊያስልኡመም)የተባለው  መጽሐፋቸው  የእስልምና  ፊቅህ  ታሃድሶ እንደሚያስፈልገው ፍንትው አድርገው አሳይተዉበታል ።

## 2-አል ኢማም አልገዛሊ (ደሩሪያት ፤ የአስፈላጊ ነገሮች ደረጃ ) አቡ ሃሚድ፡ አልገዛሊ(፡505ሂ/1111ዓ.ል.የሞቱ)

የአልጅወይኒ ተማሪ የሆኑት አቡ ሃሚድ አልገዛሊይ የመምህራቸውን ንድፈ ሃሳብ በማሳደግ (አልሙስተስፉ)በተሰኘው መጽሐፋቸዉ (ደሩርያት)ፍልጎትን ደረጃ እውጥተውታል። ሃይማኖት፣ ህይወት፣አእምሮ፣ዘር(ዝርያ)፣ገንዘብን በማለት ና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ስለ(ደሩሪያት) ሲያብራሩ ፤ (ሂፍዝ)መጠበቅ የሚለው ቃል ለመጀመሪ የተጠቀሙት  አልገዛሊ ናቸው።

 አልገዛሊ ይህን ርዕስ ሲተነትኑ ለመቃሲድ መሠረታዊ ህግን ተከትለው መረጃ ከማቅረብ ይልቅ “ታሳቢ ጥቅም ” (አልመሣሊህ አልመውሁማ) በማለት ነበር የሰየሙት።  አልገዛሊ ይህን ስያሜ የመረጡበት ምክንያት መቃሲድ እንደሌሎቹ የሸሪዓ ርዕሶች ቀጥተኛ የቁርዓንና የሃዲስ መረጃን በማጣቀስ የሚደረስበት ሳይሆን፡በክትትልና በምርምር የሚደረስበት የእዉቀት ነው ብለው በማመናቸው ነው።  አልገዛሊ ይህን ይበሉ እንጂ መቃሲድ (የሸሪዓ መዳረሻ ግብ ) በብዙ ህግች  ዙርያ ብይን ለመስጥት መሠረት አድርገውታል። አልገዛሊ ከጻፉት መሀከል ለምሳሌ ፡ጥቅም(መስለሃ) በሸሪዓ መሰረት ሶስት ዓይናት ነው ብለዋል።
1ኛ ፡ ሸሪዓ ግምት የሰጠውና ተፈቀደው ።
2ኛ ፡ ሸሪዓ ከንቱ መሆኑን (አለመፍቀዱን)ያስቀመጠዉ
3ኛ ፡ሸሪዓ የተፈቀደ ወይም፡የተከለከለ መሆን በግልጽ ያላስቀመጠው ነው።

ሸሪዓ የፈቀደው የምንለው መረጃ ያለውን በእርሱ ትይዩ ተነጻጻሪ የሆነ አሳማኝ ምክንያት (ቂያስ) የሚገኝለት ነው። ለቂያስ ምሳሌ ሲያስቀምጡ እንዲህ ይላሉ፦ “አንድን መጠጥ ወይም ምግብ ክልክል ነው የምንለው አልኮል ጋር በማነጻጸር ነው።አልኮል እርም የተደረገው ለሌላ ነገር ሳይሆን ግዴታ ለመወጣት የሚያስችለንን አእምሮአችን ለመጠበቅ ታስቦ ነው ።በአጠቃላይ ሸሪዓ አምስት የሰው ልጅን አስፈላጊ ነገሮች ለመጠበቅ የመጣ ሲሆን እነርሱም፡ ሃይማኖት ፤ ነፍስ (ህይወት ) አእምሮ ፤ ዘር፤ ገንዘብ ናቸው። እነዚህን አምስት ነገሮች የሚጠብቅ ነገር ሁሉ ጥቅም (መስለሀ)ብለን እንጠረዋለን። እነዚህ አምስት ነገሮች ለጥፋት የሚይጋልጥ ነገር ሁሉ ጉዳት (መፍሠዳህ) ብለን እንጠራዋለን ።

አልገዛሊ ይህን ብቻ ሳይሆን እነዚህ ዶሩሪያት (አስፈላጊ)ነገሮች ደረጃ፡ የሚያስቀምጥ አጠቃላይ ህግ (ቃኢዳ) አስቀምጠዋል። ይህ ህግ ሁለቱ አስፈላጊ ነገሮች ምርጫ በማይሰጥ መልኩ አንድ ላይ ቢከሰቱ በዚህ የደረጃ ሰንሰለት መሰረት ለነገሮች ቅደም ተከተል ለመስጠት ዕድል ይሰጣል።

## ኢዘዲን ቢን አብዱ ሰላም (ከሸሪዓ ህግች ጀርባ ያለው ጥበብ) (660ሂ/1209ዓ.ል.የሞተ)

ይህ ሊቅ ሁለት በመቃሲድ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁለት አጫጭር መጽሐፎችን ደርሠዋል። ሁለቱ መፅሀፎች ትኩረት የሚያደርጉት ከህጎች ጀርባ ያሉ ጥበቦች ላይ ሲሆን እርዕሳቸውም (መቃሲደሰላት)የሰላት ግብና፤ (መቃሲድሶም)የጾም ግብ በማለት ሰይመዋቸዋል። (ቀዋኢድ አልአህካም ፊመሣሊህ አልአናም) ብለው የጠሩት ሦስተኛው መጽሐፋቸው የመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ ዕድገት ላይ ትልቅ አሻራውን አሳርፏል። ኢዘዲን ቢን አብደሰላም በእነዚህ መጽሐፎች ውስጥ መሳሊህና መፋሲድን ማለትም ጥቅምና ጥፋትን ከመተንተናቸው ባሻገር የሸሪዓ ድንጋጌዎች ዓላማ የሚያደርጉትን ግብ፤ ከጀርባቸው ካሉ ጥበቦች ጋር አስተላልፈዋል። ለምሳሌ ለማንሳት ያህል እንዲህ ብለው ጽፈዋል “የሸሪዓ ድንጋጌ ጥቅምን ለማረጋገጥ ፤ጥፋትን ለማስቀረት ግብ አድርጎ መንቀሳቀስን የተረዳ ሠው(ነስ) ግልጽ የሆነ መረጃ፤ (ኢጅማእ) የዑልማ ስምምነት፤ (ቂያስ) የንጽጽር መረጃ በያገኝም ጥቅምን ችላ ማለትና ጥፋትን መቅረብ አግባብ አለመሆን ግንዛቤ ና ዕዉቅት ያገኛል።

## አልኢማም አልቂራፊና የነብዩ እንቅስቃሴዎች (ተሰሩፋት)ወይም ተግባራት(684ሂ/1285ዓ.ል.የሞተ)

የሺሃቡዲን አልቅራፊ በመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ ያደረገው አስተዋጽኦ የነብዩ( ሰ.ዐ.ወ.)የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ናተግባራት ከነብዩ( ሰ.ዐ.ወ.)ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ነጣጥሎ ማየቱነው። ይህ የአልቂራፊ ግንዛቤ ና ለመቃሲድ ያለው አመለካከት በአሁን ዘመን ካለው ጋር ተመሳሳይ ሁኖ እናገኘዋለን ። ሺሀቡዲን አልቂራፉ “አልፉሩቅ” በተሰኘው መጽሐፋቸው ተከታዩን ጽፏል።

“ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈታዋ ሲሰጡ ያለዉን ሁኔታና የፍርድ ብይን ሲያስቀምጡ ያለዉን ሁኔታና ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። የኢማምነትን ተልዕኮ ማድረስ ሚና ሲወጡና ሌላ ተግባራትን ሲፈጽሙ በሸሪዓ ድንጋጌ ላይ የሚኖረው ውጤት የተለያየ ነው። ተልዕኮ ለማድረስ የተናገሩት ወይም የሰሩት ተግባር አጠቃላይ ህግ ሲሆን ሌላው ተግባራቸው ማለትም ሠራዊት ማሰማራት፤ገንዘብ ማሰራጨት፤ የምርኮ ገንዘብ ማከፋፈል፤ ዳኛና ገዢዎችን መሾም፤ ስምምነት መፈራረም እንደ መሪ የሚፈጸሙት ተግባር ነው።”

ቂራፊ በዚህ መልኩ የነብዩ ተግባራትን ከፍላጎታቸው ጋር በማስተሳሰር የመቃሲድን ግንዛቤ ማስፋፋት ችለዋል ። ኢብን አሸርም ይህን የአልቂራፊን ሃሣብ በመውሰድ የመቃሲድ ትርጉም አድርጎ ወስዶታል። አልቂራፊ የመቃሲድን ግንዛቤ ጥቅምን ለማረጋገጥ መንገዶችን መክፈት የሚል ሌላ ሀሳብ አንስቯል። ይህ ሃሳብ ሲያነሳ ወደ ጥፋት የሚወስዱ መንገዶችን መዝጋት እንደሚገባ ሁሉ ወደ ጥቅም የሚያደርሱ መነገዶች መከፈት ተገቢ ነው በማለት በአሉታዊው (መንገድን መዝጋት) በሚለው ሀሳብ ብቻ እራሱን አላጠረም።

## አል ኢማም ኢብን አልቀይምና የሸሪዓ ዕውነታዎች አልኢማም፡ኢብን አልቀይም(748ሂ/1347 ዓ.ል.የሞተ)

የሸህ አልኢስላም አህመድ ቢንተይሚያ ተማሪ የሆኑት ኢብን ቀይም በመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍን በማበልፀግ በመጀመሪያ ደረጃ ያደረጉት አስተዋጽኦ (አልሂየልአልፊቅህያ) የፊቂህ ዘዴዎች ብለው በሰየሙት ሂሳዊ ጥናታቸው ላይፍንትው ብሎ ይታያል። በጥናታቸው እነዚህ ዘዴዎች ከመቃሲድ ጋር ያላቸውን ተቃርኖ ጠቅሰው ለአብነት ያህል ከጠቅሱት እንደ ወለድ(አራጣ)፣

ጉቦ የመሳሰሉት እርም ነገሮች በዘዴ ሸሪአዊ ቅርጽ በመስጠት ንግድና ስጦታ እንዲመስሉ በማድረግ ማቅረብ ነው። ኢብን ቀይም ይህን ሃሳብ የበለጠ ለማብራራት እንዲህ ብለው ጽፈዋል ።

“ዘዴዎችን መጠቀም እርምና ከንቱ መሆኑን ማረጋገጫው አላህ (ሱ.ወ.)ነገሮች እርም ሲያደርግ የባሪያዎቹን በምድራዊና በሰማያዊ ዓለም ያላቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ነው። ይሁንና በዘዴ አላህ አርም ያደረገው ሀላል ለማድረግ መሞከር የአምላክን ትዕዛዝ መጣስና ህጉን ውድቅ ከማድረግ ባሻገር በተለያዩ መንገድ ወደ ጥፋት መ`ዐ`ዝ ነው። የመጀመሪያው ጥፋት ከክልከላው ጀርባ ያለውን ጥበብ ና ኣላማ ውድቅ ማድረግ ማለት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዘዴ ልናገኘው የፈለግ ነውን ተግባር በእርሱ እውነታ ወይም ግብ ሳይሆን ዋናው ተፈላጊው ነገር እርም የተደረገው ተግባር ነው።

ምግብ ለሰውነታችን እንደሚያስፈልገን ሁሉ ሸሪዓ ደግሞ ለልባችን ቀለብ ነው። ይህ የሚሆነው የሸሪዓን እውነታ በመያዝ እንጂ ዉጫዊ ገፅታን በመላበስ ብቻ አይደለም፡፡ ”

ኢብን ቀይም የፊቂህ ግምገማዎችን ያስቀመጡት “፡ከህጎች ጀርባ ያለዉን ጥበብና፡ የሰውልጅ ጥቅም” መሠረት በማድረግ ነው። ይህን በቀጣይ ካለዉ ጠንከር ያለ ንግግራቸው እንረዳለን። “የሸሪዓ ድንጋጌ መሰረት የሚያደርገው ከጀርባ ያለውን ጥበብና የአላህ ባሪያዎችን ጥቅም ነው። ሸሪዓ ሙሉ በሙሉ ፍትህ፣እዝነት፣ጥበብ፣ጥቅም ነው፤ ማንኛውም ከፍትህ ወደ በደል ያዘነበለ፤ ከእዝነት ወደ ጭካኔ ያጋደለ፣ከጥቅም ወደ ጥፋት የተጠጋ፣ከጥበብ ወደ ቧልት የወጣ ነገር ሁሉ በአተረ`ዐ`ጎም ለማስተካከል ቢሞከርም የሸሪዓ አካል አይሆንም።

ይህ ከላይ የጠቀሰው የኢማም ኢብን ቀይም ንግግር የእስልም ሸሪዓዊ ድንጋጌ ለመረዳት የሚያስችል ጠቅላይ ህግ ነዉ ማለት ይቻላል። በዚህ የኢብን ቀይም ጥቅስ ውስጥ መቃሲድ መሰረታዊ ነገር ሆኖ ና ትክክለኛ ቦታውን ይዞ እናገኘዋለን። ይህንኑም ሀሣብና ግንዛቤ ግልጽ በሆነ አነጋገር ኢማሙ አሻጢቢ ያረጋግጡታል።

# <u>አልኢማም አሻጥቢይ መቃሲድ የሸሪዓ መሠረታዊ ጉዳይ</u>
# <u>(790ሂ/1388ዓ.ል.የሞተ)</u>

አቡ ኢስሃቅ አሻጥቢይ መቃሲድን ሲተነትኑ የተጠቀሙት ቃላትና ማብራሪያዎች የኢማም አልጅወይኒና የተማሪዋውን አልገዛሊ አገላለጽ ጋር ተመሳሳይ ናቸው ። ኢማሙ አሻጥቢይ ግን (አልሙዋፈቃት )በተሰኘው መጽሐፍ መቃሲድ ወደ ፊት ሦስት እርምጃ ያራመዱ ነጥቦችን አንስተዋል።

## 1-ከልቅ ጥቅም (መሳሊህ ሙርሰላ)ወደ መሰረታዊ ህግ (ኡሱሉ ሸሪዓ)

አሻጥቢይ ሙዋፈቃት የተሰኘውን መጽሀፋቸው ከማበርከታቸዉ በፊት መቃሲድ የልቅ ጥቅም (የመሳሊህል ሙርሰላ) አካል ተደርጎ ይቆጠር ነበር። ከመፅሀፉ በፊት መቃሲድ ግንዛቤ መሠረታዊ ሁኖ እንዳይወሰድ አድርጎታል። አሻጥቢይ ግን መዋፈቃት የሚባለው መጽሐፋቸው ላይ ስለመቃሲድ የሚናገሩበትን ክፍል ሲጀምሩ የጠቀሱት የቁርዓን አናቅጽት አላህ ፍጥረቱን ሲፈጥር፤ ነብያትን ሲልክ፤ ሸሪዓ ህግን ሲያስቀምጥ፤በዘፈቀደ ሳይሆን ፤ለትልቅ ዓላማ መሆኑ የሚያሳዩ አንቀጾችን ነው። በዚሁ የመጽሐፍ ክፍል መቃሲድን የእስልምና ሃይማኖት መሰረት፤ የሸሪዓ መሰረታዊ ህግና የሃይማኖቶች ጠቅላይ ህግ ነው ብለውታል ።

## 2- ከድንጋጌ ጀርባ ካለው ጥበብ ወደ ድንጋጌ መሰረት

አሻጥቢ ለመቃሲድና ለጠቅላይነቱ ቅድሚያ መሰጠት ተገቢ እንደሆነ ሲጠቅስ እንደደሩሪያት (አንገብጋቢ ነገሮች) ያሉ ጠቅላይ ህጎች (ኩልያት) ላይ ዘርፍ የሆኑ ህጎች (ጁዝዕያት)ገዚ መሆን እንደማይችሉ አጽንኦት ለመስጠት ነዉ። ይህ የሸጥቢይ ሃሳብ ትልቅ ተራማጅነት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ይህን ሃሳብ ሻጥቢይ ያራመደው የሚከተለውን መዝሃበል ማሊኪይ አመለካከት ተቃራኒ ሁኖ ነዉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ሻጥቢይ የመቃሲድን የዕውቀት ዘርፍ ጠንቅቆ ማወቅ ለማንኛው ደረጃ ለሚገኝ የሸሪዓ ምርምር (ኢጅቲሃድ)እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጠዋል።

## 3-እርግጠኛ ካልሆነ መረጃ (ዞንያ) ወደ እርግጠኛ የሆነ መረጃ (ቀጥኢያ)

ሻጥቢይ ለመቃሲደአሽርኢያ (ለሽሪዐ መዳረሻግቦች)ዕውቀት ዘርፍ ትልቅ ቦታ ለመስጠት ካለው ፍላጎት የተነሳ የመጽሀፉ መግቢያ ላይ በክትትል (እስቲቅራዕ)የሚገኙ ድምዳሜዎች እርግጠኛ ያልሆነ መረጃ መሆኑን የሚያሳይ ና የተንሰራፉ ግንዛቤ ውድቅ ያደርጋል። ይህ ታላቅ ተራማጅነት ተደርጎ የሚወስድአካሄድ ነው። የሻጥቢይ መጽሐፍ በመቃሲድ የዕውቀት ዘርፍ እንደ ዋቢ አድርገው ብዙ የሽሪዓ ሊቆች የሚጠቀሙት ቢሆንም (እስከ20ክ/ዘመን)ድረስ መቃሲድ የሽሪዓ ድንጋጌ መሰረት መሆን አለበት የሚለው ሃሳቡ ግን ብዙም ተቀባይነት አላገኘም።

# ምዕራፍ ሦስት

## በዘመናችን የእስልምናን ተሃድሶ ለማረጋገጥ የመቃሲድ ዕውቀት ሚና

በአሁኑ ግዜ ያሉ እስላማዊ ፊክር(እሳቤ)አራማጆች በእስልምና ሃይማኖት ዉስጥ ተሃድሶና ለውጥ ለማምጣት በሚያደርጉት ጥረት መቃሲድሸሪዓን እንደዋና አማራጭ ይወስዱታል። ይህን ሲባል ግን አንደ አንድ ሚድያዎች በተለይ የምዕራባዊያን ሚድያዎች ኢስላማዊ “ተህድሶ” ብለው የሚያቀርቡትን ሂሣዊ እስተያየት አይመለከትም። ምክንያቱም ይህ ሃሳብ ና አስተያየት ትክክለኛ ተሃድሶ ሳይሆን ሰፊው ሙስሊሙን ማሕበረሰብን፤ ወይም ህዳጣን ሙስሊሞችን፤ከዚያም ሲያልፍ  እስልምናን እነርሱ በሚፈልጉትሁኔታ መቅረጽ ግብ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ነው። ይህ አስትሳስብ የሙስሊሙን ማኅበረሰብን አእምራዊ፤ማኅበራዊ፤ አንዳዴም ፓለቲካዊ ስርዓት እንዳሻው ለመቅረጽ የሚፈልገው ከእስልምና እሩቅ በሆነ ፤የሙስሊሞችን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ነው።

የህግ ማውጣት ፍልስፍና መነሻ የሆነው መቃሲደሸሪዓ ዓለማችንና ህይወትን በትክክል ለመረዳት ግቡ ያደረጋዉ በኢስላማዊ አስተሳሰብና አመንኪዮ የተመሰረተ የዓውቀት ዘርፍ በመሆኑ የኢስላም ትክክለኛው ተሃድሶ ለማረጋገጥ አወንታዊ ሚና ይጫወታል። በቀጣዩ ርዕስ ይሄ እንዴት እንደሆነ በዝርዝር የምንመለከተው ሲሆን ርዕሱን ከተለያየ ማዓዘን እንመለከታለን ።

መጀመሪያ የምንመለከተው ዘመናዊ ኢስላማዊ ፊክር (እሳቤ)በመቃሲድ ዙርያ ያለውን ምልከታ ሲሆን ግብ የሚያደርገው ልማትን፤ ሰብዓዊ መብትን ነው። በሁለተኛ የደረጃ የምናነሳው መቃሲድ ሸሪዓ የኡስሉልፊቅህ ትምህርት ዘርፍ ተፈላጊውን ተሃድሶ እንዲመጣ ዋና ስልት መሆኑን ነው። በተለይ ግብና ምክንያቶች ለይቶ የሚያይ የትምህርት ዘርፍ በመሆኑ ለዚህ ነጥብ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን። በሦስተኛ ደረጃ መንገዶች መክፈት የሚለውን አስተሳሰብ መሠረት አድርጎ የሚነሳውን ይፊቅህ ምርምር (ኢጅቲሃድ)እንመለከታለን። ይህ ነጥብ የተለመደውን መንገድን መዝጋት ለሚለው መሠረታዊ ህግ አማራጭ የሚሆኑ ነው። በአራተኛ ደረጃና በመጨረሻም  መቃሲደሸሪዓ  በሁሉም የእስልምና

መዝሃቦች ወይም በሃይማኖቶቸ መሀከል የጋራ መድረክ በመሆን ያገለግላል የሚለውን ሀሳብ እንመለከታለን ።

## መቃሲድ አሸርኢያ(የሸሪኣ መዳረሻ ግብ )የልማትና የሰብዐዊ ሙብት ፕሮጀክት

የዘመናችን የፊቂሀ ሊቆችና መፈኪሮች(thinkers) በመቃሲድ አሸሪዓ የትምህርት ዘርፍ ውስጥአዲዲስ ከዘመን ጋር የመጡ ቃላቶችን አስገብተዋል። አንድአንድ ሊቆች ዘመናዊ የሚለው ቃል መጠቀም የተቃውሙ ቢሆንም በአጠቃላይ የዘመናችን ሊቆች በዚህ ረገድ ያደረጉትን አስተዋጽኦ እንመለከታለን።

በቀደምት ግዜ የተደረገው የመቃሲደሸሪዓ ምርምር "ዘርን መጠበቅ "አንዱ የአንገብጋቢ ነገሮች (ደሩሪያት) አካል አድርጎ ያስቀምጠዋል። ከዚያ በፊትም አል ዓሚሪይ የተሰኘ ዓሊም ስለ ቅሌት ቅጣት (ሀትክ ሲትር)ተናግሯል። ከእርሱ በኃላ የመጣው አልኢማም እልጅወይኒ ስለ ጥብቅነት ክብር(አልዒስማ) ስለገንዘብና የህይወት ክብር ተንትኗል የብልት ጥብቅነትና ጥብቅነቱን ያልተወጣን ሰው ቅጣቱን በዝርዝር አስቀምጣል። "ዘርን መጠበቅ" የሚለው አባባል ለመጀመሪያ ግዜ የተጠቁሙት ና ከአንገብጋቢ ነገሮች (ደሩርያት)ውስጥ ያስገቡት አልኢማም እልግዛሊ ናቸው፤ሻጥቢይም ቢሆኑ የገዛሊን ሃሳብ በመውሰድ ንዉ ተጨማሪ ማብራሪያ ያደረጉት።

ከዚህ ማብራሪያ የምንረዳው ነገር ቢኖር በ20ኛክ/ዘመን የመጡት የሸሪዓ ሊቆች የቀደምቱ "ዘር መጠበቅ" የሚለውን ቃል በማሳደግ "ቤተሰብን መጠበቅ"የሚል አዲስ ዕይታ ማምጣታቸው ነው። ኢብን አሹር የተባሉ ታላቅ ዓሊም ለምሳሌ መቃሲድ (አሸሪዓአልኢስላሚያ)በሚለው መጽሐፋቸው "ቤተሰብን መጠበቅ" የሚል እራሱን የቻለ ምዕራፍ አስቀምጠዋል ።የተወሰኑ ሰዎች ኢብን አሹር(ዘርን መጠበቅ)የሚለውን ቃል "ቤተሰብን መጠበቅ" በሚል ቃል መተካት ብቻ ነው ያደረገው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ቃል መተካት ብቻ ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ አምጥተዋል ብለው ይሞግታሉ። የሆነዉ ሆኖ ኢብን አሹር ይህን ሃሳብ በማንሳቱ ለሌሎች ዓሊሞች የመቃሲድ የእውቀት ዘርፍን ወደ አዲስ አድማስ እንዲወስዱት በር ከፍቷል። ሸህ አልቀርዳዊ ለምሳሌ፡ "መልካም ቤተሰቦች መመስረት" የሚል ሃሳብ በመቃሲድ ውስጥ በቀጥታ አስገብተዋል።

አልቀርዳዊ ይህን ሃሳብ ና አዲስ ቃል ወደ መቃሲድ በማምጣት ኢስላም ስለ ማህበረሰብ ያለውን ዕይታና ቤተሰብ የማህበረሰብ መሠረታዊ አካል መሆኑን እናንጸባርቀዋል። ይህን ሲያደርጉ ከዚህ በፊት የተነሱ ዘርን መጠበቅ፤የብልት ጥብቅነት፤የቅሌትን ቅጣት የመሳሰሉት አባባሎችን ውድቅ ማድረጋቸው ሳይሆን ክግለሰብ ና ቡድን የማያልፉትን እነዚህን ቃላቶች ወደ መሬት ለማውረድ መልካም ቤተሰብ በመመስረት ውስጥ የሚረጋገጡ መሆናቸው ለማሳየት ነው። ለቤተሰብ ቅድሚያና ትኩረት ስንሰጥ የሙስሊም ሴቶችና የልጆችን መከበርን ያረጋግጣል፤ከውርደትና ከበደል ይጠብቃቸዋል። በዚህ መልኩ የመቃሲድ ቃላቶችን እናሳድጋለቸዋለን። ሃሳቦቹን ስናሰፉቸው በአሁን ዘመን ያሉ የኡማውን ጉዳይ ማስፈጸም ና ፍላጎቱን ማሟላት እንችላለን ።

ከኢብን አሹር በኃላ ያመጣው ዘመናዊው የመቃሲድ ዕይታ አል_ዓሚሪይ እንዳሚለዉ የሰዎችን ጥቅም (በቅጣት)መልክ ማስከበር ወይም እንደገዛሊ ዕይታ "ጉዳት"ን ለማስወገድ ና "ጥቅም"ን ለማምጣት ( ሂፍዝ ወይም መጠበቅ )የሚለው ፍልስፍና ተግባራዊ በማድረግ ሳይሆን እሴቶችና ስርዐቶች ላይ ትኩረት ያደረገው እንደ ፍትህ ፤ ነጻነት ያሉ አዳዲስ ሃሳቦች በመቃሲድ አሸሪዓ ላይ በማስገባት ነዉ። ነገር ግን አንድ አንድ አሊሞ ች ይህን የመተካት ሃሳብ ተቃውመው እነዚህ እሴቶችን በቀደምቱ ዕይታ ውስጥ ማካተትን ይመርጣሉ ። ይሁነና የመቃሲደሸሪዓ የዕዉቀት ዘርፍ እንደማንኛውም ዕይታና ንድፈ ሃሳብ ማደጉና መለወጡ ችግር አለው ብዬ አላምንም። (አእምሮን መጠበቅ) የሚለውን የመቃሲድ አባባል እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ አስካሪ መጠጥን ለመከልከል ብቻ የሚመጣ አባባል ነበር። ይሁንና በዘመናችን ያሉ አእምሮን ከመጠበቅ ጋር የተያያዘ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ማካተት አለበት ። ለምሳሌ፡ የአእምሮ ስደት ና የመንጋ አስተሳሰብና መፋለም ሳይንሳዊ ምርምሮችን ማስፋፋት ፤ ዕዉቀት ፍለጋ መጓዝ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ ።

(ክብርን መጠበቅ፣ ህይወትን መጠበቅ)የሚሉት ሁለቱ የመቃሲድ አባባሎች ገዛሊና ሻጥቢይ ከአንገብጋቢ ነገሮች (ደሩሪያት)የሚቆጥሯቸው ሲሆን ከእነሱ በፊት አልአማሪ ክብርን የመጣስ ቅጣት የሚል ስያሜ ተጠቅሟል ።ከእርሱ በኃላ የመጣው ጁወይኒ (ክብርን መጠበቅ)የሚለው ሃሳብ አስቀምጦታል። ክብር ከእስልምም በፊት የነበሩ የአረብ ጎሳዎች ጋር ትልቅ ቦታ ነበረው ። ይህን እውነታ በጃህሊያ የነበረው ገጣሚ ባለ ቅኔ ዓንተራ ቢን ሸዳድ ስለክብር

የተዋደቀበትን  የጦር አዉድማ ክስተት የገለጸበት ግጥም ዉስጥ እነዚህ ስንኞች እናገኛዋለን ።

ولقد خشيت بأن أموت ولم تدر

للحرب دائرة على ابني ضمضم

الشاتمي عرضي ولم اشتمهما

والناذرين إذا لك ألقهما دمي

የግጥሙ መልዕክት ፡- ክብሬን በስድብ ያጎደፉት የበኒዶምዶም ሠዎች ላይ ጦርነት ሳልዘምት እንዳልሞት ፍርሃት አድሮብኛል። የሚል መልዕክት አለው

አለይ ኢብን አቢይ ጣሊብ ጋር ሃሳን ኢብን ሳቢት እንደዚሁ ለክብር ትልቅ ቦታ የሚሰጥ ስንኝ  ቋጥረዉ እናገኛቻዋለን ።አሊይ በግጥማቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡- ማንኛው ገንዘብ የለመነኝ ሰው እሰጠዋለሁ። ይህን በማረጌ የለስገኩት፡ ሰው፡ጨዋ ከሆነ ክብሬን ፤ መናጤ ከሆነ ክብሬን እጠብቃለሁ።

ነብዩ( ሰ.ዐ.ወ. ) የማንኛውም ሙስሊምደሙ  ክብሩም  ገንዘቡም እርም ነው ሲሉ መናገራቸው ለክብር ያለው ቦታ ታላቅ መሆኑን ያስረዳናል።  በአሁኑ ዘመን (የሰው ልጅን ክብር፣ሠብዓዊ መብትን መጠበቅ የሚሉ አዲስ አባባሎች (ክብር መጠበቅ)የሚለውን ቀደምት አባባል እየተኩት ይገኛል።

ሙስሊም በሆኑ ባልሆኑም ተመራማሪዎች  ዘንድ እስላም ና ሰብዓዊ  መብት በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ልዩነት ያለ ቢሆንም 1981 ዓ.ል. አለም አቀፋዊ ይዘት ያለዉ ኢስላማዊ የሰብአዊ መብት አዋጅ ውጥታል። ይህ አዋጅ ላይ በዛ ያሉ ዑለማዎች በተገኙበት በዩኒስኮ በኩል ነበር የታወጀው። የአዋጁም አንቀጾች ከቁርሃንና ከሀዲስ ተጣቅሰው ነው በዉስጡ የተካተቱት የሰብአዊ መብት ፣ በህይወት የመኖር መብት፣ ነጻነት ፣እኩልነት፣ፍትህ፣ፍትሃዊ ፍርድ፣ለቅጣት አለመጋለጥ፣የጥገኝነት መብት፣የዕምነትና የፈለጉትን ሃይማኖት የመከተል ነጻነት፣ ሃሳብን የመግለጽ የመሰብሰብ ትምህርት የማግኘት መብት፤የመንቀሳቀስነጻነት ናቸው።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኮሚሽን ውስጥ ያሉ አንዳንድ አባላት አለም አቀፉ የኢስላማዊ መብት አዋጅ የተጠቀማቸውን ቃላቶችን በማንሳት የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት አዋጅ ያስገኘዉን ወጥ ስምምነት ይሸረሽራል በማለት ስጋታቸውን ሲገልጹ ሌላ አባላት ደግሞ ኢስላማዊ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት አዋጅ ራሱን ችሎ መውጣቱ ተጨማሪ አወንታዊ ውጤት ነው በማለት ተከራክረዋል ። ይህ ብቻ ሳይሆን ይህ ስምምነቱ ለመብቶቹ ስነምግባር ና ሃይማኖታዊ ይዘት ያላብሳቸዋል ብለው ያምናሉ። በመቃሲድ ማዕቀፍ ዉስጥ የተዘጋጀዉ የሰብዐዊ መበት ዕይታ ሁለተኛውን ሀሳብ ሚደግፍ ሲሆን የመጀመሪያውን ቡድን ስጋትም ችላ አይልም ። የመቃሲደሸሪዓ ግንዛቤ ዘመናዊና አለም አቀፍ ህጉን ያዋጀ እንዲሆን ከፈለግን ይህን አቅጣጫ መምረጥ ግድ ይለናል። በዘመናዊ የሰብዓዊ መብት ግንዛቤና በመቃሲድ አሸሪዓ መሃል ያለው ግንኙነትና ልዩነት በተለይ ተግባራዊ ሲደረግ የሚያጋጥሙ ተግዳራቶች ለመፍታት ገና ብዙ ጥናት ያፈልጋል ።

(ሃይማኖትን መጠበቅ)የሚለው ገዛሊና ሻጥቢይ የተጠቀሙት አባባል አመጣጡ ከአል አሚሪይ (ሃይማኖትን የመልቀቅ ቅጣት)ከሚለው አባባሉ ነው። ከዚህ በመነሳት በዘመናችን የእምነት ነጻነት የሚባል ግንዛቤ ቢን አሹር መጠቀሙና ሌሎች ተመራማሪዎች “በሃይማኖት ማስገደድ የለም ”የሚለውን የቁርዓን አንቀጽ በመጥቀስና በሃይማኖት መቀየር ቅጣት ከሚለው ግንዛቤ የመጀመሪያው ጠንካራ መሆኑን በመግለጽ ይከራከራሉ። የሃይማኖት መቀየርቅጣት (ሀዱ አሪዳ)በተለመደው የፊቂህ አካሄድ (ሃይማኖትን መጠበቅ)በሚለው ግንዛቤ ስር በስፋት የሚታወቅና ሃይማኖትን የቀየረ ሰው ሌላ ወንጀል ባይሰራ እንካን ቅጣቱ ተግባራዊ ይደረግ እንደነበረ ከዚህም አልፎ ይህን የቅጣት ዓይነት ፓለቲከኞች የራሳቸው ስልጣን ለማስጠበቅ ይጠቀሙበት እንደነበር ይታወቃል።ሰፊ ምርምር ቢፈልግም በዚህ ዘመን መቃሲደሸሪዓን እንደ ስልት በመውሰድ ይህን አካሄድ “በሃይማኖት ማስገደድ የለም” በሚለው አስተሳሰብ መቀየር ይቻላል።

በመጨረሻም (ገንዘብን መጠበቅ)የሚለውን አባባል ገዛሊ የተጠቀመው ሲሆን አልአሚሪ ገንዘብን የመንጠቅ ቅጣት ወይም የስርቆት ቅጣት በሚል ካነሳው ሃሳብ ጋር ተዛማጅነት አለው ። አልጀወይኒ የገንዘብ ጥብቅነት (ኢስሙቱልማል)በማለት ያነሳው ሃሳብም ጋር ቁርኝነት አለው። እነዚህ ሃሳቦች በዘመን ሂደት እያደጉ የመጡ ሲሆን በዚህ ዘመንም በመቃሲድ ሸሪዓ ዙሪያ

የተጻፉ መጽሐፎች ምጣኔ ሃብታዊና ማኅበራዊ ዙሪያ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላቶች ይጠቀማሉ ። ለምሳሌ፡ማኅበራዊ ትብብር፤ በኢኮኖሚ መደቦች መሀከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ማጥበብ የሙሣሰሉ ሀሳቦችን በመጥቀስ የግለሰቦችን ገንዘብ መጠበቅና አራጣ እርም ማድረግ የመሳሰሉ ቀደምት ሃሳቦች አብረው ይነሳሉ፡እንደዚህ አይነቱ የግንዛቤ ዕድገት መቃሲደሸሪዓ በኢኮኖሚ በማኅበራዊ ላይ አወንታዊ አስተዋጾኦ እንዲያደርግ ያግዘዋል። በተለይ ብዙሃኑ ሙስሊም በሆነበት ሀገር ውስጥ ይህ ግንዛቤ ትልቅ ሚና አለዉ ።

"የሰው ሃብት ልማት" የሚባለው ግንዛቤ የተባበሩት መንግስታት ልማትን ለማሳለጥ ይጠቅማል ብሎ የሚወስደው ሲሆን (ከምጣኔ ሃብት ልማት)ግንዛቤ ሰፋ ያለ  ጽንሰ ሃሳብ ነው።  የተባበሩት መነግስታት በቅርቡ ያወጣቸው ሪፖርቶች እንደሚያመለከቱት (በሰው ሃብት ልማት)ዘርፍ ብዙሃኑ ሙስሊም የሆነባቸው ሀገራት የመጨረሻው ደረጃ ላይ ይገኛሉ።የሠው ሃብት ልማት ሲባል የፓለቲካ ተሳትፎ ፣ የመሃይምነት ቅነሳ፣የትምህርት ተደራሽነት፣፡የአማካይ ዕድሜ ርዝመት፣ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽነት፣የስራ አጥነት መጠን፣የኑሮ ደረጃ መሻሻል፣ማህበራዊ ፍትህን ከግንዛቤ ያስገባ ነው። አነዳንድ ሙስሊም ሃገራት በተለይ የናፍጣ አምራች ሃገራት በነፍስ ወከፍ ገቢና በማኅበራዊ ፍትህ መሃከል ንጽጽር ሲደረግ ከፍተኛ ልዩነት ያለ ሲሆን በተለይ የሴቶች በማኅበራዊና በኢኮኖሚ ዘርፍ ያላቸው ተሣትፎ በኩል ከፍተኛ ልዩነት ይስተዋላል።

አናሳ ሙስሊሞች ከሚኖሩባቸው ሀገሮች ባለፈ ሙስሊም ሃገር ሁነዉ  እንደ ኳታር፣ ብሮናይ፣የተባበሩት አረብ  ኢሜሪት ያሉ ሀገራት ላይ ከፍተኛ ልማት ካስመዘገቡ ሃገራት ተርታ ተሰልፈዋል። የእነዚህ ሀገሮች ህዝብ ስንመለከት ግን ተደምረዉ  ከአጠቃላዩ የሙስሊሞች ብዛት አንድ ፐርሰንት ያነሰ ነው። በሪፓርቱ ግርጌ ካሉት የሙስሊም ሃገሮችን ስንመለከት የመን፣ናይጄሪያ፣ ሞሪታኒያ፣ጅቡቲ፣ጋምቢያ  ሴኒጋል፣አይቮሪኮስት፣ማሊ፣ኒጀር  ይገኙበታል። የእነዚህ ሃገሮች ሙስሊም ነዋሪዎች ድምር ስንመለከት በአጠቃላይ 10 በሙቶ ይሆናሉ።

በዘመናችን " የህዝብ ጥቅም"(መሳሊ ህልኡማ) ለማረጋገጥ ከላይ የተጠቀሱትን የሰዉ ሃብት ልማት መስፈርቶችን ማማላት እንደቅደመ ሁኔታ ብናስቀምጥ የተሻለ ነው ብዮ አስባለሁ። ምክንያቱም መቃሲደሸሪአ ግብ አድርጎ

የሚንቀሳቀሰው እነዚህን መስፈርቶች ለማረጋገጥ ስለሆነ በእውቀት ላይ በተመሰረተ መልኩ መገምገምና መሬት ላይ ማረፋን ማረጋገጥ ይገባል። ይህን መሬት ላይ ለማሳረፍ በሰብአዊ መብት ዙሪያ እንዳልነው ሁሉ በመቃሲደሽሪዐ መነጽር በሰው ሃብት ልማት ዙሪያ የሚደረግ በዛ ያለ ጥናት ያስፈልጋል። መቃሲድ አሽሪአ የሰው ሃብት ልማትን አካቶ መዐዙ ለሙስሊሙ ዓለም ህዳሴ ፅኑ መሠረት ያስቀምጣል።

## <u>መቃሲደሸሪዓ ለአዲስ ምርምር(ኢጅቲሃድ) መሠረት</u>

በእስልምና የመሠረተ_ ፊቂህ (ኡሱሉልፊቅህ) ትምህርት እንደሚያስተምረዉ በ(ተዓሩድ)ተቃርኖ ና (ኢኽቲላፍ )ልዩነት መሃከል ሰፊ መለያየት አለ ። ተቃርኖ የሚባለው በእውነታ ወይም በትክክለኛ ና በስህተት፡መሀከል፡ያለ፡ሦስተኛ፡ አማራጭ፡የማይቀበል የመንክዩ ውጤት ነው። ልዩነት ግን በ"መረጃ" ዙሪያ ያለ የተለያየ የተመራማሪዎች ግንዛቤ ነው። ይህ ማለት ሁለት የሚቃረኑ የሚመስሉ መረጃዎችን ተመራማሪዉ ሲያገኝና ሁለቱን መረጃዎች ማስማማት ሲሳነዉ የሚፈጠረዉ የዕይታ ልዩነት ነዉ ። ይህ የሚመነጨዉ መረጃዉ የተዘገበበትን ሁኔታ፤ ግዜና ቦታ ካለመረዳት ሊሆን የሚችል ሲሆን እነዚህ ምክንያቶች በመረጃው ዙርያ ያለዉ አረዳድና አተገባበሩ ላይ ትልቅ ተጽእኖ ይፈጠራሉ ። ሁለቱን መረጃዎች በማጣራት ሂደት ውስጥ አንዱ መረጃ ደካማ (ዶኢፍ ) ሆኖ ሊገኝ የሚችልበትን አጋጣሚ አለ። ይህ ሲሆን ትክክለኛውን (ሰሂሁን)ሀዲስ በመውሰድ ችግሩን መፍታተ ይቻላል ። ይህ ስልት በሃዲስ ሊቆች ዘንድ(ተርጂህ)በመባል ይታወቃል ። ይህ( ተርጂህ)የሚባለው ስልት ብዙ ግዜ ሚዛናዊነት የሚጎለው ነው። ለምሳሌ አቡሁረይራ የዘገቡት ሃዲስ ማየት ይህን ለመረዳት ጠቃሚ ነዉ ።

" إنما الطيرة في المرأة والدابة والدار "

**"ገደቢስነት፡በሴቶች፣በእንሰሳትና፡በቤት፡ውስጥ፡ነው"**

በዚህ ሀዲስ ዙሪያ እናታችን አኢሻ ረ.ዐ. አስተያየት ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ፡ "ቁርዓንን በቃሲም አባት ላይ ባወርድ ጌታ እምላለሁ ነብዪ ሰ.ዐ.ወ.ያሉት ፡ በድንቁርና ግዜ( በጃሂልያ)የነበሩ ሰዎች ገደቢስነት በሴቶች በቤትና በእንስሳ ውስጥ አለ ብለው ያምናሉ ነው፡፡"

*እነዚህ የአኢሻና የአቡሁረይራ ሰሂህ ሀዲሶች የሚቃረኑ የሚመስሉ ሲሆን የሚገርሙ ነገር ግን አብዛኛዎቹ የሀዲስ ተንታኞች ሌላ ተመሳሳይ የሚያጠናክረው ሀዲስ እያለ እንካን የአኢሻን ሀዲስ ውድቅ ያደርጉታል። ለምሳሌ "ገደቢስነት የለም ። በሴቶች በፈረስ በሌሎች እንስሳቶች ውስጥ በረከት አለ" የሚለው ሃዲስን መጥቀስ ይቻላል። የአኢሻን ሃሳብ የቁርአን አንቀጾችም ያጠነክሩታል።*

**{ مَا أَصَابَ مِنْ مُصِيبَةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي أَنْفُسِكُمْ إِلَّا فِي كِتَابٍ مِنْ قَبْلِ أَنْ نَبْرَأَهَا ۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ }**

***"በምድርም በነፍሶቻችሁም መከራ (ምንም)አትነካም ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትሆን እንጂይህ በአላይ ገርነዉ "***

*ይህ ሁሉ የሃዲስና የቁርአን ድጋፍ ያለው የአኢሻን ሀዲስ እንደ ኢብን ጀውዚይ ያሉ ሊቆች ሳይቀሩ የተለያየ ምክንያት በማቅረብ ዉድቅ አድርውታል። አቡበከር ቢን አልደርቢይ የተባለው ዓሊም "ተቀባይነት የሌለው ንግግር "በማለት የአኢሻን ሀዲስ አጣጥሎታል። ከታለቅ ዓሊም በዚህ መልኩ አኢሻን መንቀፍ ተገቢ መስሎ አይታይም። ይህ ባጠቃላይ የሚያሳየው ሁለት የሚጋጩ የሚመስሉ ሀዲሶች ለማስታረቅ በሚደረገው ጥረት ብዙ ዓሊሞች የራሳቸው እምነት ያስቀድማሉ ። ሌላው ተቃራኖን ለማስታረቅ ፉቃሃዎች የሚጠቀሙበት መንገድ (ነስኽ)መሻር የሚባለዉ ነው። ነስኽ ማለት የሚጋጩ የሚመስሉ ሁለት መረጃዎች ሲገኙ የመረጃዎቹ የመጡበትን ግዜ ቅደም ተከተል በማጥናት ሁለተኛ የመጣው መረጃ የመጀመሪያውን ይሽረዋል ማለት ነው። ይህ ስልት በቁርአን አንቀጾችም ሆነ በሀዲሶች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ይህ መረጃዎችን የማስታረቂያ ስልት ተግባራዊ በሚሆንበት መንገድ ፈቂሁ (ሊቁ)ስልቱን በትክክል ባለመጠቀሙ ምክንያት ብዙ ወይም ምንም ችግር የሌለባቸው መረጃዎች ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ፡፡ (ነስኽ)መሻር የሚለውን ቃል በነብዩ ሰ.ዐ.ወ.ንግግር ውስጥ ተጠቅሶ ወይም በአንድም የሃዲስ መዛግብት ውስጥ ተጽፎ አናገኘውም። ባደረግኩት የዳሰሳ ጥናት (ነስኽ) የሚል ስርወ ቃልና ብዜቶቹ በየትኛውም የሀዲስ ሰነድ አላገኘሁትም። ይህ ቃል ስለ መረጃ ተቃርኖ ና የተቃርኖ ማስታረቅ ሂደት ሲገለጽ ሀዲስ ዘጋቢዎችና ተንታኞችነዉ የሚያነሱት አርባ የሚደርሱ የነስኽ(የመሻር)ሂደት አግኛቻለሁ። ሰሃቦች በሀዲስ ላይ አስተያየት ሲሰጡ*

(ነስኽ)የሚለው ቃል ተጠቅመው እናገኛለን ይሁን እንጂ ይህን ቃል የተጠቆሙበት ሁኔታ በጥልቀት ስንመለከትው መሻር የሚለውን ትርጉም ሳይሆን የሚሠጠው (ተኽሲስ)መገደብ የሚለውን ነው፡፡ የቀደሙቱን የተፍሢር መጽሐፎች ስንመለከትም የ(ነስኽን)የመሻርን ስልት ቁርአን አጣቅሰው፡ ማረጋገጥ ይሳናቸዋል፡፡ለዚህም ማሳያ የሚሆነው (ነስኽ)የመሻር ስልት ተግባራዊ የተደረገባችው የቁርዓን አንቀጾች በራሳቸዉ የተለያዪ አስተያየት ያስተናገዱ ናቸው። (ነስኽ)መሻር ካለመረጃ በዘፈቀደ በጥቅም ላይ የዋለ ስልት ሲሆን የሰይፍ አንቀፅ በማለት የሚታወቀው የሱረቱ ተውባ አምስተኛዉን አንቀጽ እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡

{فَإِذَا ٱنسَلَخَ ٱلْأَشْهُرُ ٱلْحُرُمُ فَٱقْتُلُوا۟ ٱلْمُشْرِكِينَ حَيْثُ وَجَدتُّمُوهُمْ وَخُذُوهُمْ وَٱحْصُرُوهُمْ وَٱقْعُدُوا۟ لَهُمْ كُلَّ مَرْصَدٍ ۚ }

**“የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው ያዝዋቸውም ክበቧቸውም ከእነርሱም (መጠባበቅ)በየመንገዱ ተቀመጡ” ተውባህ 5**

ይህ የቁርአን አንቀጽ የወረደበትን ግዜና ሁኔታ ስንመለከት በሂጅራ 9ኛ አመትና ሙስሊሞችና የመካ ካህዲዎች በጦርነት ላይ በነበሩት ግዜ ነው። አንቀጹ ፊትና ኃላ ያሉት አንቀፅች በጠቅላላ ስለጦርነት የሚያወሩ ሲሆን ይህ አንቀጽ የጦርነቱን ሂደት የሚተነትን መሆኑን እንረዳለን ። ይህ ጦርነትን የተመለከተ አንቀፅ ከመጣበት ሁኔታና ሂደት በማውጣት በከሚነት በሁሉም ቦታና ግዜ የሙስሊሞችና ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን ግንኙነት መለኪያ አድርጎ ማስቀመጥ አግባብ አይደለም ።ይህ በጦርነት ግዜ የወረደ አንቀጽ ሌሎች ስለ ሰላም ውይይት፣ ስለ እምነት ነጻነት ፣ ስለ መቻቻል፣ስለ ትግስት የሚናገሩ 200 የሚደርሱ አንቀጾች ሽሯል ብለው የሚያምኑ ብዙ ናቸው። ይህ የሚያመለክተው አብዛኛዎች የቁርአን ሙፈሲሮች ተቃርኖ የመሰላቸውን ነገር የሚያስታርቁት በ(በነስኽ) በመሻር ስልት መሆኑን ነው ። ይህ የቁርዓን አንቀጽ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻ የህይወት ክፍለ ግዜ በመውረዱ ከዚያ በፊት የነበሩትን አንቀጾች ይሽራል ብለው ያምናሉ ።

(በሃይማኖት ማስገደድ የለም ) በቀራ 256 (ከእነርሱ ይቅርታ አድርግ እለፋቸውም፡አላህ መልካም ሠሪዎች ይወዳልና) ማኢዳህ 13 (በዚያች፡እርስዋ መልካም በሆነችው ጠባይ መጥፎዊቱን ነገር ገፍትር እኛ የሚሉትን ሁሉ አዋቂ ነን )ሙእሚኑን 96 (ስለዚህ ታገስ የአላህ ቀጠሮ እውነት ነውና) ሩም 60 (የመጽሐፍን ባለቤቶችም በዚያች እርγ መልካም በኾነች ክርክር እንጂ አትከራከሩ) ዓንከቡት46 (ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አለላችሁ፡ለእኔም ሃይማኖት አለኝ)

የ(ነስኽ) ስልት በመጠቀም ሌሎች ብዙ ስለ ሰላም ስምምነት ፤ የተለያየ ባህልና ሃይማኖት ያላቸዉ ማኅበረሰብ ጋር አብሮ መኖርን የሚያስረዱ ብዙ ሃዲሶችን ሽረዋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከመዲና የሁዶች ጋር ያላቸወን ግኙኝነት የወሰኑበት(ሰሂፈቱ አልመዲና) በማለት የሚታወቀው ስምምነት ውድቅ ተደርጓል። ስምምነቱ በመዲና የሚኖሩ ሙስሊሞችና የሁዶች አንደ ህዝብ የሁሉም እምነት እንደሚከበር ይጠቁማል። አብዛኃኛዎቹ ቀደምት ኡለማዎች (በሰይፍ) አንቀጽ ማለትም ጦርነትን የተመለከቱ አንቀጾቸ ብዙ ሰላምን የተመለከቱ ሀዲሶች መሻራቸው ይናገራሉ። አንድ ሰው በቁርአን ውስጥ ሆነ በሀዲስ ስለ ጦርነትና ስለ ሰላም የሚናገሩ የተለያዩ አንቀጾች ሲያገኝ ተቃርኖ ያለ ሊመስለው ይችላል። ግን ከዘላቂ ሰላም ለምን የሁል ግዜን ጦርነት እንደሚመረጥ አይገባኝም።

የ(ነስኽ)የመሻር ስልት በጣም አስቸጋሪ ካሚያደረገው ነገር ሰሃቦችና የእነርሱ ተከታይ (ነስኽ)ተደርጓል ወይም ተሽራል ብለው ከወሰዱት በተጨማሪ ከእነርሱ በኃላ የመጡ የፊቂህ ሊቆች ሌሎች የተሻሩ ያሏችውን ነገሮች በመጨመራቸው ነው። ይህ ብዙ የፊቂህ ሊቆች ተከራካሪዎቻቸዉን ለማሣመን የሚጠቀሙበት ስልት መሆኑ ነው። ይህን የሚያረጋግጠው ቀጣዩ የአቡ ሀሰን አልከርኺይ አባባል ነው። “እኛጋር ያለው ከሚ ህግ ማንኛውም የመዝሃባችን እይታ የሚቃረን መረጃ የተሻረ ነው”

ነስኽ( መሻር)ማንኛው የፊቂህ መጽሀፍ ውስጥ በቀላሉ ተጠቅመውበት ማግኘት የሚያስገርም ስለመሆኑ የአቡ ሃሰን ንግግር ያሳያል። አንዱ መዝሃብ የሻረውን

ሌላው ሳይሸረው ስናገኝ (ነስኽ)መሻር ማዕቀፍ የሌለው ልዩ የማስታረቂያ ስልት መሆኑ ነው።

ከዚህ በመነሳት መቃሲድ አሽሪዓ (የሽሪዓ መዳረሺያ ግብ)የእውቀት ዘርፍ የተለያዩ መንገዶች በመጠቀም ተቃርኖ ያለባቸው የሚመስሉ አንቀጾችን ለማስታረቅ ታላቅ ሚና አለው ቀጣዮቹ ምሳሌዎች መቃሲድ በዚህ ረገድ ያለዉን ትልቅ ሚና ፍንትው አድርገው ያሳያሉ።

1 _ ኢባዳን በተመለከተ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የተዘገቡና ትክክለኛ (ሰሂህ)የሆኑ ከላይ ስንመለከታቸው ግን ተቃርኖ ያለባቸው የሚመስሉ ብዙ መረጃዎች (ደሊሎች)አሉ። እነዚህ መረጃዎች በሚያሳዝን መልኩ በሙስሊሞች መሃከል የግጭት ምንጭ ሆነው እናገኛቸዋለን። መረጃዎቹን በመቃሲድ መነጽር ብንመለከታቸው ኢባዳን ለማቅለል( ለተይሲር)ተፈልጎ መሆኑን እንረዳለን። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ኢባዳ (የአምልኮ ስርአት)በተለያየ አኳሃን መፈጸማቸው ለሙስሊሞች ነገሮችን ለማቅለል እና አማራጭ ለመስጠት አላማ በማድረግ ነው። ለምሳሌ፡ በሰላት የእጅ አቀማመጥ ፤ የተሸሁድ አይነቶች ሙብዛት ፤ የረሳ ሠው ሱጅድ አፈጻጸም መለያየት ፤የኢድ ሰላት ተክቢራ ፤ በሀጅ ስርአት አፈጻጸም ዝርዝር ጉዳይ የተገኙ የተለያዩ አተገባበሮች ማቅለልን ዓላማ ያደረጉ ናቸው ።

2-ሌላው ደግም ከባህልና ከወግ ጋር የተያዙ ዘገባዎች ናቸው። እነዚህ ዘገባዎች ተቃርኖ ያለባቸው ቢመስሉም አንድ ሌላውን ከመሻር ይልቅ የሽሪዓን (አለምአቀፋዊነት)ከግንዛቤ በማስገባት መረዳት ተገቢ ነው። ይህ ማለት ከባህልና ወግ ጋር ተያይዞ የተዘገቡ ሃዲሶች የሚስተዋልባቸው ልዩነት ከሠው ልጅ ባህልና ወግ ልዩነት የመነጨ ነዉ ። ሽሪዓውም ለነዚህ የተለያየ መልስ ላላቸው ባህልና ወግ እውቅና መስጠቱን እንረዳለን ። ለምሳሌ አዒሻ የዘገበችውን ሁለት ሃዲሶችን በማንሳት በቀላሉ ጉዳዩን መረዳት ይቻላል። የመጀመሪያው አዒሻ ( ረ.ዐ.) የዘገበችው ሃዲስ ሲሆን ማንኛውም ሴት ልጅ ከቤተሰቦቾ ፍቃድ ውጭ ትዳር መመሥረት እንደማትችል የሚናገር ነው "ሌላው አዒሻ (ረ.ዐ.)የዘገበችው ሃዲስ ደግሞ ከዚህ በፊት አግብታ የምታውቅና የፈታች ሴት ከቤተሰብ ፍቃድ ውጪ በራγ ምርጫና የፈለገችውን ማግባት ይፈቅዳል። ሁለቱንም ሀዲሶች የዘገበችው እናታችን አዒሻ (ረ.ዐ.)ስትሆን እራሳ

አኢሻ ያለምንም ወላጅ ፍቃድና መስማማታን ሳትጠይቅ የወንድሃን ሴት ልጅ ሀፍሳ ቢንት አብድራህማን መዳሯ ይታወቃል፡፡ የፊቂህ ተማራማሪዎች በተለይ የሃነፊ መዝሃብ ተመራማሪዎች ይህን ጉዳይን ሲያብራሩ ሴት ልጅ በራሳ ፍቃድ ትዳር መመስረት የተከለከለችው ከባህል አንጻር ሲሆን ጋጠወጥ ተብላ እንዳትፈረጅ በማሰብ ነው ይላሉ፡፡ ነገሩ ሁለቱን ሀዲሶች በማጣመር ከባህል አንጻር የሸሪዓን አለማቀፋዊነት የመቃሲድ እይታ ስንመለከተው የተቀሩውን ችግር መፍታት እንችላለን፡፡ ማንኛውም በአለማችን ክፍል የሚገኝ በተለያየ ግዜ የሚፈጠር ማኅበረሰብ ጋብቻን ሀራም ባልሆነና ባህሉና ወጉ በሚፈቀደው መልኩ ማከናወን እንዲችል ያመቻቻል፡፡ ይህም በተለያየ ባህልና ወግ እንዲሁም ዘርና ጎሣ ባላቸው ማኅበረሰብ መሀከል አብሮ የመኖር ና የመቻቻል ባህልን ያዳብራል፡፡

3-ሸሪዓን ቀለል ባለ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ደረጃ በደረጃ ህጎች ከቀላል ወደ ከባድ ይወጡ ነበር፡፡ በዚህ ረግድ የተዘገቡ ብዙ ሀዲሶች(መንሱኽ)የተሻሩ ተብለው ተፈርጀዋል፡፡ ይህ ደረጃ በደረጃ ሸሪዓ ተግባራዊ የማድረግ አካሄድ የተፈጸመው አንድ አጉል ባህል በከፍተኛ ሁኔታ ሰርፆ ያለበት ማህበረሰብን በአንዴ ለመቀየር አስቸጋሪ ስለሚሆን ነዉ፡፡ በአስካሪ መጠጥ፤ የአራጣ ክልከላ ፤ በሰላትና በጾም ግዴታ ዙሪያ የተዘገቡ ሃዲሶች መሀከል ተቃርኖ ያለባቸው ቢመስሉም ከጠቀስነው ህግና ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ማድረግ መርህ ጋር አያይዘን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ በተለይ አዲስ እስልምና የተቀበሉ ሰዎች የእስልምና አስተምህሮት ትዕዛዛትን ተግባራዊ ለማድረግ ለመለማመድ በቂ ግዜ ስለሚፈጥር ይህ መርህ ለእነርሱ ተስማሚ ነው፡፡

4-አንድአንድ ዓሊሞች የተለያዩ የሚቃረኑና የሚመስሉ የተለያዩ ግለሰቦችን የሚያናግሩ ሀዲሶችን ሰብስበው ለማስታረቅ ሲሞክሩ እናያለን፡፡ እነዚህ ሃዲሶች የተለያዩ ባህሪና ገጠመኞች ያላቸው ግለሰቦች የሚያናግሩ ስለሆነ የሚቃረኑ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ በዚህ መልኩ የተዘገቡ ሃዲሶች የምንረዳዉ ትልቁን( የሰዎችን ጥቅም እስከጥግ ማሳካት)የሚለውን የመቃሲድ ግብ ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት የተፈታች ሴት ሌላ ባል ካገባች ልጅ የማሳደግ መብቷን ታጣለች፡፡ አቡ ዳውድ በዘገቡት ሃዲስ “አንዲት ሴት ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.)በመምጣት የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ይህን ልጅን ሆዴ ለርሱ መቋጣሪያ ሆነ (በሆዴ አርግዥሁውጡቴን አጥብቼ በጉያዮ አሳድጌው) አባቱ አሁን ሲፈታኝ ዳግም ይህን

ልጄን ሲነጥቀኝ ይፈልጋል ብላ አለች ፡፡ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) "እስካላገባሽ ድረስ ልጁ ላንቺ ተገቢ ነው" አሏት ፡፡ ይህን ሃዲስ የሚቃረኑ የሚመስሉ ሌሎች ሀዲስ ያሉ ሲሆን ለምሳሌ፡ኡሙ ሰለማ( ረ.ዐ.) ነብዩን አግብታ ስትኖር ልጆቿ አብረዋት ይኖሩ ነበር። አብዛኛው የፊቅህ መዝሃቦች እናት ሌላ ባል ከገባች ልጅ የማሳደግ መብት በቀጥታ ወደ አባት ይሸጋገራል የሚለውን ሀሳብ ይደግፋሉ የፊቅህ ሊቆች የሁሉተኛውን ዘገባ ትተው የመጀመሪያውን የመረጡበት ምክንያት ቡኻሪ ስለዘገባው በሚል ብቻ ነዉ ፡፡ ከሌሎቹ አሊሞች በተለየ ከተለየ ሁለተኛውን ሃዲስ ኢብን ሃዘም አዝሃሪ ሲመረጥ ስነዓኒ የተባሉት ዓሊም ዳግም ምርጫው የልጁን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ መሆን አለበት ብሁል። በሰንዓኒ አቁዋም ውስጥ ፍትህና ጥቅም ማስከበርን የምናስተውልበት ሲሆን ሁለቱም የመቃሲድ ሸሪዓ መለኪያ ሚዛኖች ናቸው። ምክንያቱም ሸሪዓ ፍትህ ማዕደልና ጥቅምን ማሳጣት ባህሪው አይደለም። እንደዚህ ያለው እይታ አንድ ሙስሊም ግለሰብ ከማንኛውም ፍትህን በማኅበረሰቡ ውስጥ ለማረጋገጥ የተቀመጠ ማንኛውንም ሠው ሠራሽ ህግ አንጻር ፍትሃዊ አከም ይኖረዋል። ህጉ መነሻው ኢስላማዊ ባይሆን እንካን ፍትህ የሁሉም ህግጋቶች የጋራ ዓላማ ነውና።

## <u>በምክንያት ወይም መንገድ (ወሣኢል ) ና በግቦች (ቢጋያት ) መሀከል ያለው ልዩነት</u>

በመንገዶች (ወሣኢል) ና በግቦች መሀከል ልዩነት መኖሩን ያስቀመጡት ሼህ መሐመድ አልገዛሊ ናቸው ፡፡ መንገዶች ወይም ስልቶች በዘመን ሂደት ና ዕድገት ሊቀያየሩ እንደሚቻሉ ፤ ግቦች ግን ቋሚ ና ዘላቂ መሆናቸው አብራርተዋል። ለዚህም ምሣሌ ብለው ከጠቀሡት ውስጥ የምርኮ ገንዘብ (ገኒማ )ነው። ገኒማ በግልጽ ቀርዓን ላይ የተገለጸ ቢሆንም ግዜው ያለፈበትና በሌላ ነገር የሚተካ ተልዋጭ ስልት መሆኑን ይጠቅሳሉ ፡፡ በመንገድ (ስልት) ና ግቦች መሀከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ አሰፈላጊነት በስፋት የተነተኑት ሸህ ዩሱፍ አልቀረዳዊና ፈይሰል መውለዊይ ናቸዉ ፡፡ ሁለቱ ታለቅ ኢሊሞች ይህን ትንታኔ ያቀረቡት የረመዳን ወር አጀማመርን በተመለከተ የአውሮፓ የፈተዋና የምርምር ም/ቤት ባዘጋጀው ውይይት ላይ ነበር። በዚህ ውይይት ላይ ሁለቱም ዓሊሞች እንደገለፁት የረመዳን ወር መግባቱን ለማረጋገጥ የመጀመሪያው ቀን ጨረቃ ማየት በራሱ ግብ ሳይሆን ረመዳን መግባቱን የምናረጋግጥበት ስልት ነው ፡፡

የረመዳን ወር  መግባቱን ለማረጋገጥ የመጀመሪያ ቀን ጨረቃ ተጠባብቆ ከመመልከት በተሻለ የህዋ ምርምር ቀመርን ተግባሪው በማድረግ የረመዳን ወር መግቢያ ቀን ለመወሰን የተሻለ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በተለይ አናሣ ሙስሊሞች በሚኖሩበት ሀገራት ይህን  መንገድ መከተል  የተሻለ ነው፡፡ ዩሱፍ አልቀረዳዊ ይህንኑ ሐሣብ በጂልባብ ላይ ተግባራዊ ያደረጉት ሲሆን ጂልባብ በራሱ ግበ ሳይሆን የሴት ልጅ ጥብቅነት ለማረጋጋጥ የሚውል ስልት ነው፡፡ በምክንያት (በስልት )ና በግብ መሀከል ያለውን ልዩነት መረዳት በእስልምና ድንጋጌ ዙሪያ ያሉ አዳዲስና ጥንታዊ ሐሣቦችን ለማብላለት መንገድ ተከፍታል ፡፡

ዶ/ር ጠሃ አልዓለዊኒ የተባሉ ዓሊም (ኢስላህ አል ፊክር እል ኢማላሚይ )በተሠኘው መጽሐፋቸው ግብና ስልትን ለያይቶ የማየት  ግንዛቤ መስፋት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው በተለይ እንድ ጾታዊ ዕኩለነት ያሉ ሀሣቦችን ለማንሸራሸር ጠቃሚ ነው ይላሉ ።

“ቁርዓን በመጀመሪያው የተልዕኮ ዘመን ሠዎችን ወደ ኢማን ያሸጋገራቸው ሁለቱንም ጾታዎች በእኩልነት በመያዝ ነው።  ይህ ነጥብ በኢስላም ታሪክ የነበረ እውነታ  ነው። ጣኦት  እምልኮን ከመዋጋትና ከማስወገድ ያልተናነሠ ትልቅ የአስተሣሠብ አብዮታዊ ለውጥ ነበር። የመጀመሪያው የሙስሊም ማህበረሰብ ስንመለከት የአረብ ፔንሱላ የነበረው ስር  የሰደደ ቀደምት ባህል ጋር የተቆራኘ ከድንቁርናው ዘመን የተወረሠ ልማድ ብዙም ሩቅ ያልሆነ ማህበረሰብ ስለነበር ለውጦችን ደረጃ በደረጃ  ተግባራዊ ማድረግ ግድ  ይላል።በሂደት ማህበረሰቡ ባለው ከባባዊ  ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለውጥን ተግባራዊ ያደረጋል። እስልምና ሴት ልጅ ችሎት ላይ ምስክርነት እንድትሠጥ ማድረጉ  ከአስላም በፊት ያልነበረ ትልቅ የለውጥ እርምጃ ተደርጎ ይቆጠራል። በዚህም እስልምና ሴቶችን እንደ አቻ አጋር በመውሰድ ሚናቸውን ማጠንከር፣ የዘልማዱን የሴቶች ሚና ማስወገድን ታሳቢ ያደረገ ነበር። ቁርዓን ከመስክርነት ቃል ሰጭዎች ጋር ሴቶችን ሲያካትት በራሱ ግብ ሳይሆን ግብን ለማረጋገጥ የተጠቀመው ስልት ነበር።(አንዷ ሌላዎን እንድታስታውሳት) የሚለው የቁርዓን አባባል ዙሪያ ሲተነትኑ ቀደምቶቹ ዑላማዎችም ሆኑ አብዛኛው የዘመናችን ዓሊሞች ሴቶችና ወንዶች እኩል አይደሉም የሚለውን ሃሣብ ይደግፋሉ ።በዚህ ምክንያት ብዙ ትልውልድ ይህን

የተሣሣተ ሐሣብ እየተቀባበለ በጭፋን እያመነበት መጥቷል። ይህ አቋም እንዲኖር ሌሎች የፊቅህ ርዕሦችም ተፅኖ ቀላል አልነበረም ።”

እያቱላህ መህዲ ሽምሰዲን የተባሉ ዓሊም ተመሣሣይ ሀሣብ ያነሣሉ። በዘመናችን ያሉ የፊቅህ ሊቆች በቁርዓንና በሃዲስ ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ ዳይናሚካል መሆን አለበት ይላሉ። ቁርዓን ዉስጥ ያሉ ድንጋጌዎች ፍጹም የማይቀየሩ አድርጎ ማሠብ ተገቢ እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ። በማንኛዉም ግዜ ቦታ በሁሉም ስብዕና ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ ብሎ ማመን የተሣሣተ ነው። አያቱላህ መህዲ ሽምሰዲን አቋማቸው ይህ ቢሆንም ቅሉ በዚ መርህ ላይ ተመርኩዘው አዲስ የሸሪዓ ድንጋጌ አላስቀመጡም ። ይሁን እንጂ ይህን መርህ በመከተል በተለይ ከሴቶች ፣ከጅሃድ ፣ ከፋይናንስ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አበክረው ይናገራሉ።ሌላው ምሣሌ ዶ/ር ፈትሂ ኡስማን የሴት ልጅ ምስክርነት ጋር በተያያዘ ሳይንሣዊ በሆነ መልኩ የተናተኑበትን መንገድ ነው።ዶ/ር ፈትሂ ኡስማን የሴት ልጅ ምስክርነት በተመለከ የወረደውን የቁርዓን አንቀፅ ከሳይንሣዊ እውነታዎች ጋር በመያያዝ በአዲስ መልኩ ተንትነውታል። ዶ/ር ሀሰን አቱራቢም ይሁንኑ ሀሣብ በማንሣት በሴት ልጅ ጉዳይ የሚያነሱ የፊቅህ ርዕሦችንና ስለ አለባበሥ ያሉ ሀሣቦች በተመለከተ ሀሣብ አቅርበዋል። ሐጂይ ጋሩዲይ በተመሣሣይ ይህን ሀሣብ የሚጋራ ሲሆን ቁርዓንን በሁለት ከፍሎ ያየዋል። የመጀመሪያው ክፍል ከግዜ ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ሲሆን ሁለተኛው የማይቀየር መርህና አሴት ነው። ከሴቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ርዕዎችን ከታሪካዊ ክፍል ውስጥ ያካትታቸውል ።

አብዱከሪም ሰሩሽ የተባሉ ዓሊም እንደዚሁ ቁርዓን በሁለት ከፍለው ያዩ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል (ሰዋቢት )የማይቀየር ሁለተኛውን (ሙተገይራት )ተለዋዋጭ በማለት ሰይመውታል። ነገር ግን አንድ አንድ በምዕራቡ ዓለም ፍስልሰፍና የተሳቡ ፀሐፊዎች ድንጋጌን ከታሪካዊ ክስተት ጋር በማስተሳሰር ብቻ መረን ለቀው ይሄዱ እንዳሉ ማስተዋል አለብን ። እነዚህ ፀሐፊዎች “ታሪካዊ ” የሚለውን ግንዛቤ ሙሉ በሙሉ ቁርዓንና ሀዲስ ላይ ተግባራዊ ያደርጉታል ። ይህ ማለት ደግሞ አንድ መጽሐፍ (ቁርዓንና ሀዲስን) ጨምሮ በተከሠተበት ግዜና ቦታ ፣ ሲውርድ በነበረው ባህልና ወግ ብቻ የተገደበ ነው የሚል ግንዛቤ ይፈጥራል። ከዚህ በመነሣት ቁርዓን (ባህላዊ ስራት )ነው የሚል የተሣሣተ ድምዳሜ ላይ ያደርሣል። ይህ አይነቱ

ግንዛቤና ሀሣብ ቁርዓንን በሆነ ግዜ በነብዮ (ሰ.ዐ.ወ ) ዘመን ለነበረ ማህረሰብ ብቻ የሚያገልል ታሪካዊ ሰነድ ብቻ አድርጎ የሚመለከት ነው። ከዚህ ሐሳብ አራማጅ ከሆኑት መሐከል እንዷ ሀይዳ ሞጌሴ የተባለች ግለሠብ "ቁርዓን በሠዎች እኩልነት መርህ ጋር አብሮ አይሄድም "ብላ ትሞግታለች "ምን ያህለ የቁርዓን አንቀጾችን ብንጠመዝዛቸው፣ እንዲሁ ትርጉም ብንሠጣቸው የጾታ ዕኩልነት ና የቁርዓን ትዕዛዛትን ማስማማት አንችልም " በማለት ትከራከራለች። ሌላው አብኑ ወራቅ የተባለ ፀሐፊ "በኢስላም የተሠጠው ለሰብዓዊ መብትእና ለነፃነትን መርህ በቂ ድጋፍ አያደርግም "ይላል ። ኢብራሂም ሙሣ የተባለው ሌላው ግለሰብ "የኢስላምና የፊቅህ ትምህርት ለሰነምግባር ዕይታ አቅጣጫ ሊሆን አይችለም" በማለት ይገዳደራል ። ቁርዓንን ኢፍትሃዊ ና ኢሞራላዊ ነው ብሎ መሞገት እንዳኔ ሀሣብ ከአላህ መጽሐፍ (ቁርዓን )ካለን እምነት ጋር በመጀመሪያ ይጣራሳል ፡፡ ነገር ግን በቁርዓን ውስጥ የተጠቀሱ ታሪካዊ ክስተቶች እና አንዳንድ የፊቅህ ድንጋጌዎች ከታሪካዊ ፣ ከባህልና ከጆግራፊ ዳራ አንፃር መረዳት ተገቢ ነው። ይህን ግንዛቤ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ ቁልፍ መፍትሄ በስልትና በግብ መሀከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ መቻልነው ፡፡ ሼህ ገዛሊይ እንደሚሉት ስልቶች ምን ግዜም ግዜያቸው ሊያልፍባቸው፣ ሊቀያየሩ የሚችሉ ነገሮች ሲሆኑ መርሃዊ ግቦች ግን ሁልግዜም የማይለዋወጡ ወጥ ናቸው ። ይህን ግንዛቤ በመያዝ የቁርዓን እንቀጾች በየተኛው ግዜና ቦታ ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን።

## <u>መቃሲድና እዕስን ዓለማ ያደረገ የቁርዓን ተፍሲር</u>

ርዕስን መሠረት የሚያደርግ የቁርዓን ተፍሲር እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ መቃሲድን መሰረት ወደ አደረገ ተፍሲረ ተጉዟል። በርዕስ ላይ ተመርኩዞ የሚሠጥ ትንታኔ እንዱ አንዱን የሚያሟላ ወጥ አድርጎ ቁርዓንን ይመለከታል። ይህ ጠቅላይ የሆነ አመለካከት የቁርዓንና የተወሰነውን ርዕስ ለምሣሌ ከሙቶ የሚይበልጡት የድንጋጌ እንቀጾች ማዕቀፍን በማስፋት ሁሉንም ስለ እምነት፣ ታሪካ ፣ትንሣኤና ስለ ህዋ የሚናገሩ እናቅፅትን በማካተት አንድ አይነት ምስል ይሠጣል። ይህን መሠረት በማድረግ የፊቅህ ድንጋጌዎች ያስቀምጣል። እንደዚህ አይነቱ አካሄድ ለመርህ ና ለሥነምግባር ዕሴት ይህንኑ ዕድል ይሠጣል። ይህ ማለት የፊቅህ ድንጋጌዎች ህግ ብቻ ሣይሆን በሥነምግባር የተላበሠ ይሆናል ፡፡ በቁርዓን ላይ የነሣነው ርዕሣዊ ትንተኔ በዚሁ መልኩ ሀዲስም ላይ ተግባራዊ ይሆናል ። ይህ ማለት ሐዲስ የሚያነሳውን ርዕስ ከአጠቃላይነትና የነብዩን የህይወት እንቅስቃሴ በመቃሲድ መነፅር በማየት እና በመረዳት ትንታኔ ያደረግለታል። ይህ መንገድ ምናልባት ሐዲሱ ከአስላማዊ ስነምግባር ጋር የሚጋጭ ከሆነ የሐዲሱን ትክክለኛነት (ሶሂህነት)ለመመርመር ዕድል ይሠጠዋል። ዑለማዎችም ሁለት የሚቃረኑ የሚመስሉ ሐዲሶችን ለማስማማት ከተቸገሩ አንዱን ውድቅ ለማድረግ ከቁርዓን መርህ ጋር ይበልጥ ተስማሚ የሆነው ለመምረጥ ያስችላል። ሐዲሱን በቃላትም ሆነ በትርጉም ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ተመራማሪው ከእስላማዊ መርህ ጋር ያለውን ስምምነት ማየት አለበት። በመጨረሻው ማለት የምፈልገው በመቃሲድ የተመሠረተ አካሄድ ከሐዲስን ከመረዳት ተያይዞ ያሉ ክፍተቶች ይሞላል፣ በተለይ ከክስተትና ከገጠመኝ ጋር ተያይዞ ያለውን ክፍተት። ምክንያቱም ብዙዎቹ ሐዲስዎች ከአንድ ወይም ከሁለት ዐረፍተነገር የተዋቀሩ ለጥያቂ መልስ የተሠጡ ሀረጎች ናቸው። ይህ ማለት የተነገሩበትን አጋጣሚና ክስተት ፣ በምን ሁኔታ ሆነው ሰሃቦች እንደሰሙትና እንዴት አድርገው ተግባራዊ እንዳደረጉት የሚያመለክት ነገር ያላቸውም። ይህ በመሆኑ ሁኔታውን ለማውቅ ለዘጋቢው ወይም ለዓሊሙ በራሱ ምርምር እንዲደረሰበት የተተወ ነው። የጠቅላይነት እይታ እንደዚህ ያለውን ክፍተት ለመሙላት እና የጥያቄውን ጠቅላይ (ዓም)የትኛው የተገደበውን(ኻስ )መሆኑን ለመረዳት ያግዛል። ይህ የሚሆነው የመቃሲድ አሸሪዓ (የሸሪዓ መደራሻ ግቦችን ) ዕውቀተ መሠረት በማድረግ ነው ።

## ነብያዊ መዳረሻ ግቦች (መቃሊድ ነበዊያ ) መረዳት

ባለፈው ርዕሥ በተጨማሪ መነሳት የሚገባው ነገር ከነበዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግርና ተግባር ጀርባ ያለው ግብና ፍላጐት መረዳት ሀዲሱን በተገቢው መልኩ ለመጠቀም ይረዳል ። የታለቁ አሊም ቀራፊ የነበዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባር በተመለከተ ፍርድ፣ ፈትዋ፣ መሪነት በማለት መከፋፈላቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል። እነዚህ ተግባራት እንደ ልዩነታቸው ሚናቸው የተለያየ መሆኑን መጥቀሱን እናስታውሣለን ። ኢብኑ አሹር ይህን ሐሣብ የሚያጠናክር ና ሌላ ጎኑን የሚያሳን ፅሑፍ አቅርበዋል ። አብኑ አሹር ይህን በተመለከተ በምሣሌነት ከፃፉት ውስጥ ለአብነት የተወሰኑትን እናስቀምጣለን ።

1.የሸሪዓ ድንጋጌ ታሳቢ ያደገ :- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሀጅተል ወዳዕ ግዜ ለሰሐቦቻቸው "የሀጅን ተግባር ከእኔ ወሰዱ" ብለው ተናግረዋል እንደዚህ ዓይነቱን ከአምልኮ ጋር የተያያዘ ነገር ሙሉ በሙሉ እንዳለ መከተል ይገባል።

2. ፈትዋን ታሳቢ ያደረገ፡- ፈታዋን (ብይንን )ዓላማ ያደረገ ተግባርን እንደምሣሌ ሆኖ የሚቀርበው የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባር በሀጀተል ወዳዕ ግዜ ወደ ነብዩ አንድ ሠው በመምጣት "ድንጋይ ሳልወረወር መስዋቴን አረድኩኝ "አላቸው ነብዩም ችግር የለውም አሁን ድንጋዩን ወርወር አሉት። ሌላው ሠው ደግሞ መጥቶ "መስዋቴን ሳላቀርብ ፀጉሬን ላጬሁ "አላቸው ነብዩም "ችግር የለውም አሁን እረድ" አሉት። የሐዲሱ ዘጋቢ ሲናገር ያዚያን ቀን ሰዎች እየመጡ ይህን ሳንሠራ ይህን አሰቀድምን እያሉ የጠየቁትን ሁሉ ችግር የለውም በማለት መልሠውላቸዋል ። እንደዚህ ያለው ሀዲስ እንዳለ መከተል ሲገባን ሀሣቡ ግን ፈትዋ (ብይን )መስጠት ነው። የፈትዋ አሠጣጥ አንድ የአምልኮን ተግባር ከመግለጽ ባለፈ ሰፋ ያለ መሆኑን እንረዳለን። ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ የመጣበት ካልሆነ በስተቀር የሀጅ ሥነሥርዐት ተግባራት ተራ እንደሌላቸውም መረዳት ችለናል ።

3.ፍርድን ታሳቢ ያደረገ፡- አብኒ አሹር ለዚህ ምሳሌ አድርገው የቀረቡት ሀዲስ ሁለት የሀድረመውታና የኪንዳ ሠዎች በመሬት ዙሪያ ነብዩ ጋር ቀረበው ያደረጉትን ክርክር ነው። ከሁለቱ ተከራካሪዎች እንዱ ገጠሪው "ፍርድ ሰጠን "ባለው

መሠረት እፈርድላችኋለሁ ብለዋል። እንደዚህም በሁለቱ ባለትዳሮች ሀቢባና ሳቢት መሀከል ፈርዳዋል። ሀቢባ ቢንት ሰህል ቧላን ሳቢትን እንደምትወደው እንደፈታት እንደማትፈልግ አቤቱታ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ )አቀረበች ። የአትክልት ቦታውን ትመልሽለታለሽ? ብለው ነብዩ ሲጠይቋት በተስማማች ግዜ የአትክልቱን ቦታ ተረክቦ እንዲፈታት አዝዋል። እንደዚህ አይነት ሐዲሶች አጠቃላይ ድንጋጌ ሳይሆን ዳኛው የምታየውን የሚፈርድብት ሁኔታ ነው የሚያሳየው ።

4.መሪነትን ታሳቢ ያደረገ ፡- (የነብዩ ሰ.ዐ.ወ እንደ መሪ ) የዚህ ምሳሌው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጠፍ የሆነን መሬት አቅንቶ አንድ ሠው መውሰድ እንደሚችል የፈቀዱበት ሐዲስ ፣ በኸይበር ጦርነት ግዜ የአህያን ስጋ መብላት የከለከሉብት ፣ በሁነይን ዘመቻ ግዜ ማንኛው ሰው የማረከውን መውሰድ ይችላል ብለው የፈቀዱበት፣ እነዚህና የመሳሰሉት ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከሸሪዓ መደረሻ ግብ አንፃርና ከሰፊው ህዝብ ጥቅም ጋር በሚጣጣም መልኩ መወሰድ አለበት ።

5.ግሳጼ ታሳቢ ያደረገ ፡-(ይህ ክፍል በድንጋጌ ላይ ሰፋ ያለ ነው ) በዚህ ረገድ አንደ ምሣሌ የምንወስደው ቡኻሪ የዘገቡት ሀዲስ ነው አቡዘር (ረ.ዐ.)ና ባሪያውን አግኝቻቸው ባሪያው ሙሉ የክት ልብስ ለብሷል ይህ ነገር ምንድነው ብዩ ጠየቁኩት። አቡዞርን ባሪያን ስደብኩት በእናቱም አነወርኩት ባሪያውም ወደ አላህ መልዕክተኛ በመሄድ ከሠሠኝ ነብዩ( ሰ.ዐ.ወ) ከእናቱ አነወርከው? አንተ የጃሂሊያ ጠባይ ያለብህ ሠው ነህ አሉኝ ። ባሪያዎቻቸሁ ሠራተኞችቻሁ ናቸው። በዚህ ሀዲስ የነብያዊ ግሳጼ እናገኛለን ።

6.እርቅን ታሣቢ ያደረገ፡- ለዚህ ጉዳይ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነው የበሪራ ሀዲስ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሪራን ወደ ባሏ እንድትመለስ ሀሣብ ሲያቀርቡላት በሪራ ግን “የአላህ መልዕክትኛ ሆይ እያዘዙኝ ነው ? ”ስትል ጠየቀች “እየሸመገልኩነው ” ሲሏት እንደዚህ ከሆነ “ አልፈልገውም ” ብላ አለች። ሌላው ምሳሌ የሚሆነው ሀዲስ ቡሃሪ የዘገቡት የጃቢር ሀዲስ ነው ጃቢር አባቱ ሲሞት ብዙ እዳ ትቶበት ሄዶ ነበር። ነብዩ( ሰ.ዐ.ወ) አባዳሪዎችን እዳውን እንዲተውለት ለማግባባት ቢሞክሩም አልተስማሙም። ሌላው በማስተርቅ ዙሪያ የተዘገበው ሀዲስ ከዕብ ኢብኑማሊክ ለአብዳላህ ቢን ሀድረድ ያበደረውን ገንዘብ እንዲመልሰለት

ቢጠይቀውም መክፈል ባለመቻሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግማሹን የዕዳ መጠን እንዲከፍል ጠይቀውት ከዕብም በሃሣቡ ተስማምቷል።እነዚህ የተጠቀሱ ሀዲሶች ሁሉም የሚያስረዱን ነብዩ ለሰሃቦቻቸው የቀረቡት ሀሣቦች ትዕዛዝ ሳይሆን ማስታረቅን በማሠብ ነበር ።

7.ምክር መለገስ ታሳቢ ያደረገ፡- ለዚህ እሳቤ ምሣሌ የሚሆን ሀዲስ ኡመር ቢን ኸጣብ ለአንድ ሰው ፈረስ በስጦታ ካበረከቱለት በኃላ ሰውየው ፈረሱን በርካሽ ይሸጠዋል ብለው ስለ ገመቱ በተሻለ ዋጋ ከራሱ ከሰውዩው ፈረሱን ለመግዛት አሰበው በጉዳዩ ላይ ነብዩን( ሰ.ዐ.ወ) ያማከሯቸዋል ። "በአንድ ድርሃም አንኳን ቢሰጥህ እንዳትገዛው። የሠጠውን ስጦታ የሚቀበል የተፋውን እንዳሚበላ ውሻ ነው "አሉት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስጦታን መልሶ መቀበል ክልክል ነው የሚል ድንጋጌ አላስቀመጡም። ዘይድ በዘገባው ሌላ ሀዲስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "አዝዕርትን ፍሬው ሳይደርስ እንዳትሸጡ" ብለዋል። ዘይድ በነብዩ ንግግር ላይ አስተያየት ሲሰጥ "ይህን ያሉት የሰዎች ክርክር ሲበዛ በምክር መልኩ ነበር "ይላል። በሁለቱ ሐዲሶች ላይ ሰሃቦች እንደተረዱት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በግዴታ መልኩ አላዘዛቸውም።

8.ተቆርቋሪነትን ታሳቢ ያደረገ ፡- ኑዕማን አቢኑ በሺር ባወራው ሀዲስ " አባቴ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከልጆቹ ለአንዱ ልጅ ብቻ ስጦታ እንደሠጠው ነገራቸው። ነብዩ ሰ.ዐ.ወ ለሁሉም ልጆች ሶጦታ ስጥታሃል ወይ ? ሲሉ ጠየቁት። የለም አልሰጠሁም ብሎ ሲመልስላቸው፡ በበደል ላይ ምስክር አታድርጉኝ አሉት። ከዚህ ሀዲስ ማሊክ ፣ አቡሃኒፋም ሆኑ ሻፊዕ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን አይነት የስጦታ አሰጣጥ ክልክል አድረገዋል የሚል ግንዛቤ አልወሰዱም ። የሐዲሱ በተዘገበበት ሌላው መንገድ ላይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ሌላ ሰው አስመስክር" ማለታቸው ይህንኑ ሐሣብ ያጠናክራል ።

9.ሠዎችን በመልካም ተግባር ላይ ለማነሣሣት ታሳቢ ያደረገ ፡- ይህን ታሳቢ ያደረገ የነብዩ ንግግርና ተግባር በብዙ የነብዩ ትዕዛዛት ላይ እናገኛለን። ይህን ሲያደርጉ በግዴታ መልኩና ሁሉንም ሠው ለማዘዝ አይደለም። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ሀዲስ ቡኻሪ ከበራእ ቢን ዓዚብ የዘገበት ሀዲስ ነው። "ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ

)በሰባት ነገር አዘውን ፣ ሰባት ነገር ከለከሉን ፡- የተማመን መጠየቅ ፣አስክሬንን መሸኘት፣ የአነጠሰን ሠው ይማርህ ማለት ፣ጥሪን ማክበር ፣በነዚህ ሲያዙን ፣ ለወንዶች የወርቅ ቀለበት ማድረግ በብር ዕቃ፣ በሀር የተሰራ የፈረስ ግላስ፣ ለወንድ የሀር ልብሶችን መጠቀም ከልክለውናል።" እነዚህ ትእዛዝና ክልከላዎች አንደሚታወቀው ከፊሎቹ ግዴታ ሲሆኑ ከፊሎቹ ሰሀቦችን ከቅንጦት መገለጫዎች ነፃ ለማድረግ ነው ።

10.ታላቅ ነገርን ለማስተማር በማሰብ፡- ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ተከታዩ ሐዲስ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለአባዘር(ረ.ዐ) "እሁድ ተራራን የሚያህል ወርቅ ቢኖረኝ ሦስት ዲናር ሲቀር እለግሠው ነበር ።" ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ሲሉ ሁሉም ሙስሊም ይህን ተግባራዊ እንዲያደርግ በማሠብ አልነበረም ።


11.ሥርዐትን ለማስተማር ታሳቢ በማድረግ፡- ኢብኑ አሹር እንደተናገሩት አንዳንዴ ለማስፈራሪያ ግነት ተጨምሮበት ይመጣል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆን ሀዲስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ወላሂ አላመነም፣ ወላሂ አላመነም፣ ወላሂ አላመነም ብለው ሲሉ ማነው የአላህ መልዕክተኛ ብለው ሰሐቦች ብለው ጠየቋቸው። "ተንኮሉን ጐረቤቱ የማያምነው ሠው" በማለት መልሱ እዚህ ላይ ሠውየው ሙሉ በሙሉ አማኝ እይደለም ለማለት ሳይሆን የእምነቱን ጎዶሎነት ለማመልከት ነው ።

12.ምንም አይነት ትምህርታዊ መልዕክት የሌለው፡- ይህ ማለትም እንደዚህ አይነቱ ተግባራቸው በድንጋጌ፣ በአምልኮት ፣ በግብረገብነትም ሆነ " ከስርዓት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ይህ ማለት ነብዩ (ሰ.ዐ .ወ ) በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸው ሲመገቡ፣ ሲለብሱ፣ሲተኙ ፣ሲጓዝ፣ ሲጋልቡ፣ የሙሣሠሉት እንቅስቃሴዎች በዚህ ክፍል ውስጥ ይመደባሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሀጀተል ወዳዕ ግዜ በበኒኪናና ውሃ አጠገብ ያለ (ሙሀሠብ) የተባለ ኮረብታማ ቦታ ላይ ማረፋቸውን የሚጠቅሰው ሀዲስ ነው። በዚህ ሐዲስ ላይ እናታችን ዓኢሻ (ረ.ዐ) አስተያየት ስትሰጥ እንዲህ ብላለች። "እዚህ ቦታ ላይ ማረፋቸው ከሀጂ ሥነሥርዐት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም እዚህ ቦታ ላይ ያረፉት ወደ መዲና ለመመለስ አመቺ ቦታ ስለ ነበረ ነው።"እስካሁን የተዘረዘሩት የአብኑ አሹሩ የሀዲሶችን አረዳድ እኛም ለሸሪአዊ መረጃዎች የለንን ግንዛቤ ፣

የአረዳድ መንገድ ከፍ ያደርገ ነው። ይህ ማለት የቁርዐንና የሀዲስ ጥቅሶች ዙሪያ ያለንን አረዳዳንና አተገባበር ግትር እንዳይሆን እድል ይሠጠናል ።

**<u>አድራሽ "መንገድ መዝጋት" አንፃር "አድራሽ መንገድ መከፈት"</u>**

አድራሽ መንገድ መዝጋት የሚለው ግንዛቤ በፊቅህ በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን የሚሠጠው ትርጉም ወደ ተከለከለ መንገድ የሚያዳርሱ ነገሮች መከልከል ማለት ነው ። ወደ ክልክል ያደርሳል ተብሎ የሚከለከለው ነገር ወደ እርም የማዳረሱ ጥርጣሬ ካለማዳረሱ የበለጠ መሆን አለበት የሚለው ሀሣብ ላይ አብዛኛዎቹ ዑለማዎች ይሰማማሉ ። ይህን መሠረት በማድረግ ወደ ዕርሞ የሚያዳርሱ ሁኔታዎች በአራት ደረጃ አስቀምጠውታል።




ለመቀጠል እነዚህን አራት ደረጃዎች ለመረዳት እንዲቻል በምሳሌ አሰደግፈን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን ።

1.የተረጋገጠ ፡ - ጉዳት ወይም ዕርም ጋር የሚያደርስ ተግባር ለሚለው ብዙ ግዜ ዑለማዎች እንደ ምሳሌ የሚጠቅሱት "ዋና መንገድ ላይ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር" ነው ። ይህ ተግባር ክልክል መሆኑን ሁሉም ዑሉማዎች የሚሰማሙበት ሲሆን ነገር ግን የውሃ ጉዳጓዱን የሚቆፍረው አካል ኃላፊነቱን የሚወሰድና ጥፋት ቢደርስ ቅጣቱን ለመቀበል ዝግጁነት ያለው ከሆነ መቆፈር ይችላል ወይስ አይችልም በሚለው ዙሪያ የልዩነት ሀሣብ አላቸው ።

2.አንዳዴ ወደ ጉዳት ወይም አርም የሚያደርስ ለሚለው አል ኢማም አልሻጢቢይ እንደ ምሳሌ የሚጠቅሱት "ወይንመሸጥ" ሲሆን ይህ ማለት ወይኑን

የገዛው ሰው ምናልባት ለአሰካሪ መጠጥ ሊጠቀመው ይችላል ። ይህ የመሆኑ መጠን አነስተኛ ስለሆነ “መዳረሻ መንገድ መዝጋት” በሚለው መርህ ወይን መሸጥን ክልክል ማድረግ አይቻልም። ኡለማዎችእንደሚሉት “የተግባሩ ጥቅም ከጉዳቱ የበዛ ነው፣ የሚደርሰው ጉዳት በጣም በጣም አነስተኛ ነው።”

3.ጉዳት የማድረሱ ሁኔታ ና መጠን በብዛት ይሆናል ለሚለው ክፍል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው ግጭት ባለበት ግዜ የጠና መሣሪያ መሸጥ ፣መጠጥ ኮማሪ ለሆነ ሰው ወይን መሸጥ የሚለውን ነው የሀንበልያና የማሊኪያ መዝሀብ ተከታዮች “መደረሻ መንገድን መዝጋት” የሚለውን መርህ ተከተለው ክልክል አድርገዋል። የሻፊዕያና የሀነፊያ መዝሃብ ተከታዮች ግን ጉዳት መድረሱን እርግጠኛ እስካልሆነ ድርስ ክልክል አይሆንም ብለዋል ።

4.አንድ አንድ ዑለማዎች ሴት ልጅ ብቻዋን ብትጓዝ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ብለዋል። እንደዚህም በውስጡ አራጣ ያለው ግን በተፈቀደ ውል የታሰረ ግብይት ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ። እንደዚህ አይነት ተግባር ክልክል እንደሆነ ማሊኪያ ሃንበሊያዎች ሲያስረግጡ ሌሎቹ ግን እርግጠኛ ያልሆነ የበዛ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ክልክል አይሆንም ብለዋል ።

ከላይ የተዘረዘሩት ምሳሌዎች በግልጽ የሚያሳዩን ነገር ቢኖር ምክንያት (ስልት )ና ግብ እንደዚሁም ከስልት እና ከግብ ጋር ተያያዥ የሆኑት ኢህቲማላት(ምናልባት ሊሆን የሚችል ) ካለው ፖሊቲካው ና ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ተጨባጭ ጋር ሊለዋወጡ እንደሚቻሉ ነው ። ብቸዋን የምትጓዝ ሴት፣ የጦር መሣሪያ መሸጥ ፣ ወይን መሸጥ ጉዳት ሊያደርሱ እንደሚችሉ ሁሉ ምንም ጉዳት ሊያደርሱ ምናልባት ጥቅም ብቻ ሊያስገኙ የሚችሉበት ሁኔታ አለ። ይህን መነሻ በማድረግ የተፈቀዱ ነገሮችን እንዳዴ ሊያደርሱት የሚችሉትን ጉዳት በማየት ብቻ በቋሚነት ክልክል ናቸው ማለት ተገቢ አለመሆንን እንረዳለን ።

“ መደረሻ መንገዶችን መዝጋት” የሚለው መርህ ነገሮች የሚደረሱበትን ሁኔታ በማየት የሚሰጥ ፍርድ ሲሆን ይህ ትልቅ ጥቅም ያለው መርህ አንዳንዴ ደግሞ በትክክልኛው መንገድ በአንዳንድ ወግ አጥባቂዎች በትክክል ተግባር ላይ ላይውል ይችላል ። ፖለቲካዊ ዓላማ ያላቸው አምባገነኖች የሰዎችን መብት ለመንጠቅ ይህን

መርህ አለግባብ ይጠቀሙበታል። ይህንኑ "የመዳረሻ መንገድ መዝጋት" መርህ አዲሶች የግልብ መንገድ ተከታዮች በብዛት ሲጠቀሙበት እናያለን ። በተለይ ሴቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ላይ ይህ መርህ ካለ አግባቡ ጥቅም ላይ ሲውል እናያለናል ለምሣሌ ሴት ልጅ መኪና መንዳት ፣ብቻዋን መጓዝ፣ በቴሌቪዥን ና በሬድዮ ጣቢያዎች መስራት፣የፖለቲካ ተሳትፎ፣በጎዳና ላይ ብቻዋን መንቀሳቀስ "መዳራሻ መንገድ መዝጋት"የሚለውን መርህ ተጠቅመው ሲከለከሉ ይሰተዋላል ።

"መዳረሻ መንገድ መዝጋት "የሚለውን መርህ በስህተት ተግባር ላይ ማዋል ለሚለው አባባል ጥሩ ማሳያ እንዲሆን በተቀጣይ አንድ የተሠጠ ፈታዋ እንጥቀስ ።

**ጥያቄ** ፡- የሴት ልጅ መኪና መንዳት እንዴት ይታያል፣ ሴት ልጅ መኪና በራሷ ከምታሽከረክር እና በሹፌር ከምትጓዝ የትኛው ጉዳቱ ቀላል ነው? ስለዚህ ጉዳይ ምን ትላላችሁ ?

**መልስ** ፡- ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው "ወደ ክልክል ነገር የሚወሰድ ተግባር ክልክል ነው" ከሚለው መርህ በመናሳት ነው ሴት በራሷ መኪና መንዳት ብዙ ጥፋቶችን ያስከትላል ። ከጥፋቶቹ መሐከል ፡- ሂጃብን ማውለቅ እንዱ ነው ምክንያቱም አንድ ሴት መኪና ስታሽከረክር የወንዶች ዕይታን የሚሰበውንና የፈተና ምንጭ የሆነው ፊቷን ትገልጣለች። ምናልባት አንድ አንድ ሠው ሴትልጅ መኪና ስታሽከረክር ጥቁር መነፀር መልበስ ትችላለች ብሎ ሀሣብ ሊያነሣ ይችላል ለዚህ የምንሠጠው መልስ ይህ የመኪና ማሽከርክር ጥማት ያላበቸው ሴቶች ይህን ለማድረግ ፍላጐት የሌላቸው ናቸው ። ሌላው የሴቶች መኪና ማሽከርከር የሚያስከትለው ጥፋት ሀፍረት መንጠቁ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለሴቶች በተደጋጋሚ ከቤት መውጣት ብቻዋን ወደፈለገችበት እንድትሄድ ምክንያት ይሆናል። ምናልባትም በፈለገችበት ሠዓት እስከ ለሊት ውጭ ልትቆይ ትቻላለች። ሌላው ጥፋት ሴቶች በቤተሠባቸው ፣ ለትዳር አጋሮቻቸው ታዛዥ እንዳይሆኑ ና በቀላል ነገር ሲያከርፉ አየር ለመቀየር በሚል ሰበብ ከቤት ርቀው እንዲሄዱ ያደርገቸዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ ጥፋቶችን የሚያሰከትል ሲሆን ለምሣሌ ትራፊክ መብራት፣ የነዳጅ ማደያ ላይ ማቆም፣ ብልሽት ሲያጋጥማት ከሌሎች እርዳታ መጠየቅ እና ይህን ዕድል ተጠቅሞ ወረዳ የሆነ ሠው ከብሯን

የሚያጐድፍ ጥያቄ ሊያቀርብላት ይችላል። የሴት ልጅ መኪና ማሽከርከር የመንገዶችን መጨናነቅ እና ወንድ ወጣቶችን የመኪና መንዳት የስራ ዕድል ማስጣት ነው። የአደጋ መብዛት ሌላው ጥፋት ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ሴት ልጅ ከወንድ ልጅ ባነሣ መልኩ ቆራጥነት ፣የማስተዋል ችሎታ ያንሣታል።

"አዳራሽ መንገዶችን መዝጋት" የሚለው ግንዛቤ ተነፃፃሪ የሆነዉ "አዳራሽ መንገዶች መከፈት" የሚለውን መርህ አወንታዊ አማራጭ እንዲሆን በማሠብ አንዳ አንድ የማሊኪያ መዝሃብ ሊቆች እንስተዋል።

አልቂራፊ የሸሪዓዊ ድንጋጌዎችን ወሳኢል (ስልት )ና መቃሲድ( ግብ) በሚል የከፈላቸው ሲሆን ማንኛውም ወደ ዕርም ግብ የሚያዳርስ ማንኛውም ስልት ክልክል ይሆናል። ከአንፃሩም ወደ ተፈቀደ ግብ የሚያዳርስ ማንኛው ስልት የተፈቀደ መሆን ይገበዋል ። አልቂራፊ በዚህ አጋጣሚ ስልትና ግብ ያላቸውን ግንኙነት ለማሣየት ሞክሯል።

ይህን መሠረት በማድረግ ግብን በሦስት ደረጃ መጥፎ፤ መልካም ፤ መካከለኛ በማለት አሰቀምጧል። ይህንኑ የአልቂራፊ "መንገድ የመከፈት" ግንዛቤ ሌላው ኢብኑ ፈርጁን የተባለው የማሊክይ መዝሀብ ሊቅ ተግባራዊ አድርጐታል ።

| | | |
|---|---|---|
| ወደ መጥፎ ግብ መዳረሻ የሆነ ስልት ክልክል ነው | መካከለኛ ግብ መዳራሻ የሆነ ስልት የተፈቀደ ነው | መልካም ግብ መዳረሻ ስልት የተፈቀደ ነው |

ከላይ ከተጠቀሰው ሃሣብ የምንረዳው የማሊኪም መዘሃብ ሊቆች እኩይ ነገር ለመከልከል መንገድ መዝጋት ተገቢነቱን በመናገር ብቻ ሳይቆሙ ወደ መልካም ነገር የሚያዳርሱ መንገዶችንም ክፍት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ለማሣወቅ ርቀው ሄደዋል ። ከዚህ በመነሣት አንድ ተግባር በቁርዓንና በሀዲስ ባይጠቀስም ቅሉ ፡ የሠዎችን ጥቅም የሚያረጋግጥ ከሆነ መበረታታት አለበት ።

## የአለም አቀፋዊነት ግብ ሃሣብ ማሳካት (ማረጋገጥ )

በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ መልካም ባህል ሸሪዓ እውቅና የሚሰጠው ሲሆን በሸሪዓና በባህል መሀከል ያለው ግንኙት ከእውቅና መሠጠት ሰፋ እና ውስብሰብ ያለ ነው። በትክክል ስናየው በመጀመሪያው የአስላም ግዜም ሆነ በቅርብ ግዜ የአረብ ማህረሰብ ባህልና ወግ በብዙ የፊቅህ ህግና ድንጋጌዎች ላይ ቀጥታኛ ተፅዕኖ አሳደረዋል። ይህን ተግዳሮት ለማሰወገድ ኢብኑ አሹር አዲስ እይታ ያቀረበ ሲሆን "አልመቃሲድ አሸሪዓ"በተሰጠው መጽሐፉ ባህልና ወግን የሚመለከትና የሚተነትን የኢስላም ሸሪዓ አጠቃላይነት የሚል ርዕስ አሰቀምጧል። በዚህ የመጽሐፍ ክፍሉ ኢብኑ አሹር እንደተለመደው ሀዲስን ተግባራዊ ለማድረግ ባህልና ወግ ያለውን አስተዋጽኦ ሳይሆን ያነሣው ባህልና ወግ ምን ያህል በሀዲስ ግንዛቤያችን አረዳዳችን የሳረፈውን ተጽዕኖ ነው። ዑለማዎች ኢስላም ለሁሉም የሠው ልጆች ለሁሉም ቦታና ግዜ ተሰማሚ መሆኑን በተናገሩት መሠረት ሀዲሶችንም የኢስላም ዓለም አቀፍዊነት ከግንዛቤ በማሰገባት መረዳት እንዳሚገባን ኢብኑአሹር ይናገራናል ፤ የኢስላም ዓለም አቀፋዊነትን የሚያሰረዱ የቁርዓን አንቀጾችንም ይጠቀሳል ፤ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በነብይነት ከአረቦች ለምን እንደተመረጡ በስፋት ይናገራል ፡፡ አረቦች ሰልጣኔ ይልነበራቸውና ከማንኛውም ማህበረሰብ ጋር በቀላሉ መቀላቀልና መስማማት የሚችሉ መሆናቸው ፤ በዙሪያቸው ካሉ ህዝቦች ጋር የከፋ ግጭትና ጥላትነት ስላልነበራቸው ፤ የኢስላምን መልዕክት ለመሸከም አመቺ ሰለነበሩ ነው ይላል ። ይህን ዕድል ኃያሎቹ ቤዛንታዊያን ፋርሶቻ ሮሞች ግብጾቻ ለምን እንዳላገኙት ለማስረዳት ኢብን ኢሹር ተከታዩን ጽፏል ።

"የሸሪዓን አጠቃላይነት ስንመለከት በማንኛው የዓለም ክፍል ያሉ ለሁሉም የኢስላም ተከታዮች በአቅማቸው ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚችሉ ድንጋጌ መሆኑ ነው። ለዚህም አላህ (ሱ.ዐ) ሸሪዓን አእምሮ ሊረዳው የሚችል ፤ ምክንያታዊና ጥበብ የተላበሠ አድርጐታል ። የአንድን ማህበረሰብ ባህልና ወግ በሌላው ማህበረስ ላይ መጫን ተገቢ እንዳልሆነና ፤ የድንጋጌ መሠረት መሆነ የለበትም ብለን እናምናለን ። የባህሉ ባለቤቶችም ቢሆኑ ባህላቸው ከሸሪዓ ድንጋጌ ጋር ሊቀላቀ ል አይገባም ይህን ስንገነዘብ ምንም አይነት ጥፋት የማያሰከትሉ ግን ሸሪዓ የከለከላቸው ነገሮችን ሁኔታ መረዳት እንችላለን። እንደ ፀጉር መቀጠል፤ጥርስን

መሣል ፤ንቅሳት ያሉ በቀደሙት አረቦች የድከመትና የቅሌት ምልክት ተደረገው ይታዩ ስለነበርና ሴቶችን ከዚህ አይነቱና ክብረን ከማጉደፍ ለመጠበቅ የተከለከለ ነዉ ። በቁርአንም

﴿يَا أَيُّهَا النَّبِيُّ قُلْ لِأَزْوَاجِكَ وَبَنَاتِكَ وَنِسَاءِ الْمُؤْمِنِينَ يُدْنِينَ عَلَيْهِنَّ مِنْ جَلَابِيبِهِنَّ ذَٰلِكَ أَدْنَىٰ أَنْ يُعْرَفْنَ فَلَا يُؤْذَيْنَ وَكَانَ اللَّهُ غَفُورًا رَحِيمًا ﴾

**“አንተ ነብዩ ሆይ ! ለሚስቶችህ ለሴቶች ልጆችህም ለምእምናን ሚስቶችም ከመከናነቢያዎቻቸው በላያቸው ላይ እንደለቁ ንገራቸው ፡ ይህ እንዲታወቁና (በባለጌዎች )እንዳይደፈሩ ለመኾን በጣም የቀረበ ነው፡ አላህም መሓሪ አዛኝ ነው ።”አህዛብ 59**

ይህ በዚህ አንቀጽ የተቀመጠው ድንጋጌ የአረቦችን ባህል ከግምት ያስገባ ሲሆን መከናነቢያ (ጅልባልብ) አንደባህል የማይቆጥሩ ህዝቦች ይህ ድንጋጌ አይመለከታቸው። የሸሪዓ ለሁሉም ዘመንና ቦታ የመበጀት ትርጉም አጠቃላይ ህጉ ህግ ብቻ ሳይሆን ጥቅም ያካተተና አንድ ግብ ሊያረጋጥ የሚችሉ የተለያዩ ህጐች ማስቀመጥ የሚችል መሆን አለበት።”

የአለምአቀፋዊነት እሣቤ መሰረት በማድረግ አብኑ አሹር ያቀረበው ሀሣብ ሀዲስን የምንረዳበት መንገድ በወቅቱ የነበሩ አረቦችን ሁኔታ ከግንዛቤ ያደረገ መሆን ይገበዋል የሚል መልዕክት አለዉ ። ሀዲሶቹም የሰዎችን ግብረገብነትና እንቅስቃሴ በቋሚነት ያለምንም ገደብና ቅድመ ሁኔታ ገዥ መሆን የለባቸውም። ከዚህ በመነሣት ነዉ ኢብኑ አሹር የተጠቀሡትን የቁርዓንና የሀዲስ ጥቅሶችን ከሰነ ምግባር መዳረሻዎች አንፃር የተረዳቸዉ እንጂ የቃላቶችን መልዕክት በማየት ብቻ አልነበረም። ይህን የአረዳድ መንገድ መከተል ለሸሪዓ ያለን ግንዛቤና አተገባበር አመቺ፤ ያለንበት ከባቢና ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ይሆናል። በተለየ ከአረብ ከባቢ ውጭ ለሚኖሩ ሙስሊሞች ይህ አካሄድ አዋጭ ነው ።

## **መቃሲድ(የሸሪዓ መዳረሻ ግብ )በእስላም የተለያዩ መዝሀቦች መዕከል የጋራ መድረክ**

የ21 ክ/ዘመን የሙስሊሞች መገለጫ ክፍፍል ሲሆን ይህ ክፍፍል በመዝሃቦች መሐከል ጎልቶ ይታያል። ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለው መከፋፋል ደግሞ በሺዓ ና በሱና መሀከል ያለው ልዩነት ነዉ። ብዙ ሠዎች በሺዓና በሱና መሐከል ያለው ልዩነት ፖለቲካዊ አድረገው ይወስዱታል ይሁን እንጂ የመዝሀብ ቅርጽ ይዞ እናገኘዋለን። የፊቅህና የአቂዳ ልዩነቶችን ጠንቅቀው የማያዉቁ ሰዎች በፊተኛውና በአሁን ግዜ በሺዓና በሱና መሐከል ያለው ልዩነት የአምነት ልዩነት ሳይሆን የፖለቲካዊ እንደሆነ ይገልፃሉ ። ይህ ቢሆንም ቅሉ ልዩነቱ ሰፍቶ ሁሉንም አውድ በማዳረስ ከፍርድ ቤት እስከ መስጂድ ና መኃበራዊ ኑሮ በአንዳንድ ሀገራት ደሞ አፋሳሽ ግጭትለመሆን በቅቷል። በዚህ ልዩነት የፖለቲካዉ ከፍተኛሚና ሲኖርው ግጭቱ ጠባብነትን ሌላውን ያለመከተል ዝንባሌና አብሮና ተቻችሎ ለመኖር መቸገርን አስከትሏል። የሺዓም ሆነ የሱና ሊቋውንት ስለ መቃሲድ የፃፋትን ጽሑፋች የደሰሳ ጥናት ለማድረግ ሞክሬ ነበር። ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር የሁለት ጭፍራ ጸሃፍት ስለ መቃሲድ የፃፉት ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው። በጣም ትኩረት የሚስበው ደግሞ ሁለቱም ወገኖች ስለ መቃሲድ ሲተነትኑ መሠረት የሚያደርጉት ተከታዩን መንገድ ነዉ፡- ኢጅቲሃድ (ምርምር )፣ቂያስ፣ (ልኬት)፣ ሙብት ፣ መርህና እሴትን ፣ ስነምግባርን ነው ። መንገዳቸው ብቻ ሳይሆን የሚመሳሰለው ዋቢ የሚያደርጋቸው ሊቆች ተመሣሣይ ናቸው ። ለምሣሌ አልጀወይኒ፤ አልቡርሃን ከመጽሃፎች ደግሞ የኢብኑባበወይሀ(ዒለሉሸሪዓ) ፤ የገዛሊ (መስተስፋ)፤ የሻጢበይ አልሙዋፋቃት፤ የሰድር (አልኡሱል)፤ የበኒአሹር (አልመቅሲድ) የተሰኙ መጽሐፍቶች ናቸው። ይህ ብቻ ሳይሆን የሚጠቀሟቸው ሙያዊ ቃላቶች ተመሣሣይ ነው ። ለምሳሌ አዶሩሪያት (አንገብጋቢ ) ፤ ሃጂያት(አስፈላጊ )ተህሲናት (ማሚያ) ጥቅል ግብ (አልመቃሲድ አማ) ፣ ልዩ ግብ (አለመቃሲድ ኻሣ) ና ሌሎችም ። በሺዓና በሱና ዑለማዎች መሐከል ያለው ልዩነት መሠረትዊ ህግ እና ግቦች ሳይሆን አንዳአንድ ሀዲሶችን መቀበልና አለመቀበል ላይ በመሆኑ እንድአንድ በተግባር የሚከናወኑ ዝርዝር ድንጋጌዎች ላይ ልዩነት እንዲታይ አድርጓል። ይሁን እንጂ በመቃሲድ ዙሪያ ያለው አካታች አካሄድ በአንድ ሀዲስ ወይም በአንድ አስተያየት ላይ ብቻ ያላጠረ በመሆኑና አጠቃላይ የሆነ መርህ ላይ ተመስርቶ የሚጓዝ ስለሆነ ና የጋራ መድረክ

ስለሚያመቻች  ከፍ ያለው የመቃሲድ ዓላማ ማለትም የሙስሊሞችን አንድነት ማረጋገጥ የጋራ ተግዳሮትን አብሮ መጋፈጥ ያስችላል። አንድነትን ማረጋገጥና የጋራ ተግዳሮትን መጋፈጥ ዝርዝር ከሆኑ የፊቅህ ጉዳዮች የበለጠ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።  ለዚህ ነው የሸዓው ዓሊም አያቱላህ መሀዲ ሸምሱደን ማንኛውም ሙስሊም ሺዓም ይሁን ሱና እርስ በእርስ መጋጨትና ጉዳት ማድረስ ፍጹም የማይፈቀድ  መሆንን የተናገረው።  ዓሊሙ  ይህን ሲናገር ታላቁን የመቃሲድ ዓለማ የሆነውን ስምምነት፤ እንድነት ፤ ፍትህ መሠረት በማድረግ ነው። የመቃሲድ ስልት ምርምራችን ከፍ ወደአለ ደረጃ የሚያሳድግ ከመሆኑም ባሻገር በታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣውን የፖለቲካ ልዩነት መፍትሄ ለማበጀትና የእርቅና በሰላም አብሮ የመኖር ባህልን የማሳደግ እድል ይሰጣል።

## <u>መቃሲድ በሃይማኖት መሐከል ውይይት ለማድረግ</u>

ሥርዓታዊ የሃይማኖት ጥናት( Systematic theclogy )  ሰነ መለኮት የሚባለው የጥናት ዘርፍ የሃይማኖቶችን ወይም የአንድ ሃይማኖትን ምንነት፤ አጠቃላይ ስዕል፤ ለማወቅና ለመረዳት የምንጠቀመው የጥናት ዘርፍ ነው። ይህ የጥናት ዘርፍ የአንድ ሃይማኖት ታሪኩን ፤ፍልስፍናውን፤ የዕውቀትና የሰነ ምግባር ዕሴት በመመርመር ስለሃይማኖቱ የተሟላ ስዕል ያሰቀምጣል ። ይህ ዘመናዊ የሆነ ሃይማኖት ላይ የሚደረግ ምርምር ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን በክርስትና ያሉ የተለያዩ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሠራል ። ይህ የጥናት መንገድ ክርስትናን መሠረት በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስን በጥቅል በመውሰድ ስለ አንድ ርዕስ ምን ይላል ? ብሎ ይጠይቃል። የተለያየ ርዕስን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥቅሶችን  በአንድ ላይ በማሰባሰብ  የተሟላ ቅርጽ  ይሰጣል ። ለምሳሌ :- ጸሎትን ፤ ፍትህን ፤ ጽናትን ፤ እዝነትን ፤ አንድነትን ፤ ልዩነትን፤ ስነምግባርን፤ መዳንን ና  ሌሎች ርዕሶችን በማንሣት በዚህ መልኩ ጥናት ያደርገባቸዋል።  ጥናቱ የሚካሄደው “በክትትል” ሲሆን ይህ አካሄድ አጥኚዉን ነገሮችን ለመሠብሠብ፤ በአይነት በአይነት ለመከፋፈል ፤አንድ አንዱን እንዲያሟላ አድርጓ ለማስቀመጥ ይረዳዋል። የተበታተኑ እውነታዎች የሚላቸውን ርዕሦች አንድ ላይ በመሠብሠብ በመሀከላቸው ያለውን ግንኙነት በመለየትና ገዥ ሃሣብ በማውጣት ጥናታቸውን ያካሄደሉ።

ቻልስዝ ሆድጅ የተሰኘ የዚህ ዘርፍ ተማራማሪ የጥናቱ ዘርፍ አሰፈላጊነት ተከታዮቹን በነጥቦች በመዘርዝር ያሰረዳል ።

1.የሠው ልጅ አእምሮ በተፈጥሮው ነገሮችን በአጠቃላይ የማሠባሠብና የማገጣጠም ባህሪ አለው ።

2.ይህ የጥናት ዘርፍ ተበታትነዉ የተቀመጡ እውነታዎችን በመሠብሠብ ከፍ ወደአለ ዕውቀት ማደራጀት ስለሚያስችል።

3.የጥናት ዘርፉ እውነታዎቹን በመሠብሰብ ሁሉንም ሊያስማማ በሚችል መልኩ ማቅረብ ይህ መሆኑ እውነታዎቹን ከተቃርኖ ለመጠበቅ ይረዳል።

4.የቁሣዊው አለምና ባህሪና የራዕዩ ዓለም ባህሪ ተመጋጋቢ መሆናቸው የዚህን ጥናት ዘርፍ አስፈላጊነት ያጎላዋል ። የሰው ልጅ ተመራምሮ ና እጥንቶ የጌታን ስራ ማወቅና ከፍጥረት ጋር ያለውን ትስስር ማወቅ እንዳለበት አምላክ እራሱ ማድረጉ ነው ።

ሃይማኖቶችን ለማጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ሥርዕታዊ ሥነሙለኮት የመቃሲድ (የሸሪዓ መዳረሻ ግብ )የጥናት ዘርፍ ጋር ከፍተኛ ተመሣሣይነት አላቸው። መቃሲድም (በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ እንደተመለከተነው )የቁርዓንና የሐዲስ ጥቅሶችን 'ክትትል" በማድረግ አጠቃላይና መሠረታዊ የሆኑ እንደ ፍትህ ፤ሥነ ምግባር ና የተለያዩ ጥቅሞችን ማረጋገጥ ነው ።

የመቃሲድ ዕይታ ብዙ ርዕሦች በመለየት ጥበቃ የሚሹ አሰፈላጊ ነገሮች ለይቶ አሰቀምጦልናል ። ሃይማኖት ፣ ህይወት ፣ ገንዘብ ፣ አእምሮ ፣ ዘር፣ መጠበቅ አለበት ብሎ ነገሮናል። በስርዓታዊ ሰነ መለኮት ላይ ምርምር የሚያደርጉ አጥኒዎች ተመሣሣይ ሁሣብ የሚያነሱ ሲሆን ለምሣሌ ህይወትን ፣ጤናን፣ አሰካሪ መጠጥን እስከ ስካር ባለመጠጣት መጠበቅ የሚል ሃሣብ ያነሣሉ። ኢስላም ሙሉ በሙሉ መጠጥን ክልክል በማድረጉ ከነርሱ የተለየ አቋም አንዲይዝ ያደርገዋል። ይህ የሆነው የመጥፎ ነገር መዳረሻ መንገድን መዝጋት በሚለው መርሁ ነው። እነርሱ ቤተሰብን መንከባከብና መጠበቅ የሚል ሃሣብ ያነሣሉ ፤ በተመሣሣይ ኢስላም ዘርን መጠበቅ በሚለው ርዕስ ስር የቤተሰብ እንክብካቤን ያነሣል።

የመቃሲድ የጥናት ዘርፍ ከዚህ በፊት የነበሩ አቅጣጫዎችን እንደወረዱና እንደተበታተኑ ከመረዳት ይልቅ ለሃይማኖት ሊቆች በአጠቃላይ ማዕቀፍ ውስጥ ሁነው የተለያዩ ሃይማኖታዊ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ እንዲንችሉ ይረዳቸዋል። በተበታተነ መልኩ ያሉትን ትዕዛዛት እንደወረደ መረዳት ሃይማኖት ዓለማ የማያደርገውን ዋናውን የሰነምግባር ዕሴት እንዲዘነጋና በተለያየ ከባቢ ና ሁኔታ ትዕዛዝት ተፈጻሚነት እንደሚለያይ መረደት እንዲሳነው ያደርጋል ።

ከዚህ በመነሣት ሃይማኖትን ለማጥናት የሚጠቀሙት ሥርዐታዊ ሥነ መለኮትም ሆነ የመቃሲድ የጥናት ዘርፍ በሃይማኖቶች መሀከል የሚደረጉ ውይይቶችን ለማሳለጥ ከፍተኛ ሚና ይጫውታል ብዩ አስባለሁ።

## የመቃሲድ ሸሪዓ (የሸሪዓ መዳረሻ ግብ )አተገባበር

## ስለ ሥነ ምግባር ጥያቄና መልስ

በኢስላሚክ ኦንላይን ኔት የፈትዊ ድህረ ገጽ ከተለያዩ አገራት የደረሱኝ ብዙ ጥያቄዎች ሲሆኑ በድህረ ገጽ (ስለ ኢስላም ጠይቅ )የሚለው የኢንተርኔት ፎረም ላይ ከተነሱ ጥያቄ ብቻ መሀከል በኢሜል ከደረሱኝ የተወሠኑትን የራሴን ጥቂት ማስተካከያ በማድረግ አቀርባቸዋለሁ። እነዚህ ጥያቄዎችን የማቀረበው መቃሲድ ሸሪዓ ምን ያህል በግዚያችን የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ለማሳየት ነው። ጥያቄዎች መስሊም የሆኑና ያልሆኑ ሠዎች የነሣቸው ናቸው ።

**ጥያቄ ፡-** በሸሪዓ ስለመቃሲድ ስናወራ ስለስነምግባር የምናወራ ይመስለኛል። እኔ በምዕራብ ሀገር እንደምኖር አንድ ሙስሊም በምዕራብዊ የሥነምግባር መርህና በኢስላም የሥነምግባር መርህ መሀከል ከፍተኛ ልዩነት አስተውላለሁ። ይህ ልዩነት የመነጨው በግዜ ለውጥና ዕድገት እንዲሁም የነበረዉን የቆየ ባህል በፅናት በማቆየት የመጣነው ብዬ አምናለሁ። በእስልምና ከሄ/ከ ዘመን ጀምሮ እኩይ ተግባር ነው ተብሎ የሚታሰበው አሁንም መጥፎ ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል። በምዕራቡ የሰነምግባር መርህ ግን እንደዚህ ሆኖ እናገኘውም። የምዕራቡ ዓለም ከዘመን ጉዞ ጋር ስለ ስነምግባር ያለው ዕይታ እየተቀየረ ይሄዳል። ስለዚህ ጉዳይ እስከ አስተያየት ስጡኝ ?

**መልስ ፡-** ለዚህ ዋና ና አስፈላጊ ጥያቄ መልስ የምሰጠዉ ከሁለት ነገር አንፃር ነው::

1ኛ. የሥነ ምግባር ዕሴትና የአማራጭ ስነምግባር ለይተን መመለከት ተገቢ ነው ማለትም ግብ ተደርገዉ የሚወሰዱ ዕሴቶችና የሥነምግባር መተግበሪያ መንገዶች ለይተን ማየት አለብን። ታላቁና ግብ የሆነው የስነምግባር ዕሴት ብለን የምንጠራቸው አንደፍትህ ፣ ዕኩልነት ፣ ታማኝነት ፣ አደራን መወጣት ፣ ነፃነት ፣ ጥብቅነት ፣ መቻቻል ና የመሣሠሉት ነገሮች ሲሆኑ መቼም ቢሆን ማንኛው የዕድገት ደረጃ ብንደርስ እነዚህ ነገሮች ሊቀየሩ ና ሊለወጡ አይችሉም። እነዚህ ቋሚ ዕሴቶች ናቸው።

የሥነምግባር ግብረገብነቶች ወይም የስነምግባር አማራጮች ብለን የጠቀስነው በዕለት ከዕለት ህይወታችን ተግባራዊ የምናደርጋቸውና ዋናውን የስነምግባር ዕሴት የሚጠብቁና የሚያጠናከሩ ናቸው። ለምሣሌ ፍትህ በማንኛው ቦታ ና ግዜ መሠረታዊ ነገር ሲሆን በፍትህ መፍረድ የሚለው ግንዛቤ ግን እንደ ህብረተሰቡ ባህልና ተጨባጭ ፍትህ ብሎ በሚጠራውና በሚያምንበት አኳኃን ይወሰናል። ማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል የሚተግብረው በቅድመ ሁኔታ የተገደበና የተለየ መብትና ኃላፊነት መኖር አለበት ይህ መብትና ግዴታ በአንድ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ስርዓት መአቀፍ ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል ። ይህ መብትና ኃላፊነት ወደሌላ ማህበራዊ ስርዓት ስንሸጋገር ሊቀየርና ሌላ ገጽታ ሊኖረው ይችላል። ይህን የሚወሰነው በኃብረተሰቡ ውስጥ ያለው ባህልና ወግ ሲሆን፡ ጎጂ እስካለሆነ ድረስ ባህልና ወግ በፍትህ ሥራዓቱ ውስጥ ቦታ ና ዋጋ ሊሠጠው ይገባል ።

2.ኛ እዚህ ላይ መነሳት የሚገባው ነገር የአምልኮ ሥነሥርዓት እንደወረደ ቃል በቃል የሚተገበርና በማንኛውም ቦታና ግዜ ለውጥ ሊገባው አይችልም። ለምሳሌ በቀን የምናከናዉነዉ የአምስት ግዜ ሶላት ለዉጥን አይቀብልም ። ከሰላት በፊት ያለው የትጥበት ሥርዓት (ወዱእ)፤ የሶላት ረከዓ ብዛት ፤ የሚከወንበት ግዜና በሙሉ የሩኩዕ የሱጁድ እንቅስቃሴው ሊቀየር አይችልም ። እንደዚሁም ዘካ (ምፅዋት )ተመሣሣይ ነው። ማንኛውም መስሊም ከሥርዓተ አምልኮ ጋር ተያይዞ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ መከተል ብቻ እንጂ በአምልኮ ሥርዐቱ ላይ ለዉጥ ለማድረግ የሚያስችለው ጥበብም እውቀትም ችሎታም የለውም ።

ግብረገብነትን (የዕለት ከዕለት የህይወት እንቅስቃሴን )በተመለከተ ግን መረጋገጥ ካለበት ግብና ዓላማ እንፃር ተፅዕኖ ሊያደርግበት ና ሊቀያየር ይችላል ። ይህን ስንል ግን አንድ አንድ እርም የተደረጉ ተግባረት ለውጥ ይደረግባቸዋል ማለት አይደለም ለምሣሌ አስካሪ መጠጥ ፣ ቁማር ፣ አራጣ፣ ዝሙት የመሳሰሉ ተግባራት ዕርምነታቸው ምንም አዲስ ምርምርና ክርክር በማይቀበል መልኩ ግልጽ በሆነ የቁርአን አንቀጽ ክልክል መሆናቸው ተቀምጧል። መመራመር የሚፈልግ ከነዚህ ድንጋጌዎች ጀርባ ምን ግብ ተረጋገጠ ብሎ መመራመር ይችላል ። ከዚህ በመነሳት ዕርሞ የተደረገው ነገር የተከለከለበት ምክንያትና ጥበቡ ምን እንደሆነ የተለያየ ውጤት ልናገኝ እንችላለን። የውጤቱ መለያየት ግን በግልጽ የቁርአን አንቀጽ ወይም ትክክል (ሶሂህ)በሆነ ሀዲስ አርም የተደረገና ማንኛውም ሙሲሊም ነኝ የሚል ግለሰብ ተግባራዊ ማድረግ ግድ ይለዋል።

**ጥያቄ፡**- ነገሮች በፍጥነት በሚቀያየሩበት በዚህ ዘመን ሸሪዓ በሥነምግባር ዕድገትና ለውጥ ላይ እንዴት አሰተዋጾኦ ሊያደርግ ይችላል ?

**መልስ፡-** ሸሪዓ አንድ ድንጋጌ ሳያስቀምጥ በስተጀርባው ታላቅ ግብን ማረጋገጥ ዓላማ አድርጎ ነው። ይህ የሸሪዓ ልዩ ባህሪ ሲሆን አምልኮንም (ኢባዳ ) ይሁን ግብረገብነትን (ተዓሙላት )የሚመለከቱ ድንጋጌዎች መዳረሻቸው ሥነ ምግባር (ሞራል )ነው ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)ወደ እዚህ አለም የተላኩበትን ሲናገሩ የሰዎችን ስነምግባር ለማሟላት ነዉ። ሌላ ምሳሌ መጥቀስ ካስፈለገ ሶላት ከመጥፎ ና ከሚጠላ ነገር ሁሉ እንደምትከለክል አላህ (ሱ.ወ.) በቁርዓን ነገሮናል። ሀጂ ሥነስርዓት ሲከወን ብልግና ማመጽና መከራከር እንደማይፈቀድ ቁርአን አስረግጦ ይናገራል። የዘካ (ምፅዋት )ዓላማ በሀዲስ እንደተገለጸው ከከበርቴዎች ተወስዶ ለድሆች የሚሠጥ ማህበራዊ ድጋፍ ነው። ሸሪዓ በግብረገብነት ረድፍ ያስቀመጣቸው የንግድ ፣ የውል ድንጋጌዎች አንደ ፍትህ ፣ አደራ መጠበቅ ፣ አለማታለል፣ ለደካሞዎችን ከለላ መስጠትን የመሰሉ የመልካም ስነምግባር ዕሴትን ለማስረጽ ታሳቢ ያደረገ ነው። ሸሪዓን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ብንችል ምንኛ በማህረሰባችን ውስጥ መልካም ስነምግባር በተስፋፋ ነበር ። በአጠቃላይ የኢስላም ሸሪዓ የስነምግባር ህግ ነው እንጂ የሃይማኖት አባቶች ህግ አይደለም ።

**ጥያቄ ፡-** ቁርዓን ላይ እንደተጠቀሰው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለዓለማት ዕዝነት እንዳተላኩ ይናገራል በእንፃሩ ደግሞ የሸሪዓ ስርዓት ጠንከር ያለ ሆኖ ሰናየው ሁለቱን ለማስታረቅ የከብደናል ። በሸሪዓና በነብዩ የተላኩበት ዕዝነት መሐከል ተቃርኖ ያለ አይመስልም? እስኪ ሥለዚህ ነገር ትንሽ ማብራሪያ ቢሰጡን ?

**መልስ ፡-** አዎ እንዳልከው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለዓላማት ሁሉ ዕዝነት ነዉ የተላኩት። ሸሪዓው ዉስጥም የተጠቀሰው ችግር አለ ብየ አላመንም።ሸሪዓ ለሠዎች ዕዝነት ያላበሰ የመጠቀ መልካም ስነምግባር ስርዓት ያጎናጸፈ ስርዓት ነው። ሁል ግዜ ይህን ሳስብ የታላቁ ዓሊም የሸምሱዲን ኢብነልቀይም ንግግር ትዝ ይለኛለን ።

“የሸሪዓ ድንጋጌ መሠረት የሚያደርገው የሠዎችን የምድራዊና የመጨረሻዉን ዓለም ጥቅም ነዉ ።ሸሪዓ ሙሉ በሙሉ ፍትህ ፣ እዝነት ፣ ጥበብ ፣ ጥቅም ነዉ ። ከፍትህ ያፈነገጠ ነገር ሁሉ በደል፤ ከእዝነት ያፈነገጠ ሁሉ ጭካኔ ከጥቅም ያገለለ ሁሉ ጥፋት፤ ከጥበብ የራቀ ሁሉ ዛዛታ እንጂ ሸሪዓ አይደለም። ሰዎች በተሣሣተ ግንዛቤና ትርጉም ሸሪዓ ሊያረጉት ቢሞክሩም ሸሪዓ ሊሆን አይችለም።”

በብዙ ሠዎች የአረዳድ ና የአተገባበር ጉድለት ብዙ ችግሮች የተከሠቱበት አጋጣሚ አለ። በጥያቄህ እንደጠቀስከው ይህ አይነቱ ችግር ስለ ሸሪዓ የተሳሳተ ምስል ይሠጣል ። ሸሪዓ ፍትህን፣ አዝነትን ፣ ጥቅምን ፣ ጥበብን ዓላማ ና ግብ ቢያደርግም አንድ አንድ ትልቅ የፖለቲካና ማህበራዊ ቦታ የሚሰጣቸው ግለሠቦች የራሳቸውን ግዜያዊ ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸውን ፣ ስልጣናቸውን ፣ ጥቅማቸውን ለማሰጠበቅ ሸሪዓን በተሣሣተ መልኩ ተግባራዊ ሲያደርጉ ይስተዋላል። ይህን ዓላማቸውን ለማስቀጠል ሲሉ የራሳቸው የሸሪዓ አረዳድ እንዲስፋፋ ጥረት ያደረጋሉ። እነዚህ ሠዎች የኢስላም ጠላቶች ሸሪዓን ከሚበድሉት በላይ ሲበድሉትና መጥፎ ምስል ሲያላብሱት እንመለከታለን።

**ጥያቄ፡-** ፍቅር የህይወት ታላቅ ግብ ነው የሰው ልጅ ደስታን ማግኘት ያሁልግዜ ምኞቱ ሲሆን ያሚወደው ሠው ጋር ፍቅር መለዋወጥ ደግሞ ደስታ ይሰጠዋል። ታዲያ በነፃነትና በሰላም ምንም ዓይነት የቤተሰብ ውስብስብ ህይወት ሳይጨመርበት ፍቅርን አንድንኖር ለምን አይፈቀድልንም? አንድ ትክክለኛ ሠው የፍቅር ፍሬን በስጋዊ አካሉ እንዲያጣጥመው እንዴት ይከለከላል። ይህን ክልክላስ የሸሪዓ እንዴትየስነ ምግባር አካል አድርጎ ይወስደዋል?

**መልስ ፡-፡** የብዙ ሙስሊሞች ተግባር ለሸሪዓ መጥፎ ገጽታ መስጠቱ ይታወቃል። ፍቅር አላህ (ሱ.ወ) ከለገሡን ፀጋዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ሠውን መውደዱ ይህን ፍቅር ለመግለጽ የሚደረጉ አካላዊ ግንኙነቶች መኖሩ ተፈጥሯዊ ነው። እስልምና ይህን ተፈጥሯዊ ሁኔታ ሥርዓት ያሲዘዋል እንጂ ተፃራሪ ሆኖ አይቆምም። ኢስላም ጋብቻ ባልፈፀሙ ሠዎች መሀከል ሥጋዊ ግንኙነት ይከለክላል እንጂ ኢስላም ፊቅርን ይከለክላል ያለ ማንም የለም። ኢስላም ለምን ህጋዊ ያልሆነን ግንኙነት ከለከለ ብለን ስንጠይቅ በፍቅርና በተለያዩ ዕሴቶች መሀከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ ይፈልጋል ። ለምሣሌ ቤተሠብ ተመስርቶ እንዲጸና ፤ ባለትዳሮች ደስተኛ ህይወት እንዲኖሩ ማስቻል ዋናው ግቡ ነው። ምክንያቱም ኢስላም ቤተሰብን የማኅበረሰብ መሠረት አድርጎ ነው የሚቆጥረው። አንደ ኢስላም እይታ አንድ ባለ ትዳር ወንድ ወይም ሴት ዝሙትን ከፈፀሙ ወንጀልን እንደሰሩ ይቆጥራል ፡፡ ዝሙትን የፈፀሙት ፍቅር ለማግለጽ ቢሆንም እንኳን የቤተሠብ ጽንሰ ሃሣብ ጋር ስለሚጋጭ ተቀባይነት የለውም። የተዋደዱት ጥንዶች ገና ጋብቻ ያልፈፀሙ ከሆኑ ደግሞ ኢስላም መዋደድን አይከለክልም ግን ይህን ፍቅር ወደ ሥጋዊ ግንኙነት መውሰድ ሳይሆን መጋባት እንዳለባቸው ያዛል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል

" لم أر للمتحابين إلا النكاح "

**"ለተዋደዱ ሁለት ጥንዶች ጋብቻ እንጂ ሌላ አላየሁም"**

እዚህ ላይ ራሱን የሚያነሳዉ ጥያቄ ሁለት ጥንዶች ህጋዊ ጋብቻ ሳይፈጽሙ በሚያደርጉት ገብረ ስጋ ግንኙነት ልጅ ቢፈጠር ልጁ ካለቤተሰብ የሚያድግበት ዕድል ሰፊ ሲሆን የልጅ ወንጀል ምን ስለሆነ ነው ኃላፊነት የሚወስድ ቤተሰብ በሌለበት ሁኔታ ማደግ የሚፈረድበት? በጥያቄህ ላይ እንዳነሰሃው ጥንዶቹ የቤተሰብን ውስብስብ ኃላፊነት ፈርተው ወይም ዕድሚያችን ገና ነው ብለው ልጅ መውለድን ማዘግየት ከፈለጉ ይህን ኢስላም አይቃወምም። ልጅ መወለድ ካለበት ግን በህጋዊ ቤተሰብ ማዕቀፍ ውስጥ ነው መውለድ ያለበት። ይህ ስናደርግ ህፃናትን ከበደበል ነፃ እናዳረጋቸዋለን። በብዙ የአላማችን ክፍል እንደሚታወቀው በአንድ ወላጅ በተለይ በነጠላ እናት ስር የሚያድጉ ህፃናቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል ይህ የማያስከተለውን ቀውስ እየተመለከትን ነዉ። እንዳልከው ፍቅር ድንቅ ነገር ነው ፡፡ ኢስላም ግን በዚህ ውብና ድንቅ ነገር

መሀከልና ቤተሠብ ፤ ማህበረሰብ በሚባል ታላቅ ዕሴት መሀከል ሚዛናዊ ማድረግ ይፈልጋል ።

**ጥያቄ ፡-** ኢስላም ሽብርተኝነትን እያበረታታ እንዴት የታላቅና የበጎ ሥነ ምግባር ሃይማኖት ነዉ ትላላች?

**መልስ፡-** ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት መጀመሪያ የሽብርተኝነትን ትርጉምና በትክክልኛው ሽብር የሆነዉንና ያልሆነዉን መለየት ያስፈልጋል ። ከዚያ መልሱ በራሱ ፍንትዉ ብሎ ይታያሃል ።ሽብርሃይማኖት የለዉም። ሽብር ኢስላም ፣ ክርስቲያን ፣ይሁዳ ፣ ቡድሃ፣ ሁንዱስ ነው ማለት ነው ና አንደኛው ሃይማኖት ጋር ማስተሳሰር አይቻልም። የአንድን ሃይማኖት ምንነት ለማወቅ ትክክለኛው ምንጭ የሆነዉ የራሱ መጽሐፍ የተሻለ ሲሆን ሁሉም በሚባል መልኩ ስለ ፈጣሪና ፍጥረት እይታ አላቸው። ተከታዮቻቸውንም በስነምግባር ለማነጽና ከፍ ያለ መንፈሳዊ ደረጃ እንዲደርሱ ያለማምዳሉ ። ሽብር ማለት ኃይል መጠቀም ማለት አይደለም፡ ምክንያቱም ሁሉም ትክክል አስተሣሰብ ያለው ሠው አንዳንዴ ኃይልን መጠቀም ተገቢ መሆኑን ያምናል ። የሠው ልጅ ራሱን ለመከለከል ኃይል ይጠቀማል፡ በመንገድ ላይ ጥቃት ከተፈፀሙብህ ኃይል ተጠቅመህ ራስህን ትከላከላህ፤ ወንጀልን በቁጥጥር ስር ለማዋል ኃይል መጠቀም አንዱ አማራጭ ነው፤ እንስሳትን በህጋዊ መልኩ ለማደን አንኳን ኃይል መጠቀም ግድ ይለናል። በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ኃይልን መጠቀም ችግር እንደለለው ሁሉም ሠው የማያምን ሲሆን ኃይል መጠቀምን ውግዝ ወይም ተቀባይነት ያለው የሚያደርገው የተፈፀመበት አኳኃን ነው።

ራስን መከላከል ሽብር አይደለም፡ ለምሣሌ የሆነ መሳሪያ የታጠቀ ቡድን አንተ ወደ አለህበት አካባቢ መጥቶ ጥቃት ቢከፍትና ከቤትህ አፈናቅሎ አካባቢውን ቢወር ወረራውን ለመቀልበስ ማንም እገዛ ባያደርግልህ ራስህን አዘጋጅተህ መከላከል መብትህ እንደሆነ አታምንም ? ግን ራሴን እከለከላሁ በሚል ስበብ በሌሎች ንፁሃን ላይ ጉዳት ማደረስ ተቀባይነት የለውም ፡፡

ሽብር የግለሰቦች ተግባር ብቻ ሳይሆን ግለስቦችን በመመልመል የራሳቸውን ፍላጎት ለማረጋገጥ የማንቀሳቀሱ ቡድኖች አሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን የታጠቀ

ሠራዊትና ከባድ መሣሪያ ተጠቅመው የሽብር ተግባር የማፈፀሙ አሸባሪ መንግስቶች እንዳሉም ማወቅ ተገቢ ነው ።

ንጹሃን ግለሠቦች በተለየዩ መልኩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ የሽብር ሰለባ የሚሆኑ ሲሆን ግድያ፣ የአካል ጉዳት ፣ በስቃይ ፣ ርሃብ ፣ የጤና አገልግሎት እጦት ፣ ከኢኮኖሚ ማዕቀብና ለሌሎች ጉዳት ይጋለጣሉ ።

የሽብር ጥቃት ለከተሞችና ከጦርነት ሩቅ በሆነ ቦታዎች ብቻ ሳይሆን የሚፈፀመው የጦርነት ቀጠና በሆኑ አካባቢዎች የሽብር ጥቃት ይድርሳል። ይህ የሚሆነው ተፋላሚ ሃይሎች የጦርነትን ሥነምግባር ወደ ጎን በመተው ሲቪሎችን የጦር አስረኞችን የሽብር ጥቃት ሰለባ ሊያደርጎቸው ይችላሉ ።

ማንኛውም የፍትህና የስብዓዊ መብትን መርህ የጣሰ ንጹሃንና በተማረኩ ወታደሮች ላይ የሚደርስ ጥቃት ሽብር ነው ብለን ከተስማማን ከዚህ በመነሳት ለሽብር ከመቃሲድአሽሪዓ እንፃር ትርጉም ልንሠጠው እንችላለን ፡፡

* ሽብር ማለት በማንኛውም ሁኔታ በሲቪልም ይሆን ሲቪል ባልሆኑ ሰዎች ላይ የፍትህና የሰብዓዊ መብት መርህ ጋር በሚጋጭ መልኩ ጉዳት ማድረስ ነው ።

## ማጠቃለያ

በዘመናችን የሚስተዋለው የኢስላማዊ ሸሪዓ አተገባበር ወይም በትክክልኛ አገላለጽ ቀጠቢስ አተገባበር ስንመለከተው አካታች ሳይሆን ግብታዊ ፣ ሥነ ምግባራዊ ሳይሆን ቃል በቃል ነገሮችን በጥቁር ወይም መነፀር ብቻ የሚያይ፤ አንድ አቅጣጫ እንጂ የነገሮች ብዙ አቅጣጫዎች የማያስተዉል፤ ቃላቶችን እንጂ ከጀርባቸው ያለውን ዓላማ ና ግብ ከግንዛቤ የማያስገባ ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ የቀደመውን ዕውቀትና ቀደምት ሊቆች ያስቀመጡትን ምርምር አይነኬና ቅዱስ አድርጎ ማየት ሲጨመርበት ነገሩን ከድጡ ወደ ማጡ ያደርገዋል። የሸሪዓን መንፈሳዊ ገፅታ ከማደብዘዝ በተጨማሪ የተለየ ሀሣብን አመንጪ ግለሠቦችን አለመቀበል ይስተዋልበታል። አክራሪ ርዕዮተዓለም ያላቸው ቡድኖች ማገንገንና መጠናከርን ፣ ነፃነትን መደፍጠጥን ፣ የአምባገነን ሥርዕትን መጠናከርን ያስከተላል። ይህን ሁሉ ችግር ለመፍታት (መቃሲድ )አሸሪዓ የዕውቀት ዘርፍ አይነተኛ መፍትሄ ነው ። ለውይይት በማቅረብ፤ በፍልስፍና ደረጃ በማንሳት ና በዘመናት መሃከል ያለውን ልዩነት በመገምገም የነበሩ የመዝሀብ ተቃርኖዎችን በማቀራረብ ፡ ዕርቅን አብሮነትንና ተቻችሎ መኖርን በማበረታታት መፍትሄ ይሰጣል ። በመጨረሻም የምንለው መቃሲድን ተግባራዊ ማድረግ የሁሉም ትኩረት ሊሆን ይገባል ።

# ይህ መጽሐፍ

መቃሲደ ሸሪዓ(የሸሪዓ ግቦች) ዛሬ እንገብጋቢ ከሚባሉ ምልከታዎች መካከል ኢስላማዊ አስተሳሰብን ለማስተካከልና ለማደስ ከሚያስፈልጉ ዕውቀቶች መካከል አንዱ ነው። መቃሲድ ምንድነው? በእስልምና ታሪክ ውስጥ ያለውስ ቦታ ምን ይመስላል? ባለፉት ዘመናት በመቃሲድ ዕውቀት የሚታወቁት ዑለማዎች እነማን ነበሩ? በዘመናችንስ ካለው ለብዓዊ መብት፣ማኅበራዊ ፍትህና ፖለቲካ ምልከታዎች ጋር ምን ግንኙነት አለው። ለለአዳዲስ ጉዳዮች ምልከታ በመዝሀቦች መካከል ስላለው አስተሳሰብ፣ በእምነቶች መካከል ስላለው ውይይት፣ ስለ‹‹ሽብርተኝነት›› ግንዛቤና ሥነምግባራት ..... በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ተነስተዋል።

ዶክተር ጃሲር አልዐውዳህ የመጽሐፉ አዘጋጅ ናቸው። በኳታር አሲስላማዊ ኮሌጅ ላይ በፖለቲካዊ ፕሮግራም ላይ መምሕር ናቸው። በብሪቴን ዌልዝ ዩንቨርስቲ በኢስላማዊ ሸሪዓና የምዕራባዊያን ሕግጋት ጥናት ላይ ዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በካናዳም በሚገኘው ዋተርሉው ዩንቨርስቲ በ ‹‹ ሙነዘማት አተሸሪዕ›› የዶክትሬት ዲግሪ አላቸው። በለንደን የመቃሲደ ሸሪዓ አንድ ተቋም ሥራ አስኪያጅ ናቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከዐሥር ዩንቨርስቲዎች በላይ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ